# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት


# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር የመጀመሪያ እትም 2014 ዓ.ም የሆነው አማርኛን እንደፌዴራል ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀውን የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መጽሐፍ ውስጥ የመፃፍ ክሂል ይዘት አደረጃጀት እና አቀራረብ መገምገም


በ

ቤዛዬ ፀጋዬ ኃይለማርያም



ነሀሴ 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ

# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር የመጀመሪያ እትም 2014 ዓ.ም የሆነው አማርኛን እንደፌዴራል ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀውን የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መጽሐፍ ውስጥ የመፃፍ ክሂል ይዘት አደረጃጀት እና አቀራረብ መገምገም


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት


ለተግባራዊ ሥነ-ልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤምኤ ዲግሪ

ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ


ቤዛዬ ፀጋዬ ኃይለማርያም


ነሀሴ 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ

## መታሰቢያነቱ

አሳድገሽኝ ‹‹ሀ››ብለሽ አስተምረሽኝ ዛሬ የደረስኩበትን ደረጃ  ሳታዪ ለተለየሽኝ ኤፍራታና ግድም  ካራቆሬ ገብርዔል ጓሮ  ቁጭ አርጌሽ  ለመጣሁት ውድ አክስቴ ወሮ.ቀለሟ መሸሻ ኃ.ማርያም ይሁንልኝ፡፡

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር የመጀመሪያ እትም 2014 ዓ.ም የሆነው አማርኛን እንደፌዴራል**

**ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀውን የ10ኛ ክፍል**

**የአማርኛ መጽሐፍ ውስጥ የመፃፍ ክሂል ይዘት**

**አደረጃጀት እና አቀራረብ መገምገም**

**የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ**

| | | |
|---|---|---|
| አማካሪ | ፊርማ | ቀን |
| ፈታኝ | ፊርማ | ቀን |
| ፈታኝ | ፊርማ | ቀን |

# ምስጋና

የሁሉ ነገሬ መሠረቱ የዕውቀቱ፣የዕድሜ የጤና…እግዛብሔር ነውና ምስጋና እና ክብር ለእርሱ ይሁን፡፡

በመቀጠል በዩንቨርሲቲው የድህረ ትምህርት ቆይታዬ ጀምሬ እስከማጠናቅቅ እና ለዚህ ያበቁኝን (ያስተማሩኝን) ውድ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል መምህራን እና የትምህርት ክፍሉ ልዩ ልዩ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን አመሠግናለሁ! አከብራችኋለሁ፡፡

በተለይ ልዩ ምስጋና የማቀርበው መምህሬ እና አማካሪዬ የካበቱትን ዕውቀት እና ልምዳቸውን በማካፈል አሁን ላለሁበት ደረጃ እንድደርስ አስተዋፅኦዋቸው ለላቀ ለዶክተር ግርማ ገብሬ ምስጋና ብቻ ሳይሆን አከብራቸዋለሁ፡፡

በመቀጠል ከፊደል ዕውቀት እስካሁን ድረስ ለእኔ ተነሳሽነት እና ሞራል ለሆነኝ በተለይ የእርሱን ሙያ (የሙያዎች ሁሉ ቁልፍ የሆነውን መምህርነት) ለእኔ በማስተላለፍ የሙያ ዓርማዬን ያዢ ብሎኝ መምህር እንድሆን ያደረገኝ፣የዚሁ ትምህርት ክፍል ተማሪ ለሆነው ምናልባት የእግዛብሄር ፈቃድ ከሆነ አብሮኝ የሚመረቀው ውድ አባቴን እና ባልደረባዬን ፀጋዬ ኃይለማርያምን አመሠግነዋለሁ!እወደዋለሁ፡፡

ባለሽ ነገር ብቻ ሳይሆን የእናትነትን ፍቅር ከልጅነት እስከ ዕውቀት እየሰጠሽኝ ከጎኔ በመሆን ምርኩዝ ለሆንሺኝ ውድ እናቴ በላይነሽ መሸሻ፣በተለይ እንድለይህ ፈቃደኛ የማትሆን ብለይህም በስልክ ዘውትር ጤንነቴን ብቻ ሳይሆን የሚቸግረኝን ነገር ሁሉ ለምትጠይቀኝ ፍቅር ፀጋዬ፣በመቀጠል ትከሻዬ ለሆንከው የትናየት ፀጋዬ፣ኪሴ ለሆንሺው አክሱማይት ፀጋዬ ሁላችሁንም አመሠግናችኋለሁ አወዳችኋለሁ፡፡

በማስተማር ብቻ ሳይሆን ካስተማረኝም በኋላ የዚህን ጥናት ሙሉ ወጪውን በመሸፈን አሁን ላለሁበት ደረጃ ያደረሰኝን አንጋፋውን (በኢትጵያ የመጀመሪያውን)የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲን አመሰግነዋለሁ፤የዚህ ዩንቨርሲቲ ተማሪ በመሆኔም እድለኛ ስለሆንኩ እግዛብሄርን፣በመቀጠል በብዙ ነገር ያስተናገዱኝን የዩንቨርሲቲውን ማህበረሰብ አመሰግናቸዋለሁ፡፡

በመጨረሻም ለዚህ ጥናት ከፍተኛ ሙያዊ ድርሻችሁን ለተወጣችሁ እና አስተዋፅዖ ላበረከታችሁ የዱራሜ ህዳሴ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡

## ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ምስጋና............................................................................................................ i
ማውጫ............................................................................................................ ii
ሠንጠረዥ ............................................................................................................ v
አጠቃሎ ............................................................................................................ vi
ምዕራፍ አንድ............................................................................................................ 1
መግቢያ............................................................................................................ 1
1.1.የጥናቱዳራ ............................................................................................................ 1
1.2.የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፡-............................................................................................................ 3
1.3.የጥናቱ ዓላማ............................................................................................................ 4
1.4.የጥናቱ ጠቀሜታዎች............................................................................................................ 4
1.5.የጥናቱ ወሰን ............................................................................................................ 4
ምዕራፍ ሁለት............................................................................................................ 6
ክለሳ ድርሳናት ............................................................................................................ 6
2.1.የመርሀ ትምህርት ምንነት ............................................................................................................ 6
2.1.1.የመርሀ ትምህርት ዓላማ............................................................................................................ 6
2.1.2.የመርሀ ትምህርት ባህሪያት............................................................................................................ 7
2.2.የቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ምንነት............................................................................................................ 8
2.2.1. የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ዓላማ ............................................................................................................ 8
2.2.2.የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ይዘት ............................................................................................................ 9
2.3.የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ አደረጃጀት............................................................................................................ 10
2.3.1.የመጻፍ ክሂል ምንነት ............................................................................................................ 11
2.3.2. የጽህፈት ትምህርት ዓላማ............................................................................................................ 11
2.3.3.የመጻፍ ክሂል የይዘት መምረጫ መስፈርት ............................................................................................................ 12
2.3.4.የመጻፍ ክሂል ይዘቶች አደረጃጀት............................................................................................................ 13
2.4. የመጻፍ ክሂል አቀራረብ ............................................................................................................ 14
2.4.1.ውጤት ተኮር አቀራረብ............................................................................................................ 14

2.4.2.ሂደታዊ አቀራረብ ............ 15
ምዕራፍ ሦሥት ............ 17
የጥናቱ ዘዴ ............ 17
3.1.1.የሰነድ ግምገማ ............ 17
3.1.2.የመምህራን ቃለ-መጠይቅ ............ 18
3.2.የመረጃ መትንተኛ ዘዴ ............ 18
ምዕራፍ አራት ............ 19
የመረጃ ትንተና የጥናቱ ውጤት ............ 19
4.1.የመረጃ ትንተና ............ 19
4.1.1.የመጽሀፉ አጠቃላይ ገጽታ ............ 19
4.1.2.የቋንቋ ትምህርትን ዓላማ መሠረት በማድረግ የተዘጋጁ አጠቃላይ የመጽሀፉ ቅኝት ............ 20
4.1.3. የአሥረኛ ክፍል የመምህሩ መምሪያን በማገናዘብ ከመማሪያ መጽሀፉ የተሰበሰቡ አጠቃላይ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ዝርዝር፡-............ 22
4.2.በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተካተቱ የጽህፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ............ 23
4.2.1.ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ ............ 23
4.2.2.ከአጠቃላይ ወደዝርዝር አቀራረብ ............ 27
4.2.3.ውጤት ተኮር አቀራረብ ............ 30
4.2.4.ሂደት ተኮር አቀራረብ ............ 31
4.2.1.ቅድመ ጽህፈት ............ 33
4.2.2.የጽህፈት ጊዜ ............ 33
4.2.3.ድህረ ጽህፈት. ............ 34
4.3.በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የጽህፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ............ 34
4.3.1.ተከታታይነት ............ 34
4.3.2.ተለጣጣቂነት ............ 37
4.4.የመጻፍ ክሂል ከሌሎች ክሂሎች ጋር ያለው አደረጃጀት ............ 39
4.4.1.የመ ጻፍ ክሂል ተዋረዳዊ አደረጃጀት ............ 40
4.4.2.ጎናዊ አደረጃጀት ............ 43
4.4.3.ተተገባሪነት ............ 46
4.4.የውጤት ማብራሪያ ............ 51

ምዕራፍ አምስት ........................................................................................................ 53
ማጠቃለያ እና አስተያየት .................................................................................... 53
5.1.ማጠቃለያ ............................................................................................................ 53
5.2.አስተያየት .............................................................................................................. 54
ዋቢ መጽሀፍት ........................................................................................................ 56
አባሪዎች ................................................................................................................... 58

## ሠንጠረዥ

ሠንጠረዥ አንድ በመጸሀፉ ውስጥ የተካተቱ (የሚገኙ) አጠቃላይ ይዘቶች ቅኝት ..................20
ሠንጠረዥ ሁለት ከመመሪያ የተሰበሰቡ አጠቃላይ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ዝርዝር .............22
ሠንጠረዥ ሶስት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የቀረቡ የጽህፈት ትምህርት ይዘቶች....................26
ሠንጠረዥ አራት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የቀረቡ የጽህፈት ትምህርት ይዘቶች....................29
ሠንጠረዥ አምስት በመጽሀፉ ውስጥ በተከታታይ የቀረቡ የጽህፈት ትምህርት ይዘቶች ........35
ሠንጠረዥ ስድስት የክሂሎችን ተዋረዳዊ አደረጃጀት የሚያሳይ አጭር መግለጫ ...................42
ሠንጠረዥ ሰባት የጽህፈት ክሂሎች ከሌሎች ክሂሎች ጋር ያለቸው ጎናዊ ግንኙነት ወይም አደረጃጀት.....................................................................................................44
ሠንጠረዥ ስምንት የጽህፈት ክሂል ከሌሎች የትምህርት ይዘቶች ጋር ያላቸው ጎናዊ አደረጃጀት.....................................................................................................45

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት ዋና ዓላማ አድርጎ የተነሳው በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር የመጀመሪያ እትም 2014 ዓ.ም የሆነውን አማርኛን እንደፌዴራል ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀው የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መጽሐፍ ውስጥ የመፃፍ ክሂል ይዘት አደረጃጀት እና አቀራረብ መገምገምን ነው፡፡ይህን ዓላማ መሠረት በማድረግ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀም ለግምገማው በተዘጋጁት መርሆዎች አማካይነት መረጃዎቹ ገላጭ የምርምር ስልትን በመጠቀም ተብራርተዋል፡፡በዚህ ጥናት ውስጥ አብይ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሆኖ ያገለገለው የሰነድ ግምገማ ሲሆን የሚገመገመው ሰነድም በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር የመጀመሪያ እትም 2014 ዓ.ም የሆነው አማርኛን እንደፌዴራልቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀውን የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መጽሐፍ ውስጥ የመፃፍ ክሂል ይዘት አደረጃጀት እና አቀራረብ መገምገም ላይ ሲሆን በተጨማሪ በአስረኛ ክፍል ላይ የሚያስተምሩ መምህራን በቃለ-መጠይቅ መረጃ ሰጪነት ተሳትፈዋል፡፡ መማሪያ መጽሀፉን በማንበብ እና በመመልከት እንዲሁም ከመምህራን የተገኙ የቃለ-መጠይቅ ምላሾች ለግምገማው በተዘጋጁት መርሆች አማካይነት ተተንትነዋል፡፡ የመረጃዎች ትንተና ውጤትም ለ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበው በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር የመጀመሪያ እትም 2014 ዓ.ም የሆነው አማርኛን እንደፌዴራል ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀውን የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መጽሐፍ አሥር ምዕራፎች እናዳሉት እና በአስሩም ምዕራፍ ውስጥ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች በተለያየ የአቀራረብና የአደረጃጀት መርህ እንደተዘጋጁ ተደርሶባቸዋል፡፡በመሆኑም የጽህፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ እና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአቀራረብ ስልት መኖራቸው ተስተውሏል፡፡በጽህፈት ክሂሉ አደረጃጀት ውስጥ የተከታታይነት እና ተለጣጣቂነት ዝግጅት ተስተውሏል፡፡የጽህፈት ክሂሎቹ በአስሩም ምዕራፍ 29 ጊዜ በተለያዩ የመማር ማስተማር ርዕሶች ወይም ይዘቶች በተዋረዳዊ እና ጎናዊ አደረጃጀት ቀርበዋል፡፡በአብዛኛው የጽህፈት ክሂሉ ትኩረት የተደረገው አንቀጽን በማነጻጸር እና በማወዳደር ከድርሰት ደግሞ በአመዛዛኝ ላይ ተደጋግመው እንደቀረቡ ታይተዋል፤ይህ ደግሞ ለተማሪዎቹ የጽህፈት ክሂሉን በተደጋጋሚ እንዲለማመዱ አጽንኦት እንደተሰጠበት ያመለክተናል፡፡በአጠቃላይ የጽህፈት ክሂል አቀራረቦች እና አደረጃጀቶች መርህን የተከተሉ በመሆናቸው ጠንካራ ጎናቸው አመዝኗል፡፡ስለዚህ ለወደፊት አዘገጃጀቱ በሌሎቹም የመጽሀፍት ዝግጅቶች ላይ ቢደገም የሚሉ የመፍትሄ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1.የጥናቱ ዳራ

የጽህፈት ትምህርት ይዘቶች ተማሪዎች የቋንቀዋውን የጽህፈት ክሂል ሥርዓት በሚገባ ተረድተው በትክክለኛ መንገድ ጥቅም ላይ እንዲያውሉ የሚያስችሉ መሆን አለባቸው፡፡
በመሆኑም የጽህፈት ክሂልን ከሌሎቹ የክሂል ዓይነቶች ለየት የሚያደርጉት በትምህርት ብቻ የሚገኝ መሆኑን እና ለመማርም ቅደም ተከተል ክንውን ያለው በመሆኑ መፃፍ አእምሮአዊ ተግባር እነደሆነ እና በተወከሉ ትምህርቶች ሀሳብ፣ስሜትና ፍላጎትን የመግለፅ ሂደት እንደሆነ ማረው (1996፡Vii) "መፃፍ ክሂል ብዙ ተግባር ነው፡፡ ርዕስ የመምረጥንና የማጥበብን፣ የቃላት አጠቃቀምን፣የአረፍተ ነገር አወቃቀርንና የአንቀፅ አደረጃጀትን ይጠቀማል፤ክሂሉ እየፃፉ መማርን የሚጠይቅ በመሆኑ ወደ ፅሁፍ ስራ ለመገባት መጀመሪያም ይሁን በኋላ በርካታ ሂደቶችን ማለፍ የግድ ይላል" በማለት ገልጸዋል፡፡
እንደማረው(1996) አባባል ከሂደቶቹ አንዱ ክሂሉ የተደራጀበትንና የቀረበበትን መንገድ ማየትን ይመስላል፡፡

በመሆኑም በቋንቋ መማሪያ መፃህፍት በይዘቶች አቀራረብ እና አደረጃጀት ላይ ስለሚደርጉ የግምገማ ዓይነቶች ምሁራን ሲዘረዝሩ፣ ግምገማ በሚካሄድበት ወቅት መታየት ያለባቸው ጉዳዮች በሶስት ደረጃ እንደ ሚከናወኑ ሲገልጹ ቅድመ አገልግሎት ግምገማ፣ የአገልግሎት ጊዜ ግምገማ እና ድህረ አገልግሎት ግምገማ ሲሆኑ ከነዚህ መካከል የአገልግሎት ጊዜ ግምገማ ትኩረት በሥራ ላይ ያሉ መማሪያ መጽሐፍት ታትመው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እየተማሩበት ወይም እየተገለገሉበት ባለበት ሂደት የሚከናወን የግምገማ ሥርዓት ነው በማለት ያብራራሉ (Cunnings worth 1995)፡፡
በመቀጠልም Dubbin &olishtain(1986) እንደሚያስረዱት መርሃ ትምህርት እና መማሪያ መፃሕፍት በትይዩ ወይም በቅንጅት መዘጋጀታቸውን መገምገም እና በመካከላቸው ልዩነት ካለ ፈትሾ የቋንቋ ትምህርትን ዓላማ (ክሂሎችንም ይሁን የዕውቀት ዘርፎችን) በተገቢ መንገድ መዘጋጀቱን በመፈተሽ የመማር ማስተማሩን ሂደት የተሸለ እና የተስተካከለ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል በማለት ይገልጻሉ፡፡

ከዚህ አንጻር መርሀ ትምህርት ዋነኛ የዚህ ጥናት አካል ባይሆንም የማንኛውም የትምህርት መጽሀፍ ዝግጅት መነሻ እና መሠረት የሚያደርገው መርሀ ትምህርቱን በመሆኑ የጽህፈት ክሂልን አደረጃጀት ብቻ ሳይሆን አቀራረብንም መፈተሸ እንደሚቻል ነው፡፡በመሆኑም በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር የመጀመሪያ እትም 2014 ዓ.ም የሆነውን አማርኛን እንደፌዴራል ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀው የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መጽሐፍ (2014፡iii) እንደሚከተለው ተገልጿል፡-

> መጽሐፉ የተሰናዳው ለደረጃው የተዘጋጀውን መርሐ ትምህርት መሠረት አድርጎ ነው፡፡ ተማሪዎች በደረጃቸው የተለያዩ ባህላዊ፣ ሳይንሳዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ አካባቢያዊ፣ ዓለማቀፋዊ፣ወዘተ. ይዘቶችን/ አሴቶችን በአማርኛ ቋንቋ እንዲገልጹ ስለሚጠበቅ፣ መጽሐፉ ለይዘቶችም ከክሂሎች ያልተናነሰ ትኩረት ይሰጣል፡፡ የዚህም ዋና ዓላማ ተማሪዎች በምንባቦች አማካይነት የንግግርና የማዳመጥ፣ የንባብና የጽሕፈት ክሂሎቻቸውን፤ የቃላትና የሰዋስው ዕውቀታቸውን እንዲሁም የሥነ-ጽሑፍ ችሎታቸውን እንዲያጎለብቱ ማገዝነው፡፡ መጽሐፉ ከሕይወት ተሞክሮ ጋር የተዛመደ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ተማሪዎቹ አዳዲስ ጉዳዮችን ለመማር ግላዊ ገጠመኞቻቸውን እና ልምዶቻቸውን እንዲጠቀሙ ይጠበቃል፡፡ በዚህም መሠረት ችግር ፈቺና አሳታፊ ተግባራትና መልመጃዎች በየምዕራፎቹ ተካተዋል፡፡ተግባራቱም ተማሪዎቹ ቋንቋውን በተለያየ መንገድ እንዲጠቀሙበት የሚያስችሉ ናቸው ፡፡

የመምህሩ መምሪያ በአብዛኛው የመምህሩን የክፍል ውስጥ የአቀራረብ ስልት ገላጭና ረዳት ቢሆንም የዚህ ጥናት አካል ተደርጎ አልተወሰደም፤ነገር ግን የጽህፈት ትምህርት የሚቀርብባቸውን መንገዶች በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር የመጀመሪያ እትም 2014 ዓ.ም የሆነውን አማርኛን እንደፌዴራል ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀው የ10ኛ ክፍል የአማርኛ የመምህሩ መምሪያ መጽሐፍ ውስጥ እንዴት መደራጀት እንዳለበት በመግቢያ ላይ እንደሚከተለው ተገልጿል፡-

> በመምህር መምሪያው ውስጥ ሁሉም ነገር አይጠበቅም፡፡ ይልቅስ አበይት ይዘቶቹን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፣ የተማሪዎችን ነባራዊ እውነታ ባገናዘበ ሁኔታ ወሳኝ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በማተኮር መጠቆሚያዎችን፣ ማመላከቻዎችን እና ፍንጮችን መስጠት ይጠበቃል፡፡መምህራን በዚህ ግንዛቤ ላይ ተመስርተው አቀራረቡን የበለጠ ማራኪና አመቺ ለማድረግ የሚያስችሏቸውን የአቀራረብ ዘዴዎችን ማሰብ እና በሥራ ላይ ማዋል ይችላሉ፡፡ ተማሪዎቹ ዘና ባለ ሁኔታ ትምህርቱን በጉጉት እንዲከታተሉ ለማትጋት የመምህራን ኪናዊ አቀራረብ ወሳኝ ነው፡፡ በተለይ ከተማሪዎቹ እድሜ፣ባህልና የዕውቀት ደረጃ ጋር የተገናዘቡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችንና ሌሎች ጨዋታ -ቀመስ ተግባራትን በመጠቀም የትምህርቱን ሂደት ሳቢና፣ ክፍለ ጊዜውንም ተናፋቂ ማድረግ ይቻላል፡፡

በመሆኑም በዚህ አገላለጽ በመጽሀፉ ውስጥ የጽህፈት ክሂሉ አቀራረብን እና አደረጃጀትን እንዴት እንደቀረበና እንደተደራጀ የተማሪውም ሆነ የመምህሩ መምሪያ መጽሀፎች ፍንጭ ሰጥተውናል፡፡ከዚህ አንጻር በመጽሀፉ ውስጥ የጽህፈት ክሂሎቹ የተደራጁበትና የቀረቡበት መንገድ በትክክል ከላይ እንደተገለጸው ነው እንዴ የሚል ጉጉት የሚፈጥር በመሆኑ በጥናት (በግምገማ) መረጋገጥ እንዳለበት

ነው፡፡በመሆኑም መጽሀፉ ገና በስራ ላይ ያልተተረጎመ አዲስ እና በሙከራ ደረጃ ያለ መሆኑ፣መጽሀፉ ለተዘጋጀላቸው ተማሪዎች እና ለሚያስተምሩ መምህራን ወይም ለ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ገና በበቂ ሁኔታ ያልተዳረሰ ያልተማሩትና ያላስተማሩት በመሆኑ ጠንካራና ደካማ ጎኑን ከወዲሁ ማወቁ አስፈላጊ ነው፡፡

## 1.2.የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፡-

ርዕሱ ለጥናቱ የተመረጠበት ምክንያት መማሪያ መጻህፉ አዲስ በመሆኑና ከዚህ ቀደም የተጠና ባለመሆኑ በውስጡ ያካተታቸው የጽህፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች እንዴት ቀረቡ? አደረጃጀታቸውስ ምን ይመስላል? የሚለውን ለመገምገም ነው፡፡

በመሆኑም በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር የመጀመሪያ እትም 2014 ዓ.ም የሆነው አማርኛን እንደፌዴራል ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀው የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መጽሐፍ ውስጥ የመፃፍ ክሂል ይዘት አደረጃጀት እና አቀራረብ መገምገም ሲሆን መጽሐፉን ገና ስራ ላይ ለማዋል በየክልሉ አልፎ አልፎ ሞዴል ተደርገው በተወሰዱ ጥቂት ትምህርት ቤቶች ላይ ለሙከራ ተጀመረ እንጂ በመላው ሀገሪቱ ላይ መሰጠት(መማር) በሚገባቸው ቦታዎች ላይ ሁሉ አልተጀመረም፡፡ በመሆኑም ሙሉ ለሙሉ በሥራ (በመማር ማስተማር) ተግባር ላይ ከመዋሉ በፊት በመጽሀፉ ውስጥ የጽህፈት ክሂልን የይዘት አደረጃጀት እና አቀራረብ አዲስ ከመሆኑም አንፃር መገምገም (መፈተሽ) ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም አጥኚዋ የሁለተኛ ደረጃ እና የዚሁ ክፍል መምህርት በመሆኗ ክሂሉን በተመለከተ የመጽሀፉ ዝግጅት የጽህፈት ክሂልን መርህ ተከትሎ መዘጋጀት አለመዘጋጀቱን ማወቅ ለመማር ማስተማሩ ሂደት አስፈላጊ በመሆኑ ነው፡፡ ይህን አስፈላጊነት ያለው (2009፡14) በርካታ ምሁራን ገምጋሚ ምርምርን ለማካሄድ የሚያስገድዱ ሶስት ምክንያቶች አሉ ይላሉ፡፡እነዚህም ምክንያቶች፡-

- አዳዲስ ፕሮግራሞችንና ተግባራዊ የሚደረጉ ፖሊሲዎችን የማሻሻል ፍላጎት፣
- የአዳዲስ አሰራሮችን ደካማና ጠንካራ ጎኖች በመለየት የተሸሉ ዘዴዎችን ለመቀየስ የሚኖር ፍላጎትና፣
- የተገኙ አዳዲስ ውጤቶችን ጉድለት፣ጥራትና ተቀባይነት ለመወሰን የሚሉ ናቸው በማለት ገልጸዋል፡፡ከዚህ አንጻር ስናይ ያለውም (2009)የገለጹት የመገምገምን አስፈላጊነት ነው፡፡

## 1.3.የጥናቱ ዓላማ

ይህ ጥናት ዋና ዓላማ አድርጎ የተነሳው በአዲሱ የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መጽሐፍ ውስጥ የመፃፍ ክሂልን የይዘት አደረጃጀት መገምገም ሲሆን ከዚህ ዋና ዓላማ የመነጩ ዝርዝር ዓላማዎች ደግሞ የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

1.በአዲሱ የአማርኛ ቋንቋ መጽሀፍ ውስጥ የሚገኙ ይዘቶች የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር ያላቸውን አደረጃጀት ጠንካራና ደካማ ጎን መለየት

2. የጽህፈት ክሂልን ለማስተማር የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እና የተማሪው ሚና በመጽሀፉ ውስጥ ይዘቱ እንዴት እንደቀረበ አደረጃጀቱን መፈተሽ

3. በመጽሀፉዝግጅት የጽህፈት ክሂል መልመጃዎችን አደረጃጀት እና አቀራረብን መፈተሽ

## 1.4.የጥናቱ ጠቀሜታዎች

ጥናቱ ለሥርዓተ ትምህርት ባለሙያዎች፣ለመምህራን እና ለተማሪዎች በሚከተለው ሁኔታ ይጠቅማል፣

1. ለስርዓተ-ትምህርት ባለሙያዎች ስለ ጽህፈት ክሂል የይዘት አደረጃጀት በመማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የተሻለ ግንዛቤ ኖሯቸው ጠንካራ እና ደካማ ጎኑን በመለየት ሥራዓተ-ትምህርቱን እንዲያዘጋጁ አመቺ ሁኔታ ይፈጥርላቸዋል

2. ለመምህራን፣በትምህርቱ ሂደት ከሚከተሏቸው የማስተማሪያ ዘዴዎች በተጨማሪ የተሻለ ግንዛቤ አግኝተው የመፃፍ ክሂልን በክፍል ውስጥ መተግበር እንዲችሉ ያግዛል ተብሎ ይታሰባል፡፡

3. በዚህ ርዕስ ዙሪያ ለሚደረጉ ቀጣይ ጥናቶች መነሻ እና ዋቢ በመሆን ያገለግላል፡፡

## 1.5.የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የሚደረገው በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር የመጀመሪያ እትም 2014 ዓ.ም የሆነውን አማርኛን እንደፌዴራል ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀውን የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መጽሐፍ ውስጥ የመፃፍ ክሂል ይዘት አደረጃጀት እና አቀራረብ መገምገም ላይ ብቻ ያተኮረ ነው፡፡ሌሎች የቋንቋ ክሂሎችንም ሆነ የዕውቀት ዘርፎችን በትኩረት አይመለከትም፡፡

## 1.6 የጥናቱ ውሱንነት

ይህን ጥናት ለማጥናት መረጃ ምንጭ እና በመረጃ አሰባሰብ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች ነበሩ፡፡በጥናቱ ዳራ ላይ እንደተገለጸው በመጀመሪያ መጽሀፉ እንዲማሩ ለተዘጋጀላቸው ተማሪዎች እና እንዲያስተምሩ ለሚፈለጉ መምህራን ወይም ለ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሙሉ ለሙሉ ተዳርሶ ገና በስራ ላይ ያልዋለ በሙከራ ደረጃ ያለ በመሆኑ የመረጃ ምንጮችን እንደልብ ማግኘት አስቸጋሪ ሆኖ ነበር፡፡ ሆኖም ግን የሚጠናውን መጽሀፍ በመጠቀም  እና ለሙከራ የተሰጠበትን ትምህርት ቤት አፈላልጎ በማግኘት መረጃዎችን ለማግኘት ሙከራ ተደርጓል፡፡ነገርግን ለበለጠ መረጃ የመጽሀፉን አዘጋጆች ማግኘት ስላልተቻለ ከእነርሱ መቅረብ የሚገባው ነገር የቀረ ይመስላል፡፡ሆኖም ጥናቱ ገና ጅምር በመሆኑ የጽህፈት ክሂልን አደረጃጀትና አቀራረብን በሙከራ ላይ ላለ መጽሀፍ በተገኘው የመረጃ ምንጭ ለመገምገም ተችሏል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1. የመርሀ ትምህርት ምንነት

መርሀ ትምህርት የመጽሀፍ ዝግጅትን፣ የቋንቋና የመማር ባሕሪያትን የሚመለከቱ ይዘቶች የሚቀርቡበት የመማር ማስተማር ግቦችን በማቅረብ እንደ መመሪያ የሚያገለግል መሆኑን እና በመማር ማስተማር ሂደት በየክፍል ደረጃው የሚቀርብ ዝግጅት ሆኖ በየትምህርት አይነቱ የተቀነባበሩ ይዘቶችን፣ የማስተማሪያ ዘደዎችን፣ የመገምምገሚያ ስልቶችን የሚያመላክት መመሪያና ለትምህርት ሥራ የተዘጋጀ መተግበሪያ መሣሪያ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተማሪው ከራሱ የህይወት ልምድና እውቀት በመነሳት የባህሪ ለውጥ ለማምጣት በተወሰነ አካባቢ፣ ቦታና ጊዜ የሚተገበር የትምህርት እቅድ ነው( Yalden 1987)፡፡

ከላይኛው አባባል የምንረዳው መርሀ ትምህርት የትምህርት ሥርዓትን መነሻ አድርጎ የሚዘጋጅና ተማሪው በምን ዓይነት ሂደት ምን ተምሮ ምን ማወቅ እንዳለበት መምህሩም እዴት ማስተማር እንደሚገባው የሚጠቁም መሰረታዊ የትምህርት ሥራ አካል እንደሆነ ያብራራሉ፡፡

### 2.1.1. የመርሀ ትምህርት ዓላማ

አንድ መርሀ ትምህርት ሲዘጋጅ ተማሪዎች እንዲያውቁ ወይም እንዲሆኑ የሚፈለገውን ጉዳይ በዓላማው መታየት አለበት፡፡ ዓላማ ሲነደፍ ሊታይ እና ሊተገበር የሚችል በሚታወቅ በግልጽ ቋንቋ ሊገለጽ ይገባል፡፡

በተመሳሳይ Lawrence (2011)ተማሪዎች ከታቀደው ከመማር ማስተማር ክንውን በኋላ የሚያገኙት ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ በዓላማነት ይካተታሉ፡፡ በተጨማሪም ትምህርቱ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈጥረው አዎንታዊ ለውጥ ምን ሊሆን እንደሚችል ይታቀዳል፡፡" በማለት ገልጸዋል፡፡

መርሀ ትምህርት በሚዘጋጅበት ጊዜ ግልጽና የማያሻማ ዓላማ ሊኖረው እንደሚገባ ገልጸው ዓላማውም በሰነዱ መጀመሪያ ላይ የተቀመጠ፣በዓላማው መሠረትም ይዘቶች ደረጃ በደረጃ ተለይተው መቀመጥ እንዳለባቸው በማስረዳት የመርሀ ትምህርት ዓላማዎች የትምህርቱን ይዘት ለመምረጥ፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎችን ለመዘጋጀት፣አግባብ ያለውን የትምህርት ዘርፍ በተገቢው መንገድ

ትኩረት ለመስጠት፣ የትምህርት ይዘቶችን በተፈለገው ጊዜና ቦታ በአስፈላጊው ሁኔታ በቅደም ተከተል ለማቀናበርና ለማደራጀት፣የትምህርት ሥርዓቱን በወጉና በአግባቡ ለመከታተልና ለመተግበር የሚያስችሉ በርካታ ጠቀሜታ የሚያበረክቱ ናቸው (Ur 1991) ፡፡

## 2.1.2.የመርሀ ትምህርት ባህሪያት

ጥሩ መርሀ ትምህርት የሚያካትታቸውን ሰባት ባህሪያት እንደሆኑ Breen(1984) እንደሚከተለው ይዘረዝሩታል፣ አብዛኛውን ጊዜ በመግቢያ ላይ ግልጽ ዓላማዎችን የሚያሳዩ፣ ይዘቶችን ለምሳሌ ቃላትን፣ሀረጋት እና አረፍተ ነገሮችን አጠቃላይ በሆነ ሁኔታ የሚገለጽ ተፈላጊ የሆነውን የቋንቋ ትምህርት የሚያሳይ፣ማንኛውንም የማህበረሰብ ክፍል፣በአንድነት የሚያስተናግድ፣የቋንቋ ትምህርት በቅደም ተከተል የሚዘጋጅበትን ዘዴ ፣ከቋንቋው ይዘት ጋር ሊሰሩ የሚችሉትን የትምህርት ግብዓቶችን የያዘና በመማር ማስተማሩ ክንውን የቋንቋ ትምህርት የሚተላለፍበትን ስልት የሚጠቁሙ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ እንደBreen (1984) አገላለጽ አንድ መርሀ ትምህርት በመማር ማስተማሩ ሂደት የትምህርት ይዘትን ግልጽ በሆነ መንገድ ማቅረብ፣ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት የሚሄዱበትን ምክንያት ለምን እንደሆነ እና ምን እንደሚማሩ እንዲያውቁ ማድረግ፣የትምህ ርት መርጃ መሳሪያዎችን ማዘጋጀት፣ትምህርቱን በውል እንዴት መተግበር እንደሚገባ ሁኔታዎችን ማመቻቸት እና የጊዜ ሁኔታንና አጠቃቀምን መቼ፣ ለምንና በምን እንደምንገለገል በማሳየት ከትምህርቱ ሥራ ጋር ማቀናጀት ባህሪያቶቹ ናቸው፡፡

## 2.2. የመርሀ ትምህርት እና የመማሪያ መጽሀፍ ግንኙነት

የቋንቋ መማሪያ መፅሀፍን ከሌሎች መፅሀፍ ለየት የሚያደርገው፡- የቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ ዓላማዎችን(አራቱን ክሂሎችን፣ሰዋስውን እና ሥነ-ጽሁፍን) የሚካተቱትን ዝርዝር ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ መርሀ ትምህርትን መሠረት በማድረግ የሚዘጋጅ መሆኑ ነው፡፡ይህን በተመለከተ Sheldon (1988:1) የመማሪያ መፅሐፍ አንዱና ዋናኛ የትምህርት መሳሪያ ነዉ፣ምክንያቱም በመርሃ ትምህርቱ ነጥብ በነጥብ ካልሆነ በስተቀር ሙሉ በሙሉ በግልፅና በዝርዝር ያልሰፈሩ በተማሪዉ መማሪያ መጽሐፍ የሚቀርብ በመሆኑ ነዉ፡፡ ተቀዳሚ ዓላማዉም የተማሪዉን የቋንቋ ተግባቦታዊ ብቃት ለማዳበር ይረዳ ዘንድ ለማስተማሪያነት የሚዘጋጅ መሳሪያ ነዉ በማለት ገልጸዋል፡፡ ከSheldon (1988) የምንረዳው የመማሪያ መጽሀፍ የታለሚዉን ተማሪ የእዉቀት አድማስ (ግንዛቤ) ከማሳደግ አልፎ መምህሩንና ተማሪዉን የሚያስተሳስር መሳሪያ የተማሪዉ

መማሪያ መጽሐፍ ነዉ። አንድ መምህር ሲያስተምርም በመማሪያ መፅሐፉ ያሉ ጭብጦችን እንደሚተገብር ይታመናል።

የቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ዝግጅት የቋንቋ መርሀ ትምህርትን ተመርኩዞ የቋንቋ ትምህርት አላማዎችን ከግብ ለማድረስ የተማሪውን እድሜ፣ ችሎታ፣ ደረጃ፣ ፍላጎት ወዘተ ያገናዘበ ወይም እንደሌሎች መማሪያ መፅሀፍት አስቀድሞ የተገለፀውን አላማ ከግብ ለማድረስ የሚዘጋጅ የመምህሩና የተማሪው አጋዥ መሳሪያ መሆኑን ነው።

## 2.3.የቋንቋ መማሪያ መፅሃፍ ምንነት

የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት የቋንቋ ትምህርት ዓላማን መሰረት በማድረግ በስርዓት የተደራጁ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶችን በውስጣቸው ያካተቱ ሠነዶች ናቸው።ተስፋዬ (1981:43) "የቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት የተደራጁ እና የተውጣጡ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶችን ከተማሪውአካባቢያዊ እና ዳራዊ ዕውቀት አንፃር አካቶ በመያዝ የተቀረፁ የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎችን ከግብ ለማድረስ የተዘጋጁ ሰነዶች እንደሆኑ ያብራራሉ።"የተለያዩ ምሁራን የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ምንነት በተለያየ መንገድ ሲገልፁ የሚታይ ቢሆንም በብያኔያቸው የሚያነሷቸው ነጥቦች ተመሳሳይነት አላቸው።

ለአብነት Grant (1987:5) "የመማሪያ መጻሕፍት የተማሪውን የትምህርት ደረጃ፣ ዕድሜ፣ ፍላጎት፣ የትምህርት ዓላማዎችን የያዘ፣ ለአላማዎቹ ግብ መምቻ የሚሆኑ ማስፈፀሚያ የሚሆኑ ተመጣጣኝ፣ ተለጣጣቂና ተደጋጋፊ ይዘቶችን የያዘ ለመማር ማስተማር ሂደት አገልግሎት ላይ የሚውል የትምህርት ግብዓት ነው"በማለት ይገልጻሉ።

በአጠቃላይ በተለያዩ ምሁራን ሥራዎች የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ምንነትን በሚመለከት የተሰጡ መግለጫዎች የቋንቋ ትምህርት ዓላማን መሠረት ያደረጉ፣ በሥርዓተ ትምህርቱና በመርሃ ትምህርቱ ዝግጅት ላይ የተመሠረቱ የግብ መምቻ ሰነዶች ናቸው። ተመጣጣኝ፣ ተደጋጋፊ፣ ተለጣጣቂ እና ውህደት ያላቸው በተፈለጉ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ላይ በመመስረት አደረጃጀታቸው አራቱን ክህሎቶችና ሁለቱን የዕውቀት ዘርፎችን (የሥነ-ልሣን እና የሥነ-ጽሑፍ) እውቀትን ለማስተላለፍ የሚያስችሉ መልመጃዎችን ያካተቱ መሆናቸውንም እንገነዘባለን።

### 2.3.1. የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ዓላማ

ዓላማ አንድ ተግባር ከተተገበረ በኋላ ይሆናል ተብሎ የተገመተው ውጤት ሲሆን ከቋንቋ አኳያ ትምህርቱ ከተከናወነ በኋላ ተማሪዎች ላይ ይታያል ተብሎ የሚጠበቀውን ችሎታ እና ዕውቀት

ያስገነዝበናል፡፡ይህ ማለት ዓላማ የቋንቋውን ትመህርት መነሻና መድረሻ የሚያሳይ መንደርደሪያ እና ማረፊያ እንደሆነ በምሁራን ተገልጽዋል፡፡

በመሆኑም በመማር ማስትማር ሂደት ያለዓላማ ማስተማር እንደማይቻል ተስፋዬ (1981) ሲገልጹ፡-

- የትምህርት ይዘት በዝርዝር ሊነደፍ አይችልም፣
- የማስተማር ዘዴን ለማዳበር ወይም ለማዘጋጀት አይቻልም፣
- ተገቢ ፈተና ለመፈተን አይቻልም፣የማስተማሪያ መሳሪያዎቹ ምንምን መያዝ እንዳለባቸው ለመወሰን አይቻልም፣
- የማስተማሪያ መሳሪያዎቹ ምን እንደሚያስገኙ በውል አይታወቅም፡፡

## 2.3.2. የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ይዘት

የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍት ይዘት ማካተት የሚገባቸውን ጉዳዮች ምሁራን ጥቆማ ይሰጣሉ፡፡በመሆኑም በመማሪያ መጽሀፎች ውስጥ በቋንቋ ትምህርትነት መገኘት የሚገባቸውን የትምህርት ልምዶች ወይም ይዘቶች ከመመረጣቸው በፊት አጽንኦት ሊሰጣቸው የሚገባቸው ጉዳዮች እንዳሉ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ yalden (1987)እንደሚከተለው ይገልጻሉ፣የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ሲመረጡ ዐብይ ጉዳዮች ናቸው ያሉዋቸውየተማሪው ፍላጎት፣የተማሪው ዕድሜ፣የዕውቀት ደረጃ እና በጥቅሉ የተማሪው ዳራ ሊጠና ይገባል በማለት ዘርዝረዋል፡፡ይዘቱ በሚመረጥበት ጊዜ በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የተዘጋጁትን አጠቃላይ እና ዝርዝር ዓላማዎችን ያገናዘበ መሆን እንዳለበትም አክለው ገልጸዋል፡፡ ከዚህ ገለጻ የምንረዳው የቋንቋ ትምህርት መማሪያ መጽሀፍ ይዘት ሲዘጋጅ የተማሪውን ዳራ ያገናዘበ እና መርሀ ትምህቱን መሰረት ያደረገ ከሆነ በመጽሀፉ ውስጥ የሚዘጋጀው ይዘት የቋንቋ ትምህርትን ዓላማ ግብ እንደሚመታ ነው፡፡

## 2.4.የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ አደረጃጀት

የቋንቋ ትምህርት ይዘት በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ አንድ ተማሪ ተምሮ ሲያበቃ ያመጣል ተብሎ የሚጠበቅ በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የሚገኝ ቁም ነገር ነው፡፡Nunan (1988) ይዘትን ተማሪው እንዲማረው የተፈለገው የቋንቋ እውቀት፣ክህሎት እና አመለካከት የሚያመለክት ስለ ቋንቋ መማር ሂደት በንድፈ ሀሳባዊ አመለካከት ላይ እንደሚከናወን ይገልጻሉ፡፡

በተጨማሪ የትምህርት ዓላማዎች እና ይዘቶች ከተመረጡ በኋላ ቀጥሎ የሚመጣው ጉዳይ የትምህርት ይዘቶቹ እንዴት ተደራጅተው ይቅረቡ የሚል ይሆናል፡፡በመሆኑም ዓላማውን ከግብ ለማድረስ በተመረጡ ይዘቶች የታሰበውን የባህሪ ለውጥ ለማየት ይዘቶቹ በጥሩ ሁኔታ ሊዋቀሩ ይገባል፡፡ በመሆኑም ለትምህርት ይዘቶች በተሸለ ስልት መደራጀት ሶስት ጉዳዮችን እንደሚያስከትል እናተከታታይነት፣ተለጣጣቂነት እና ውህደትን ማሟላት እንደሚገባቸው ገልጸዋል(Tyler 1950)፡፡

ከዚሁ ጋር በተመሳሳይ ተስፋዬ (1981) አንድ የቋንቋ ትምህርት ይዘት በጥሩ ሁኔታ ለማደራጀት ሶስት ዓይነት የአደረጃጀት መስፈርቶች እንዳሉ ከላይኛው ጋር ሶስት ተመሳሳይ ሀሳቦችን ዘርዝረዋል፡፡እነርሱም በአጭሩ እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡-

**ሀ.ተለጣጣቂነት፡-** በአንድ መፅሀፍ ልዩ ልዩ ምዕራፎች መካከልም ሆነ ለተለያዩ ክፍሎች በተዘጋጁ መፅሀፍት መካከል ተለጣጣቂነት የቅደም ተከተል ጉዳይ ነው፡፡ተማሪው ቀጥሎ የሚደርሰበት ምዕራፍ ካለፈው የተለየና ያደገ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ያለፈውን የሚደግም ከሆነ ግን እድገት ወይም አዲስነት አይኖረውም፡፡

**ለ.ተከታታይነት፡-** በአንድ የትምህርት ዓይነት እያደገ ግን በተደጋጋሚ የሚመጣ ነው ፡፡ለምሳሌ ጽህፈትን ከአንደኛ ክፍል እስከ አስራሁለተኛ ክፍል እናስተምራለን፡፡ይህ ጽህፈትን የማስተማር ጉዳይ እየተደጋገመ የሚመጣ ነው፡፡

**መ.ውህደት፡-** በሥርዓተ ትምህርት ያሉትን የትምህርት ልምዶች መሰረታዊ ግንኙነት የሚመለከት ነው፡፡የተዋሀዱ የትምህርት ልምዶች ቅንብር የትምህርት ልምዳችን የእርስ በርስ መደጋገፍ፣የትምህርት ልምዶች አንዱ ሌላውን የማዳበር እና የማበልጸግ ጉዳይ ነው፡፡

**ሠ.ተግባራዊነት፡-** በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህሩን እና ተማሪውን አሳታፊ ሊሆን ይገባል፡፡ይህ ማለት የማስተማሪያ የትምህርት ይዘት ለተማሪው በተግባር የሚገለጽ መሆን አለበት፡፡

ፈ.ተገቢነት፡- የተዘጋጀው የማስተማሪያ መሣሪያው በይዘቱ ለተማሪዎች ደረጃ፣ ለተማሪዎች ዕድሜ፣ ለተማሪዎች ችሎታና ለተማሪዎቸ ፍላጎት የሚመጥን መሆን እንዳለበት የሚያመለክት ነው።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ነጥቦች መማሪያ መፅሀፍት ውስጥ አፅንኦት ተሰጥቶዋቸው ሊዘጋጁ የሚገባቸው ነገሮች ናቸው።

## 2.4.1.የመጻፍ ክሂል ምንነት

የመጻፍን ምንነት በማስመልከት የተለያዩ ምሁራን ብያኔዎችን ሰጥተዋል፤የብያኔዎች አገላለጽ የተለያዩ ቢመስሉም ተመሳሳይነታቸው ይጎላል።

Nunan(1999:273)መጻፍን እንደሚከተለው ገልጸውታል፡-“መጻፍ ለተወሰነ የልምምድ ጊዜ የሚቆይ የማሰላሰልን ብቃት የሚጠይቅ አእምሯዊ ሂደት ነው፤ካሉ በኋላ አንባቢው ሊረዳው በሚችል ሁኔታ ለድምጾች ውክልና በተሰጣቸው ትእምርቶች አማካይነት ሀሳብን ማሳወቅ መቻል ነው።”

በቋንቋ ተግባቦት ሂደት ከአራቱ ክሂሎች አንዱ መጻፍ ሲሆን ለሀሳብ ወይም ለመልዕክት መቀባቢያነት የሚያገለግል ነው።በመሆኑም መጻፍ የድምጽ ወኪል በሆኑ ትዕምርቶችና ምልክቶች አማካኝነት የሚተገበር የመልዕክት ማስተላለፊያ ነው።የመጻፍ ክሂል ዕውቀት የሚቀሰምበትና የሚተላለፍበት እና አንድ የተጻፈ መልዕክት ከዘመን ወደዘመን እንዲሸጋገር መተላለፊያ በመሆን ያገለግላል (Tangerpermpoon 2009)።ከላይኛው ከሁለቱም ገለጻ የምንረዳው መጻፍ ሀሳብን ከብዕር ጋር በማገናኘት ለአንባቢ መልዕክትን የማስተላለፊያ መንገድ ሲሆን የሚጻፈው ነገረ (ሀሳብ) ከሰዎች ሂሊና የሚመነጭ ታስቦበት የሚሰራ ነገር እንደሆነ ነው።

## 2.4.2. የጽህፈት ትምህርት ዓላማ

የጽህፈት ትምህርት አላማ ተማሪዎች ያሰቡትን ነገር ወይም በሂሊናቸው ያላቸውን አመለካከት በጽሁፍ በመግለጽ ጽሁፋዊ ተግባቦትን እንዲለማመዱ የማድረግ ተግባር መሆኑን ምሁራን ይገልጻሉ።ተማሪዎች ጽህፈትን የሚማሩባቸው ዓላማዎች ለአንባቢ ሀሳብን ለማስተላለፍ፣በንባብ የሚተላለፈው መልዕክት ሃሳብን በጽሁፍ ለመግለጽ፣ዕውቀትን ለማግኘት፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚከሰቱ ክስተቶችን መዝግቦ ለማስተላለፍ በቋንቋው መጻፍን መተግበር ነው በማለት ገልጸዋል። (Raimes 1983፡4-7)

በተጨማሪ Heaton (1991፡138) ጽህፈትን መማር የተለያዩ የጽህፈትን ንዑሳን ክሂሎችን፣ ዓረፍተ ነገሮችን በመጻፍ መጠቀምን ይመለከታል፡፡ ተፈላጊውን ሀሳብ ለማስተላለፍ ተገቢ የአጻጻፍ ስልቶችን የመምረጥ፣የዓረፍተ ነገር እና የአንቀጽ አወቃቀር ሥርዓትን ጠብቆ የመጻፍ፣የተለመደ እና መደበኛ ቋንቋን መተግበር እና መጠቀም ነው ይላሉ፡፡ባጭሩ የጽህፈት ትምህርት ዓላማዎች የተማሪዎችን የቃላት እና የዓረፍተነገርን አቀነጃጀት በመለማመድ በጽሁፍ አማካይነት ተግባቦትን በመፍጠር የጽህፈት ንዑሳን ክሂሎችን ማለማመድ ናቸው በማለት ገልጸዋል፡፡

## 2.4.3.የመጻፍ ክሂል የይዘት መምረጫ መስፈርት

የቋንቋ ትምህርት ይዘት አደረጃጀት ላይ ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገባቸው ጉዳዮችን፣ መምረጫ መስፈርቱን፣ መርሆዎቹን እና ባህሪያቱን በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር ምሁራን የተባለውን ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡ከዚህ አንጻር የጽህፈት ክሂልም ይዘቶች ምርጫ እነኚህኑ ቀደም ሲል የተገለጹትን መሠረት አድርጎ የሚዘጋጅ በመሆኑ የተወሰኑትን ለጽህፈት ክሂል ብቻ ከዚህ በታች እንደሚከተለው እናያለን፡፡

ስለመጽሀፍት አዘገጃጀት ጥናት ያካሄዱ ምሁራን የጋራ የሚያደርጉት የይዘት መምረጫ መስፈርቶች አሉ፡፡ እነርሱም፡-ተገቢነት፣አስፈላጊነት፣ዘላቂነት፣አስደሳችነት እና ለመማር ያላቸው ምቹነት ናቸው (Tyler 1949 )፡፡

እነዚህን ከላይ በጥቅል የተቀመጡትን ይዘት መምረጫ መስፈርቶችን ከጽህፈት ክሂል አንጻር እንደሚከተለው እንዘረዝራለን፡-

***ሀ.ተገቢነት፡-***የታቀደውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የዕውቀትና የባህሪ ለውጥ በተማሪው ላይ ለማምጣት በተግባር ሊያውለው የሚችለውን መለማመጃ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡የፊደላትን ወይም የሆሄያትን ቅርጽ ለይቶ ላላወቀ ተማሪ ዓረፍተነገር ወይም አንቀጽ እንዲጽፍ ማቅረብ ተገቢነት የሌለው የጽህፈት መለማመጃ ይዘት ነው፡፡ስለዚህ ተማሪው ጽህፈትን እንዲያጎለብት የሚመረጡለት ይዘቶች ከችሎታው እና ከጽህፈት ዓላማ ጋር የተዛመደ እና ተገቢነት ያለው መሆን አለበት፡፡

**ለ.ዘላቂነት፡-**ተማሪው የጽህፈት ክሂል ይዘቶቹን በክፍል ብቻ ሳይሆን ከመማሪያ ክፍል ውጪም ሊለማመድባቸው የሚያስችሉ መሆን አለባቸው፡፡ ይዘቶቹ በመማሪያ ክፍልእና ከመማሪያ ክፍል ውጪ ለረዢም ጊዜ ለማገልገል መቻላቸው ዘላቂነትን ያሳያል፡፡ ለምሳሌ በጽህፈት ትምህርት

አስተወጥኦ መንደፍን ወይም የድርሰት ዓይነቶችን በተለያየ ክፍል ላይ በተከታታይ መማር ዘላቂነትን ያመለክታል፡፡

**መ.አስደሳችነት**፡-ለተማሪው በአካባቢው በሚያውቀው ነገር ላይ መሠረት የሆነ እና ከዕድሜው እና ከህይወቱ ጋር ተያያዥነት ያለው የጽህፈት መለማመጃ ይዘት ሊያስደስቱት ይችላሉ፡፡በጽህፈት ክሂል የደብዳቤ አጻጻፍን እንዲለማመዱ ለዘመዶቻቸው እንዲጽፉ ከማድረግ ይልቅ የሴት ጓደኛ ከወንድ ጓደኛ ጋር እንዲጻጻፉ ቢደረግ የበለጠ ተነሳሽነት ኖሯቸው ደስተኛ ይሆናሉ፤ተማሪው ሊጺፍ የሚችላቸው የህይወት ገጠመኞች ያስደስቱታል በመሆኑም የተማሪውን ዕድሜ፣ዳራ እና ገጠመኙን ያገናዘቡ የመለማመጃ ርዕሶች(ይዘቶች)ስለሚያስደስቱት ስሜቱን የሚነካ (የሚስቡ) መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል (Cunningsworth 1995)፡፡

**ሠ.ለመማር ያላቸው አመቺነት፡-**በመማር ማስተማር ሂደት ይዘት መረጣ ሲደረግ የመጀመሪያዎቹን ይዘቶች ወይም የትምህርት ልምዶች መሠረት ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡በዚህ ሁኔታ የተመረጡ የትምህርት ልምዶች የተማሪውን የመማር ሂደት ትርጉም ያለው ያደርጉታል፡፡በጽህፈት ትምህርት ሂደት መለማመጃው ከቀላሉ ወደ ከባዱ ወይም ከትንሹ ወደትልቁ ካልሆነም ከጠባቡ ወደሰፊው የሚያለማመድ መሆን አለበት፡፡ለምሳሌ ከቃል ወደ ሀረግ ፣ከሀረግ ወደ ዓረፍተነገር፣ከዓረፍተ ነገር ወደ አንቀጽ እያለ ሲሄድ ለተማሪው ለመማር አመቺነት እና ተደጋጋፊነት አላቸው፡፡

### 2.4.4. የመጻፍ ክሂል ይዘቶች አደረጃጀት

የጽህፈት ክሂል ይዘቶች የቋንቋውን ሥርዓት እና አጠቃቀም እርስ በርስ አንዱ ለሌለው ድጋፍ በመሆን ይደራጃሉ፡፡በዚህ መሠረት እያንዳንዱ ይዘት የመጀመሪያውን መሠረት በማድረግ ይደራጃል፡፡የትምህርት ልምዶችን (ይዘቶችን) ለማደራጀት ከተማሪዎች የማወቅ ባህርይ አንጻር ተጠየቃዊ በሆነ ቅደም ተከተል በደረጃ ማስቀመጥ ነው(Taba 1962)፡፡

ከላይ እንደተገለጸው የአንድ ቋንቋ ይዘት ቋንቋው ለአገልግሎት የሚውልበት መንገድ ብቻ ሳይሆን ለመጠቀምም ሥርዓት(ህግ) አስፈላጊ በመሆኑ ሁለቱም አንድ ላይ ማለትም አጠቃቀምና ሥርዓት አንድ ላይ መደራጀት እንዳለባቸው ነው፡፡

**ሀ.ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ፡-**የጽህፈት ክሂል ትምህርት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት ስልት በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡትን የጽህፈት ክሂል ይዘቶችን ተማሪዎች በምሳሌዎች

እየታገዙ መልመጃዎችን ከተለማመዱ በኋላ የጽህፈት ሥርዓትን በራሳቸው ጥረት እንዲተገብሩት የሚያደርግ የይዘት አደረጃጀት ነው፡፡

**ለ.ከአጠቃላይ ወደዝርዝር አቀራረብ፡-**በዚህ የአቀራረብ ዘዴ በቅድሚያ የሚቀርበውን የጽህፈት ክሂል ይዘትን በሚመለከት የቋንቋው ህግ የሚፈቅደውን አቀራረብ መሠረት በማድረግ ተማሪዎች የጽህፈት ክሂል ሥርዓትን መነሻ በማድረግ የተዘጋጁትን መልመጃዎች እንዲሰሩ የሚያደርግ አቀራረብ ነው፡፡ይህን በተመለከተ Cunningsworth (1995፡99) ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሚቀርቡ የጽህፈት ይዘቶች "ገለጻዎችን ደንቦች እና ሞዴሎች በግልፅ ተብራርተው ከቀረቡላቸው በኋላ የክሂሉን መልመጃዎች እየሰሩ የሚለማመዱበት ሂደት ነው በማለት ገልጸዋል፡፡"ይህ ገለጻ ጽህፈትን በመማር ማስተማር ሂደት ከመምህሩ ይልቅ ተማሪውን እንደሚያሰራ እና ጥቅል (ሰፊ)የሆነው ይዘት መተንተን እንዳለበት የሚገልጽ ነው፡፡

## 2.5 . የመጻፍ ክሂል አቀራረብ

ጽሁፍ ለመጻፍ ተማሪዎች የሚያከናውኗቸው የተለያዩ የአቀራረብ ደረጃዎች እንዳሉ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ለአብነት Richards (1990፡108) የጽህፈት ኪሂል አቀራረቦችን ውጤት ተኮር እና ሂደታዊ አቀራረብ በማለት በሁለት የከፍሏቸዋል፡፡

### 2.5.1. ውጤት ተኮር አቀራረብ

ውጤት ተኮር አቀራረብ ትኩረቱ በጽህፈት ሂደት ላይ ሳይሆን በውጤት ላይ ነው፡፡ተማሪዎቹ የመጻፍ ችሎታቸውን ሲጨምሩ የጽህፈት ተግባራትን የማከናወናቸው ሂደት እየጨመረ ይሄዳል፡፡ለዚህ ደግሞ ልዩ ልዩ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ፡፡በውጤት ተኮር አቀራረብ ተማሪዎች የአንቀጽ እና የዓረፍተነገር አቀነባበርን ያበለጽጋሉ በማለት ገልጸዋል (Richards 1990)፡፡

በውጤት ተኮር አቀራረብ ተማሪዎች ሶስት ደረጃዎችን ማለፍ እንዳለባቸው Pincas (1982) እንደሚከተለው ገልጸዋል፤ እነርሱም፡-

**ሀ.የትውውቅ ጊዜ**፡- ለተማሪዎች መምህራን ሞዴል ጽሁፍ አቅርበውላቸው ይህንን ሞዴል እያዩ ወይም በመረዳት በተነሳሽነት እንዲሰሩ ወይም እንዲጽፉ የሚደረግበት ነው፡፡ይህን ክንውን በመደገፍ Pincas (1982, 14) "መምህራን ለተማሪዎቻቸ መርጠው የሚያሳዩዋቸው ሞዴል ጽሁፎች ከክፍል ደረጃቸው፣ ከዕድሜያቸው፣ከፆታቸውና ከባህላቸው አንፃር ሆኖ ለተግባራዊነቱ የሚያነሳሳቸው መሆን አለበት" በማለት ገልጸዋል፡፡

እንደPincas(1982) አገላለጽ በውጤታዊ የአፃፃፍ ተማሪዎች እንዲጽፉ የሚፈለገውን ነገር በቅድሚያ በሞዴል ደረጃ በመመልከት እና አንብበውን በመረዳት ፍላጎታቸውን በማነሳሳት ከሞዴሉ አንፃር መስራት ወይም መፃፍ እንዳለባቸው ነው፡፡

**ለ.የልምምድ ጊዜ፡-**ተማሪዎች የተመለከቱትንና ያነበቡትን ሞዴሎች መሠረት በማድረግ በራሳቸው ፍላጎት ሃሳባቸውን በማፍለቅ የሚለማመዱበት የመጻፍ ክንውን ነው፡፡ይህን ተግባር Pincas (1982,14)"በልምምድ ጊዜ ተማሪዎች የተወሰነ ጽህፈትን በመጻፍ እና በመለማመድ ወደመሪ የጽህፈት ተግባር የሚተላለፉበት ወቅት ነው "በማለት ገልጸዋል፡፡ከPincas(1982) ገለጻ የምንገነዘበው ነገር ቢኖር ተማሪዎች ጽህፈትን ከሞዴሎች አንፃር በመለማመድ ሃሳባቸውን በራሳቸው ጊዜ እና ፍላጎት በመጻፍ ወደመሪ የጽህፈት ክንውን መሸጋገር እንደሚችሉ ነው፡፡

**መ.የውጤት ጊዜ፡-**በዚህ ወቅት ተማሪዎች በሀ እና በለ የተጠቀሱትን የመጻፍ ክንውን ወቅትን በራሳቸው በማለፍ ያለማንም ረዳትነት እንደየፍላጎታቸው በነፃነት ይጽፋሉ፡፡እዚህጋ የመምህሩ ተግባር አነስተኛ በመሆኑ ተማሪዎች በተነሳሽነት እና በራስ መተማመን ይተገብራሉ፡፡ከዚህ የተነሳ የቃላት አመራረጡ፣የአንቀጽ አደረጃጀቱ እና የሰዋስው ስርዓቱ በመጨሻ የሚታዩ ፍሬ ነገሮች እንደሆኑ ነው ( Richards 1990)፡፡

## 2.5.2.ሂደታዊ አቀራረብ

ይህ ሂደት ጽህፈትን በመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች ሲጽፉ በውጤቱ ላይ ሳይሆን ውጤቱን ለመድረስ በሚያከናውኑት ተግባር ላይ ነው፡፡በዚህ ሂደት ከትክክለኛነት ይልቅ ለጽሁፉ አካሄድ ትኩረት ይደረጋል፡፡በሂደቱ ለተማሪዎች የሚጽፉትን ነገር ወይም ርዕስ መምህሩ ሳይሆን የሚመርጥላቸው በተሰማቸውና በፈለጉት ጉዳይ ለመጻፍ እራሳቸው ናቸው፡፡ይህን በተመለከተ Raimes (1983) "አንድ ጸሀፊ ከመጻፉ በፊት የሚያስበው ስለሚጽፈው ጉዳይ ዓላማ እና ስለተደራሲያን ሳይሆን የሚጽፈውን ነገር ሀሳብ እንዴት ጀምሮ እና አቀናጅቶ መጻፍ እንዳለበት መሆኑን ይገልጻሉ፡፡"

ስለዚህ የላይኛው ገለጻ የሚነግረን ተማሪዎች አንድን ጽሁፍ ለመጻፍ ከቃል ጀምሮ እስከ ዓረፍተነገር አወቃቀርና አንቀጽ አደረጃጀት ድረስ ሀሳባቸውን በራሳቸው ፍላጎት እና ተነሳሽነት በመረጡት ርዕስ ላይ መጻፍ እንደሚችሉ ነው፡፡

Richards, (1990) ሂደታዊ ጽህፈት የተለያዩ የክንውን ደረጃዎች አሉት፡፡እነርሱም ቅድመ-ጽህፈት፣የጽህፍ ጊዜ እና ድህረ ጽህፈት ተግባራት ናቸው በማለት ጠቅሰዋል፡፡" ዝርዝሩን ቀጥሎ እናያለን፡-

**ሀ.ቅድመ ጽህፈት፡-**ቅድመ ጽህፈት ከሚያካትታቸውን ነገሮች Richards (1990፡109) እንደሚከተለው ዘርዝሯል፡-የሚጽፉበትን ርዕስ መምረጥ፣ስለርዕስ ማሰብ፣ አንባቢያንን መገንዘብ እና ለምን ዓላማ እና ጉዳይ እንደሚጽፉ ሊረዱ ይገባል በማለት ገልጿል፡፡

የRichards (1990) የሚያስረዳን ተማሪዎች የሚጽፉትን መረጃ ለመሰብሰብ አንባቢውን ለማሰብ፣ ዓላማውን ለመወሰን እና የመጀመሪያ ንድፍን ለማቀድ የሚሰሩትን ክንውን ያካትታል፡፡ የቅድመ ጽህፈት ተግባር ላይ ለመጻፍ የሚያስችሉ አስተሰቦችን የሚያሰባስቡበት ሂደት ነው፡፡ ጽሁፍ ከመጻፉ በፊት በርዕስ ጉዳዩ ላይ በቅድሚያ ይታሰባል፣ የርዕሱ ስፋትና ጥልቀት መታወቅ አለበት፤ ከርዕሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው አመለካከቶች ወይም አስተሳሰቦች ግልጽ መሆን እንዳለባቸው ነው፡፡

**ለ.የጽህፈት ጊዜ፡-**የጽህፈት ጊዜ ሃሳብን በማርቀቅ በወረቀት ላይ ትክክለኛ የጽህፈት ክንውን የሚጀመርበት ሂደት ነው፡፡በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች በቅድመ ጽህፈት ደረጃ የሰበሰባቸውን አመለካከቶች ወይም አስተሳሰቦች የሚጽፉበት ደረጃ ነው፡፡በተጨማሪም ሀሳቦችን በቅደም ተከተል አደራጅተው ጽሁፉን ቅርጽ የሚያስይዙበት ክፍል ነው፡፡ (Richards 1990፡109) ስለዚህ በመማር ማስተማር ሂደት ላይ ተማሪዎች የመጀመሪያውን ረቂቅ ለመጻፍ በሚያውቁት እና በሚፈልጉት ርዕስ ወይም ይዘት ላይ ማነጣጠር አለባቸው፡፡

**መ.ድህረ ጽህፈት፡-**ድህረ ጽህፈት በጽህፈት ጊዜ የተጻፈውን ጽሁፍ እንዴት እንደተጻፈ የሚፈተሽበትና እንዲተላለፍ የተፈለገውን ሀሳብ ለማስተላለፍ የመጨረሻ ማስተካከያ የሚደረግበት ሂደት ነው፡፡ተማሪው የጽሁፉን መልእክት ለተደራሲው ግልጽ መሆኑን የሚረዳበት እና የሚያረጋግጥበት የትግበራ ሂደት ነው (Richards 1990፡109)፡፡

ድህረ ጽህፈት ተማሪዎች በቅድመ እና በጽህፈት ጊዜ ያረቀቁትን እና ያደራጁትን ሀሳብ ከተደራሲ አኳያ የተጻፈው መልዕክት ሊተላለፍ መቻል አለመቻሉን ወይም በአጭሩ አንባቢን እንደሚመጥን እና እንደማይመጥን የሚፈተሽበት ነው (Attkins 1996፡120)፡፡

# ምዕራፍ ሦሥት

# የጥናቱ ዘዴ

በዚህ ምዕራፍ የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች እና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተገልጸዋል፡፡በመሆኑም ግምገማ በማንኛዉም የሥራ መስክ መረጃን መሠረት በማድረግ የሚተገበረዉን ተግባር ብቃቱን እስከ ምን ድረስ እንደሆነ የሚቃኝበት፣ ለታሰበለት ዓላማ ያበረከተዉን አስተዋፅኦ ተመልክተን ጥንካሬና ድክመቶችን ለይተን በመመልከት የምንተነትንበት የስራ ሂደት ነዉ፡፡በመሆኑም የሰነድ (መጽሐፍ)ግምገማ(ፍተሸ) ለማድረግ የሚያስፈልገውን ዘዴ ያለው (2009፡19) እንደሚከተለው ገልጸውታል፡-

> በምርም ሂደት ሁሉም ነገሮች በቁጥር የሚገለጡ ወይም የሚወከሉ አይደሉም፡፡ ተመራማሪው ለማጥናት የፈለገው ጉዳይ በመጠን ሳይሆን በዓይነት የሚገለጽ ይሆናል፡፡ ስለዚህ በዓይነታዊ ምርምር ተመራማሪው የሚያጠናቸው ጉዳዮች ሁሉ በመጠን ይህን ያህል ተዛምዶ ወይም ልይይት (variation)አላቸው ብሎ ያገኛቸውን መረጃዎች በስታስቲካዊ ዘዴ አይገልጻቸውም፡፡መረጃዎቹን ተንትኖ የጥናቱን ውጤት ላንባቢ የሚያቀርበው ትረካዊ ወይም ገለጻዊ መንገድን ተከትሎ ነው፡፡

በመሆኑም የዚህ ጥናት ትኩረት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር የመጀመሪያ እትም 2014 ዓ.ም የሆነው አማርኛን እንደፌዴራል ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀውን የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መጽሐፍ ውስጥ የመፃፍ ክሂልን የይዘት አደረጃጀት መገምገም ላይ ስለሆነ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀም ለግምገማው በሚዘጋጁት መርሆዎች አማካይነት መረጃዎቹ ገላጭ የምርምር ስልትን በመጠቀም ተብራርተዋል፡፡

## 3.1.መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ

### 3.1.1. የሰነድ ግምገማ

በዚህ ጥናት ውስጥ አብይ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሆኖ የሚያገለግለው የሰነድ ግምገማ ነው፡፡የሚገመገመውም ሰነድ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር የመጀመሪያ እትም 2014 ዓ.ም የሆነው አማርኛን እንደፌዴራል ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀውን የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መጽሐፍ ውስጥ የመፃፍ ይዘት ላይ ሲሆን ትኩረቱ የመጻፍ ክሂልን የይዘት አደረጃጀት እና አቀራረብ ላይ አድርጓል፡፡

### 3.1.2. የመምህራን ቃለ-መጠይቅ

ለጥናቱ በተመረጠው ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን በቃለመጠይቅ መረጃ ሰጪነት ተሳትፈዋል፡፡መምህራኑ የተመረጡት መጽሀፉ በመላ ሀገሪቱ ላይ ተሰራጭቶ በሥራ ላይ የዋለ ሳይሆን በየክልሉ አልፎ አልፎ ለሙከራ በተመረጡ ትምህርት ቤቶች እየተተገበረ ያለ በመሆኑ ለዚህም ጥናት በደቡብ ክልል በዱራሜ ከተማ ሂዳሴ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትቤት እያስተማሩ ያሉት ሁለት መምህራን ቃለምልልሱን አድርገዋል፡፡ (**በተጨማሪ አባሪ 2 እና 3 ይመልከቱ**)

## 3.2.የመረጃ መትንተኛ ዘዴ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር የመጀመሪያ እትም 2014 ዓ.ም የሆነው አማርኛን እንደፌዴራል ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀውን የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መጽሐፍ ውስጥ የመፃፍ ክሂልን የይዘት አደረጃጀት መገምገም(መፈተሽ) ሲሆን ሊተነተኑ የሚገቡ በምዕራፍ ሁለት ስለ ጽህፈት ክሂል አደረጃጀት እና አቀራረብ የተጠቀሱትን መርሆች እና ጽንሰ ሀሳቦችን መሰረት በማድረግ ተገምግሟል (ተፈትሿል)፤ በተጨማሪ የጽህፈት ክሂል መልመጃዎች ተዋረዳዊ እና ጎናዊ አደረጃጀቶችን ለጥናቱ መሠረት በተደረገው ዓይነታዊ የምርምር ዘዴ በመፈተሽ የተገኙትን መረጃዎች በዓይነት በዓይነት በመለየት በገላጭ ስልት ተተንትነዋል፤ በመጨረሻም የመምህራኑ ቃለምልልስ (ገለጻ)ተተንትኗል ወይም ማብራሪያ ተሰጥቶበታል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ትንተና የጥናቱ ውጤት

በምዕራፍ አራት ዋናው የጥናቱ ሥራ የሆነው ለ10ኛ ክፍል የተዘጋጀው መጽሀፍ ጽህፈትን ለማስተማር ይዘቶቹ እንዴት እንደተደራጁ እና እንደቀረቡ ገምግሞ(ፈትሾ) መተንተን ነው። በመሆኑም በምዕራፍ አንድ በጥናቱ ዓላማ ላይ የተገለጹ ነገሮች እዚህጋ ምላሽ አግኝተዋል ወይም ግብ መተዋል።

## 4.1.የመረጃ ትንተና

አንድ ጥናት ታላሚ አድርጎ ለያዘው ጉዳይ ውጤት ለማስገኘት ወይም ግብ ለመምታት የሚያከናውነው ተግባር (ተጠየቃዊ ፍተሸ)የመረጃ ትንተና ነው፤የመረጃ ትንተና ለምርምር መሠረታዊ ነገር መሆኑን ወይም ዋና ተግባር እንደሆነ እንረዳለን፤የምርምርን ህግ ተከትሎ ከተሰራበት ደግሞ ከግብ እንደሚያደርስ መገንዘብ ይቻላል (Brown 2001)።

ከላይ የተገለጸው የ(Brown 2001)አባባል አንድን ጥናት ተጨባጭ ለማድረግ ጥናቱ የሚከናወንባቸው መረጃዎች እውነት ሊሆኑ እንደሚገባ ነው።

በመሆኑም በዚህ ክፍል የጥናቱ ዋና አካል የተደረገውን መማሪያ መጽሀፍ በማናበብ እና በመመልከት እንዲሁም ከመምህራን የተገኙ የቃለ-መጠይቅ ምላሾች ለጥናቱ በተዘጋጁት መርሆች አማካይነት ትንተና ተሰጥቶባቸዋል።

### 4.1.1.የመጽሀፉ አጠቃላይ ገጽታ

ለ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበው አዲሱ የአማርኛ ቋንቋ መጽሀፍ አሥር ምዕራፎች አሉት።መጽሀፉ በመጠን ለአያያዝ አመቺ እንዲሆን ተደርጎ የተዘጋጀ ነው።በመጽሀፉ ውስጥ የትምህርት ይዘቶችን ዓላማን ግብ ለመምታት የሚያደርሱ ዐቢይና ንዑሳን የትምህርት ልምዶች ይገኙበታል።በዚህ ፍተሸ (ግምገማ)ተማሪዎች የቀደመ ዕውቀታቸውን ተጠቅመው ሊሰርዋቸው የሚችሉ ከተማሪዎች ችሎታ እና አቅም በላይ ያልሆኑ ይዘቶች ለመሆናቸው በመጽሀፉ ምልከታ ተደርሶበታል።ዝርዝር ሁኔታው ወደፊት ይገለጻል።በመሆኑም የመማሪያ መጽሐፉ የተዘጋጀው አማርኛን እንደፌዴራል ቋንቋ ለሚማሩ ለአሥረኛ ክፍል ተማሪዎች ነው።ከትምህርቱ የሚጠበቁ ዋና ዋና ውጤቶችም፡-

የማዳመጥ ክሂልን ማዳበር፣የንግግር ክሂልን ማዳበር፣የንባብ ክሂልን ማዳበር፣ የጽሕፈት ክሂልን ማጎልበት፣የቃላት ዕውቀትን ማዳበር እና የሰዋስው ዕውቀትን ማበልጸግ ናቸው። መጽሐፉ የተሰናዳው ለደረጃው የተዘጋጀውን መርሐ-ትምህርት መሠረት አድርጎ ነው። ተማሪዎች በደረጃቸው የተለያዩ ባህላዊ፣ ሳይንሳዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ አካባቢያዊ፣ ዓለማቀፋዊ፣ ወዘተ.ይዘቶችን( እሴቶችን) በአማርኛ ቋንቋ እንዲገልጹ ስለሚጠበቅ፣ መጽሐፉ ለይዘቶችም ከክሂሎች ያልተናነሰ ትኩረት ይሰጣል። የዚህም ዋና ዓላማ ተማሪዎች በምንባቦች አማካይነት የንግግርና የማዳመጥ፣ የንባብናየጽሕፈት ክሂሎቻቸውን፤የቃላትና የሰዋስው ዕውቀታቸውን እንዲሁም የሥነጽሑፍ ችሎታቸውን እንዲያጎለብቱ ማገዝ ነው መጽሐፉ ከሕይወት ተሞክሮ ጋር የተዛመደ እንዲሆን ተደርጓል፤ ተማሪዎቹ አዳዲስ ጉዳዮችን ለመማር ግላዊ ገጠመኞቻቸውንና ልምዶቻቸውን እንዲጠቀሙ ይጠበቃል። በዚህም መሠረት ችግር ፈቺና አሳታፊ ተግባራትና መልመጃዎች በየምዕራፎቹ ተካተዋል።ተግባራቱም ተማሪዎቹ ቋንቋውን በተለያየ መንገድ ለተግባቦት እንዲጠቀሙበት የሚያስችሉ ናቸው።

## 4.1.2.የቋንቋ ትምህርትን ዓላማ መሠረት በማድረግ የተዘጋጁ አጠቃላይ የመጽሀፉ ቅኝት

የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች ዋናዋናዎቹ ሁለት ሲሆኑ እነርሱም አራቱ ክሂሎች (ማዳመጥ፣ መናገር፣ማንበብ እና መጽሀፍ)ሲሆኑ ከሁለቱ የዕውቀት ዘርፎች ደግሞ ሰዋስው(ሥነ-ልሳን) ናቸው።ይሁንና በመጽሀፉ ውስጥ የእነዚህን አጠቃላይ አደረጃጀት በአስሩም ምዕራፍ ውስጥ እንዴት እንደተካተቱ መጠናቸውንና ዓይነታቸውን ቀጥሎ በሚገኘው ሠንጠረዥ አንድ እንደሚከተለው እናያለን።

**ሠንጠረዥ አንድ በመጸሀፉ ውስጥ የተካተቱ (የሚገኙ) አጠቃላይ ይዘቶች ቅኝት**

| ምዕራፍ | ርዕስ | በምዕራፉየተካተቱ ይዘቶች | | በምዕራፉ ያልተካተቱይዘቶች | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ክሂሎች | የዕውቀት ዘርፎች | ክሂሎች | የዕውቀት ዘርፎች | ገጽ |
| አንድ | የሥራ ባህልና ምርት | ማዳመጥ<br>ንግግር<br>ንባብ<br>ጽህፈት | ሰዋስው | | ሥነ-ፀሁፍ | 1-2<br>3-4<br>4-8<br>8-12<br>13 |
| ሁለት | የህይወት ክህሎት | ማዳመጥ<br>ንግግር<br>ንባብ<br>ጽህፈት | ሰዋስው | | ሥነ-ፀሁፍ | 16-17<br>18-19<br>19-21<br>21-23<br>24-26 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሶስት | ሱስና አደንዛዥ ዕጽ | ማዳመጥ<br>ንግግር<br>ንባብ<br>ጽህፈት | ሰዋስው | | ሥነ-ፀሁፍ | 29-30<br>30-32<br>32-36<br>36-37<br>38 |
| አራት | ልቦለድ | ማዳመጥ<br>ንግግር<br>ንባብ<br>ጽህፈት | ሰዋስው | | ሥነ-ፀሁፍ | 41-42<br>43-44<br>44-46<br>46-48<br>48 |
| አምስት | እንግዳ ተቀባይ | ማዳመጥ<br>ንግግር<br>ንባብ<br>ጽህፈት | ሰዋስው | | ሥነ-ፀሁፍ | 51-52<br>52<br>53-56<br>57-58<br>58 |
| ስድስት | ባህላዊ ክንውኖች | ማዳመጥ<br>ንግግር<br>ንባብ<br>ጽህፈት | ሰዋስው | | ሥነ-ፀሁፍ | 61-62<br>63<br>63-66<br>67<br>68 |
| ሰባት | አካቶ ትምህርት | ማዳመጥ<br>ንግግር<br>ንባብ<br>ጽህፈት | ሰዋስው | | ሥነ-ፀሁፍ | 72-73<br>73<br>74-76<br>76-77<br>79 |
| ስምንት | ሥነ-ግጥም | ማዳመጥ<br>ንግግር<br>ንባብ<br>ጽህፈት | ሰዋስው | | ሥነ-ፀሁፍ | 82<br>83<br>84-86<br>87<br>88 |
| ዘጠኝ | አንድነትና ብዝሀነት | ማዳመጥ<br>ንግግር<br>ንባብ<br>ጽህፈት | ሰዋስው | | ሥነ-ፀሁፍ | 91---92<br>92-95<br>96--97 |
| አሥር | ስደት | ማዳመጥ<br>ንግግር<br>ንባብ<br>ጽህፈት | ሰዋስው | | ሥነ-ፀሁፍ | 100-101<br>101-104<br>104-105<br>105-106 |

እንደ አጠቃላይ ስታይ በዚህ መጽሀፍ ዝግጅት የይዘት ስፋትና ጥልቀት ልዩነት ይኑረው እንጂ ሁሉም ማለትም አራቱም ክሂሎች እና ሰዋስው በአሥሩም ምዕራፎች ተካተዋል ወይም ተደራጅተዋል፡፡

## 4.1.3. ከአሥረኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፉ የተሰበሰቡ አጠቃላይ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ዝርዝር፡-

**ሠንጠረዥ ሁለት ከመማሪያ መጽሐፉ የተሰበሰቡ አጠቃላይ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ዝርዝር**

| ምዕራፍ | ይዘት | ገጽ |
|---|---|---|
| አንድ | የደብዳቤ አጻጻፍ፣ኢ-መደበኛ (የግል) ደብደቤ፣እና መደበኛ (የሥራ)ደብዳቤ፣ የሰዎችን የህይወት ታሪክ መጻፍ | 8--12 |
| ሁለት | የማወዳደር እና የማነጻጸር የአጻጻፍ ስልቶች፣ላይ የቀረበውን ማስታወሻ መሠረት አድርጋችሁ ቀጥሎ ከቀረቡት ተግባራት መካከል አንዱን በመምረጥ ሥሩ:- በትዊተርና በፌስቡክ መካከል ያሉ ልዩነቶችን በማንሳት አንድ አንቀጽ ያለው አነጻጻሪ ጽሑፍ አዘጋጁ፡፡በስልክና በበይነ መረብ መካከል ያሉ ተመሳሳይነቶችን በማንሳት አንድ አንቀጽ ያለው ጽሑፍአዘጋጁ፡፡በኢሜል መልዕክትን መላክና በፖስታ መልዕክትን መላክ አስመልክቶ መረጃዎችን ከድረ ገጾች በመፈለግ በሁለቱ መካከል ያለውን ተመሳስሎ በማንሳት ከአንድ ገጽ ያልበለጠ አመዛዛኝ ድርሰት ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡ቴሌ ብርና ሞባይል ባንክ በተሰኙት አገልግሎቶች መካከል ያሉ ልዩነቶችን በማንሳት ከአንድ ገጽ ያልበለጠ <u>**አመዛዛኝ ድርሰት**</u> ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡ | 22-23 |
| ሶስት | 1.የድርሰት አጻጻፍ መርሆች .<br>2.ቀጥሎ በቀረቡት ጽሑፎች ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላት በሚገኙበት አውድ መሠረት ያላቸውን አገባባዊ ፍችጻፉ፡፡በዚህ ትዕዛዚ ከተሰጡት ለአብነት የተወሰደ፡- 2.1.ለረጅም ጊዜ በሱስ <u>**መጠመድ**</u>ና ተጋላጭ መሆን የአእምሮ ጉዳት፣ የማስታወስ ክህሎት ማሽቆልቆል፣ ተስፋመቁረጥ፣ እራስን መቆጣጠር አለመቻልና ሌሎች ተጓዳኝ የአካልና የሥነ-ልቦና ቀውሶችንና ብሎም ሞትን ሊያስከትል ይችላል፡፡ | 36--37 |
| አራት | መጻፍን ለመማር ጠቃሚ መመሪያ ፡-ሀሳብንማመንጨት፤ሀሳብን መምረጥ፣ቢጋር ማዘጋጀት፣ማርቀቅና መጻፍ፤ጅምር ሀሳብ አሟልታችሁ አንቀጽ ጻፉ፤ቃላትን በመጠቀም በልቦለድ ውስት የላቸውንአጠቃቀም ለመለየት የሚያስችል አጭር ልቦለድ ጻፉ፡፡. ከላይ የቀረበውን መመሪያ መሰረት በማድረግ የሚከተለውን ጅምር ሀሳብ አሟልታችሁ አንቀጽ ጻፉ፡፡ከታች የቀረበውን ግጥም እንደገና በማስተካከል ጻፉ፡፡ከላይ በምዕራፉ የቀረበውን የልቦለድ ምንባብ ጭብጦች/ መልዕክቶች አሳጥራችሁ በሁለት አንቀጽ ጻፉ፡፡ከታች የተዘረዘሩ ቃላትን በመጠቀም ቃላት በልቦለድ ውስጥ ያላቸውን አጠቃቀም ለማሳየት የሚያስችል አጭር ልቦለድ ጻፉ፡፡ከዚህ በታች የሚገኙት አረፍተ ነገሮች ሰዋስዋዊ ስህተቶች ያሉባቸው ስለሆኑ አስተካክላችሁ ጻፏቸው፡፡ | 46--49 |

| | | |
|---|---|---|
| አምስት | ስለእንግዳ አቀባበል በመጠየቅ መጻፍ፤ሁለት አንቀጽ ድርሰት ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፤ቃላትን ተጠቅማችሁ አንድ አንቀጽ ጻፉ፤የግጥምን ጭብጥ ጸሀፊው የት ሆኖ እንደጻፈው በማሰላሰልአንድ አጭር ድርሰት አዘጋጁ፤ የሚከተሉትን አያያዥ ቃላት ተጠቅማቸሁ አንድ አንቀጽ ጻፉ። ርዕስ መምረጥ፣ ቢጋር መንደፍ፣ ማርቀቅ፣ መጻፍ፣ ማደት፣ እንደገና መጻፍ፣ የሚሉ ቅደም ተከተሎችን በመጠበቅ በመረጣችሁት ርእስ አንቀጽ ጻፉ።<br>ከዚህ በታች የቀረበውን ግጥም በጥንቃቄ አንብቡና የግጥሙን ጭብጥና ጸሐፊው የት ሆኖ እንደጻፈው በማሰላሰል አንድ አጭር ድርሰት አዘጋጁ።በአንቀጽ ውስጥ አገልግሎት ላይ የዋሉ አሥር ዋናዋና ቃላት ናቸው የምትሏቸውን ለቅማችሁ አውጡና መዝገበ ቃላዊ ፍቻቸውን ጻፉ፤ | 57–58 |
| ስድስት | | |
| ሰባት | አራቱ የድርሰት ዓይነቶች፤አንድ ርዕስ መርጣችሁ ከ150 ቃላት ባልበለጠ ተራኪ፣ስዕላዊ፣አስረጂ ወይም አመዛዛኝ ድርሰት ጻፉ፤ስለአካል ጉዳተኞች መረጃ በማሰባሰብ ታሪካቸውን የሚገልጽ ድርሰት ጻፉ፤ሴቶችን ማስተማር ማህበረሰብን ማስተማር ነው፤በዚህ ሀሳብ ጽሁፍ አዘጋጁ።አካል ጉዳተኛ የሆኑ ሰዎች አካል ጉዳተኛ ካልሆኑ ሰዎች እኩል ውጤታማ መሆን ይችላሉ በሚል ርዕሰ ጉዳይ ድርሰት ጻፉ።ቀጥሎ የቀረቡት አረፍተ ነገሮች ሰዋስዋዊ ስህተቶች አሉባቸው። ስህተቶቹን በማረም ሰዋስዋዊ ህጎችን የጠበቁ አረፍተ ነገሮች ጻፉ። | 76--79 |
| ስምንት | ግጥምሞችን አሚልታችሁ ጻፉ፤ስለመማሪያ ክፍላችሁ አጭር ግጥም ጻፉ፤የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች አብራርታችሁ ጻፉ። | 87 |
| ዘጠኝ | ባህሎችን አስመልክቶ ከሽማግሌዎች በመጠየቅና መጽሀፍትን በማንበብ አንቀጽ ጻፉ፤ባህላዊ የእርቅ ሥርዓት የሚገልጽ ድርሰት ጻፉ፤የጋብቻ ዓይነቶችን ጻፉ፤ባህላዊ ጋብቻ ሲከናወን የሚደረጉ ነገሮችን መረጃ ከሰበሰባችሁ በኋላ ሙሉ ሂደቱን የሚገልጽ ጽሁፍ አዘጋጁ። | 67 |
| አስር | . በምዕራፍ ሰባት በቀረበው ድርሰት አጻጻፍ መመሪያ መሰረት በሚከተሉት ርዕሶች አመዛዛኝድርሰትጻፉ።መምህርና ተማሪ ገጠርና ከተማ ትምህርት ቤትና ገበያ እናንተ በመረጣችሁት ርዕስ በምክንያትና ውጤት የአጻጻፍ ስልት አንቀጽ ጻፉና ለጓደኞቻችሁ አሳዩ።ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጻቸው የተስማሙ አስር አረፍተ ነገሮች ጻፉ። | 104 |

# 4.2.በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተካተቱ የጽህፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ

## 4.2.1.ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ

ይህ የአቀራረብ ስልት ትኩረት የሚያደርገው ዝርዝር የቋንቋ ባህርያትን የሚያሳዩ ምሳሌዎችና መልመጃዎች አጢነው ከተገነዘቡና ከሰሩ በኋላ አጠቃላይ የጽህፈት ክሂልን ሥርዓት እንዲረዱ የሚያደርግ ነው። Woods (1995:76) ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ማቅረብ ማለት በአግባቡ የተመረጡ ምሳሌዎች በማቅረብ ተማሪዎች የቀረቡትን ምሳሌዎች መሠረት

አድርገው የተሰጥዋቸውን የጽህፈት ክንውን ከሰሩ በኂላ የቋንቋውን የጽህፈት ሥርዓት በራሳቸውእንዲደርሱበት የሚያደርግ አካሄድ የተከተለ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ በመሆኑም የአቀራረብ ስልቱ ተማሪዎቹ ከቋንቋው ዝርዝር ተነስተው አጠቃላይ ወደሆነው የቋንቋ ህግ እንዲሸጋገሩ የሚያስችል አካሄድን የሚከተል መሆኑን Larsen-Freeman (1991) ይጠቁማሉ፡፡ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የሚደረግ የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ተማሪዎች ስለ ቋንቋው ህግ በቀጥታ ከመማራቸው በፊት ከዝርዝር ትምህርት ተነስተው በራሳቸው የመረዳት አቅም የቋንቋውን የጽህፈት ሥርዓትን በራሳቸው ጥረት እንዲተገብሩት የሚያደርግ የይዘት አደረጃጀት እንደሆነ በምዕራፍ ሁለት ላይ ተጠቁሟል፡፡

በመሰረቱ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የሚባለው አንድ ጽሁፍ ከመነሻው በምሳሌዎች እና በመረጃዎች ተደግፎ እየተተነተነ ወይም እየተዘረዘረ መቋጫው ላይ ጥቅል ሀሳብ ሲኖረው ነው፡፡ በመሆኑም በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ በአብነት ተጠቅሰው ከቀረቡ የጽህፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ውስጥ ቀጥሎ የቀረቡትን ለምሳሌ ምዕራፍ አራት ገፅ 46–49 ላይ "ልቦለድ "በሚለው ርዕስ ላይ የሚከተለውን ማየት እንችላለን፡-

- ሀሳብን ማመንጨት፤ሀሳብን መምረጥ፣ቢጋር ማዘጋጀት፣ ማርቀቅና መጻፍ፤ጅምር ሀሳብ አሟልታችሁ አንቀጽ ጻፉ፡፡
- ቃላትን በመጠቀም በልቦለድ ውስጥ የላቸውን አጠቃቀም ለመለየት የሚያስችል አጭር ልቦለድ ጻፉ፡፡.
- ከላይ የቀረበውን መመሪያ መሰረት በማድረግ የሚከተለውን ጅምር ሀሳብ አሟልታችሁ አንቀጽ ጻፉ፡፡

ከላይ ከቀረበው ይዘት ሀሳብን በማመንጨት አንቀጽ መጻፍ፣ቃላትን በመጠቀም ልቦለድን መጻፍ እና መመሪያን መሠረት በማድረግ ጅምር ሀሳቦችን ማስፋት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የሆነ ተግባር ነው፡፡ከላይ ከተጠቀሱት አንዱን እንኳ ብንወስድ መመሪያን መሰረት በማድረግ ጅምር ሀሳብን አሟልቶ መጻፍ፣ መመሪያ በራሱ ብቻ የአንድን ነገር አሰራር ወይም ሁነት የሚያመለክት ቅደም ተከተል ያለው ዝርዝር ሀሳብ ነው፤ጅምር ሀሳብ ደግሞ ተዘርዝሮ ያላለቀ ከተዘረዘረ በኂላ ተጠቃሎ የሚያልቅ ሀሳብ ነው፤በዚህ ሁኔታ የሚቀርቡት ሀሳቦች መንደርደሪያ ኖሯቸው እየተዘረዘሩ ወደማጠቃለያ ጭብጥ የሚደረስበት የአጻጻፍ ሂደት እንደሆነ መረዳት እንችላለን፡፡

በአጠቃላይ በተደረገው የሰነድ ግምገማ ወይም ፍተሻ በአስረኛ ክፍል መማሪያ ማጽሀፍ ውስጥ የተገለጹት ከዝርዝር ወደአጠቃላይ የቀረቡ የጽህፈት ክሂል የትምህርት ይዘቶች በተለያየ የአቀራረብ ስልት ይገኛሉ፡፡ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተካተቱ የጽህፈት ክሂል አቀራረቦች ከዝርዝር ወደአጠቃላይ ዘዴን ተከትለው የተደራጁ ቢሆኑም ምሳሌዎቹን ብቻ መሠረት በማድረግ የሚተገበሩ መልመጃዎች ሁሉንም ተማሪዎች ባገናዘበ መልኩ ትክክለኛ የሆነውን የቋንቋው የጽህፈት ክሂልን ህግ በራሳቸው ለመለማመድ እንደሚችሉ መረዳት ይቻላል፡፡ይህ ሊሆን የሚችልበት ምክንያት አንድ ትዕዛዝ በአንድ ጉዳይ ላይ ብቻ ስለማያተኩር ነው፡፡ለምሳሌ በምዕራፍ አምስት ገጽ 57 ላይ ከዚህ በታች የቀረበውን ግጥም በጥንቃቄ አንብቡና የግጥምን ጭብጥ ጸሀፊው የት ሆኖ እንደጻፈው በማሰላሰል አንድ አጭር ድርሰት አዘጋጁ፤ የሚከተሉትን አያያዥ ቃላት ተጠቅማችሁ አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡ ርዕስ መምረጥ፣ ቢጋር መንደፍ፣ ማርቀቅ፣ መጻፍ፣ ማደት፣ እንደገና መጻፍ፣ የሚሉ ቅደም ተከተሎችን በመጠበቅ በመረጣችሁት ርእስ አንቀጽ ጻፉ፡፡በምዕራፍ ዘጠኝ ገጽ 96 ላይ የድርሰት አጻጻፍ ህግጋትን ተከትላችሁ በአንድነትና ብዝሃነት ላይ ያተኮረ አመዛዛኝ ድርሰት ጻፉ፡፡
ይህ ማለት የግድ አንድና ሁለት ጉዳዮች ላይ ብቻ አፅንኦት ይደረግ ለማለት አይደለም፡፡ምክንያቱም በአንድ ይዘት ውስጥ ከሁለት ያለፉ ነገሮች መቅረባቸው ይዘቶቹን ከዝርዝር ሀሳብ ወይም ተያያዥነት ያላቸውን ሀሳቦች ተማሪዎቹ እየተለማመዱ ወደ ጥቅል ሀሳብ እንዲሄዱ የሚያስችል ጥሩ ጎን ይኖረዋል ማለት ነው፡፡

የዚህ አቀራረብ ስልት ጠንካራና ደካማ ጎኖች የሚባሉት፡ -

**ጠንካራ ጎኖች፡**

- አእምሯቸውን በስፋት እና በጥልቀት እንዲጠቀሙበት ያግዛቸዋል፤
- የእርስ በእርስ መስተጋብርን ስለሚፈቅድ ለቋንቋ ክሂሎች መዳበር ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፤
- ተማሪዎች ከሚቀርቡላቸው ምሳሌዎች ተነስተው ህግጋትን እንዲያወጡ ስለሚጋብዛቸው በነፃነት የመማርና በራስ የመተማመን ችሎታቸውን ያዳብራሉ፤
- የመመር ፍላጎታቸውን ያነሳሳል፤ እና ችግር አፈታት ችሎታቸውን ያዳብራል፡፡

**ደካማ ጎኖች፡-**

- በህግጋት ትንታኔ መማር የለመዱ ተማሪዎችን ግራ ሊያጋባ ይችላል፤
- ጊዜና ጉልበት ያባክናል፤የጽህፈት ሥርዓቶቹ ለተማሪዎቹ መጀመሪያ ላይ ስለማይቀርቡ ተማሪዎቹ ወደተሳሳተ ግንዛቤ እንዲያመሩ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም የተጠቀሱትን ዝርዝር ሀሳቦች በሠንጠረዥ ሶስት ጠቅለል አርገን እናያለን፡፡

ሠንጠረዥ ሶስት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የቀረቡ የጽህፈት ትምህርት ይዘቶች

| ምዕራፍ | ርዕስ | ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የቀረቡ የጽህፈት ትምህርት ይዘቶች | ገፅ |
|---|---|---|---|
| አራት | ልቦለድ | መጻፍን ለመማር ጠቃሚ መመሪያ ፡-<br>• ሀሳብንማመንጨት፤ ሀሳብን መምረጥ፣ ቢጋር ማዘጋጀት፣ ማርቀቅና መጻፍ፤ ጅምር ሀሳብ አሟልታችሁ አንቀጽ ጻፉ፡፡<br>• ቃላትን በመጠቀም በልቦለድ ውስጥ የላቸውን አጠቃቀም ለመለየት የሚያስችል አጭር ልቦለድ ጻፉ፡፡.<br>• ከላይ የቀረበውን መመሪያ መሰረት በማድረግ የሚከተለውን ጅምር ሀሳብ አሟልታችሁ አንቀጽ ጻፉ።<br>• ከላይ በምዕራፉ የቀረበውን የልቦለድ ምንባብ ጭብጦች/ መልዕክቶች አሳጥራችሁ በሁለት አንቀጽ ጻፉ።<br>• ከታች የተዘረዘሩ ቃላትን በመጠቀም ቃላት በልቦለድ ውስጥ ያላቸውን አጠቃቀም ለማሳየት የሚያስችል አጭር ልቦለድ ጻፉ።<br>• ከዚህ በታች የሚገኙት አረፍተ ነገሮች ሰዋስዋዊ ስህተቶች ያሉባቸው ስለሆኑ አስተካክላችሁ ጻፏቸው። | 46--49 |
| አምስት | እንግዳ ተቀባይ | • ቃላትን ተጠቅማችሁ አንድ አንቀጽ ጻፉ፤<br>• የግጥምን ጭብጥ ጸሀፊው የት ሆኖ እንደጻፈው በማሰላሰልአንድ አጭር ድርሰት አዘጋጁ፤<br>• የሚከተሉትን አያያዥ ቃላት ተጠቅማቸሁ አንድ አንቀጽ ጻፉ። ርዕስ መምረጥ፣ ቢጋር መንደፍ፣ ማርቀቅ፣ መጻፍ፣ ማደት፣ እንደገና መጻፍ፣ የሚሉ ቅደም ተከተሎችን በመጠበቅ በመረጣችሁት ርእስ አንቀጽ ጻፉ።<br>• ከዚህ በታች የቀረበውን ግጥም በጥንቃቄ አንብቡና የግጥሙን ጭብጥና ጸሐፊው የት ሆኖ እንደጻፈው በማሰላሰል አንድ አጭር ድርሰት አዘጋጁ። | 57--58 |
| ዘጠኝ | አንድነትና ብዝሀነት | • እያንዳንዳችሁ በምትኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ ያለውን ማህበራዊ ግንኙነት በሚመለከት አንቀጽ ጻፉ።<br>• የድርሰት አጻጻፍ ህግጋትን ተከትላችሁ በአንድነትና ብዝሃነት ላይ ያተኮረ አመዛዛኝ ድርሰት ጻፉ።<br>• ከተዘረዘሩት ቃላት ውስጥ የተወሰኑትን መነሻ በማድረግ አንድ አንቀጽ ጻፉ። | 96 |
| አስር | ስደት | በምዕራፍ ሰባት በቀረበው ድርሰት አጻጻፍ መመሪያ መሰረት በሚከተሉት ርዕሶች አመዛዛኝ ድርሰትጻፉ።መምህርና ተማሪ ገጠርና ከተማ ትምህርት ቤትና ገበያ እናንተ በመረጣችሁት ርዕስ በምክንያትና ውጤት የአጻጻፍ ስልት አንቀጽ ጻፉና ለጓደኞቻችሁ አሳዩ። | 104 |

በጥቅሉ  በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተካተቱ የጽህፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ ለመቅረባቸው ከላይ ለአብነት የተጠቀሱት ያመለክቱናል፡፡

በሠንጠረዡ ውስጥ ካሉት ለምሳሌ በሠንጠረዡ መጀመሪያ ላይ የሚገኘውን ምዕራፍ አራት ላይ ሀሳብን ማመንጨት፤ሀሳብን መምረጥ፣ቢጋር ማዘጋጀት፣ ማርቀቅና መጻፍ፤ጅምር ሀሳብ አሟልታችሁ አንቀጽ ጻፉ፡፡የሚለው የጽህፈት ክሂል ክንውን እና ቃላትን በመጠቀም በልቦለድ ውስጥ የላቸውን አጠቃቀም ለመለየት የሚያስችል አጭር ልቦለድ ጻፉ፣የሚሉት የጽህፈት ክሂል ክንውኖች ጅማሬያቸው ዝርዝር ሆኖ ፍጻሜያቸው ጥቅል ሀሳብ የሚሆን ነው፡፡
ምዕራፍ አሥርን ገፅ 104ን ብናይ እንዲጻፉ ትዕዛዝ የተሰጠባቸው ይዘቶችን ብናይ በምክንያትና ውጤት የሚዘረዘሩ ነገርች ናቸው፡፡ማብቂያቸው ወይም ድምዳሜያቸው የተዘረዘሩት ነገሮች በጭብጥ ይጠቃለላሉ፡፡

## 4.2.2. ከአጠቃላይ ወደዝርዝር አቀራረብ

- በዚህ ስልት ተማሪዎች ስለሚማሩት ቋንቋ ህግጋት የሚያሳይ ገለጻ ይቀርብላቸዋል፡፡ ከገለጻው በመነሳትም ክሂሉን ለመተግበር ወይም ለተግባቦት ለማዋል ይሞክራሉ፡፡ ይህም መሆኑ ተማሪዎች የቋንቋውን ህግጋት በፍጥነትና በቀላሉ እንዲረዷቸው ያስችላችዋል፡፡ ሆኖም ይህ ብቻውን በቂ አይሆንም፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች በገለጻ ብቻ በመታገዝ ክሂሉን በጥቅም ላይ ወይም ለተግባቦት ማዋሉ አዳጋች ሊሆንባቸው ይችላል፡፡ ስለዚህ ገለጻው በበቂ ምሳሌዎች ተደግፎ ሊቀርብ ይገባል (Cunningsworth፣ 1995)፡፡ Harmer (1987) እና Larsen-Freeman (1991) ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደርጃጀት ስልትን አስመልክቶ ከላይ ከቀረበው ገለጻ ጋር ተመሳሳይ ገለጻ ሰጥተዋል፡፡ በዚህ የአቀራረብ ስልት ለተማሪዎች  ክሂሎችን የሚያሳይ ገለጻ ይቀርብላቸዋል፡፡ ገለጻውንም መሠረት በማድረግ ህግጋቱን በዝርዝር መለማመድ ይቀጥላሉ፡፡

  **ጠንካራ ጎኖቹ፡ -**

- የጽህፈት ክሂሉን በቀጥታ የሚያቀርብ በመሆኑ ጊዜ ይቆጥባል፤
- ተማሪዎቹ የጽህፈት ክሂሉን ከተረዱ በኋላ ምሳሌ ያቀርብላቸዋል፤
- የማገናዘብ ችሎታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎችን የመማር ስልት ያጠናክራል፡፡

  **ደካማ ጎኖች፡-**

- የጽህፈት ክሂሉን  በቀጥታ በመግለፅ የሚጀምር በመሆኑ በተለይ ለህፃናት ይከብዳቸዋል፤

- የትምህርቱ አቀራረብ በመምህሩ የሚመራ በመሆኑ የተማሪዎቹን ተሳትፎና የእርስ በእርስ ግንኙነት ይገድባል፣

ከላይ በዝርዝር ለማየት እንደተሞከረው ሁለቱም የአቀራረብ ስልቶች የየራሳቸው ጥንካሬና ድክመት ይታይባቸዋል፡፡ በተለይም አንዱ አቀራረብ የሌላኛው ግልባጭ ከመሆኑ የተነሳ የአንዱ ጥንካሬ የሌላው ድክመት ሆኖ ታይቷል፡፡ በመሆኑም አንደኛው የሌላኛውን ክፍተት የሚሞላ መሆኑን ተገንዝቦ እንደ አስፈላጊነታቸው ሁለቱንም አቀራረቦች እያፈራረቁ ጥቅም ላይ ማዋል ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች የተለያዩ እንደመሆናቸው መጠን የተለያየ የትምህርት አቀባበል ችሎታ፣ የመማር ስልት ምርጫ፣ ወዘተ ያላቸው መሆናቸውም ልብ ሊባል ይገባል፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን በተለያዩ የትምህርት አላማዎች፣የተለያዩ የአቀራረብ ስልቶችን የሚከተሉ ከመሆናቸው የተነሳ እነዚህንና መሰል ሁነቶችን ለማቻቻል እንደየሁነቱ ሁለቱንም የአቀራረብ መርሆዎች በተገቢው ሁኔታ እያፈራረቁ መጠቀም የሚያስፈልግ መሆኑን Harmer (1991) ያስገነዝበናል፡፡

በዚህ የአቀራረብ ዘዴ በቅድሚያ የሚቀርበውን የጽህፈት ክሂል ይዘትን በሚመለከት የቋንቋው ህግ የሚፈቅደውን አቀራረብ መሠረት በማድረግ ተማሪዎች የጽህፈት ክሂል ክንውንን መነሻ በማድረግ የተዘጋጁትን የጽህፈት ክሂሎችን ክንውን እንዲሰሩ የሚያደርግ አቀራረብ ነው፡፡

ቀጥሎ በቀረቡት ጽሑፎች ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላት በሚገኙበት አውድ መሠረት ያላቸውን አገባባዊ ፍችጻፉ፡፡በዚህ ትዕዛዚ ከተሰጡት ለአብነት የተወሰደ፡-ለረጅም ጊዜ በሱስ <u>**መጠመድ**</u>ና ተጋላጭ መሆን የአእምሮ ጉዳት፣ የማስታወስ ክህሎት ማሽቆልቆል፣ተስፋ መቁረጥ፣እራስን መቆጣጠር አለመቻልና ሌሎች ተጓዳኝ የአካልና የሥነ-ልቦና ቀውሶችንና ብሎም ሞትን ሊያስከትል ይችላል፡፡
የልምምድ ሂደታቸው ወደ ዝርዝር የቀረቡ ናቸው፡፡ በመቀጠልም መመሪያ ተሰጥቶባቸው የቀረቡትን የጽህፈት ክሂል ይዘቶችን ስናይ በመማሪያ መጽሀፉ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የቀረቡ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች መረጃዎች፣ ልምምዶችና ምሳሌዎች ቀርበዋል፡፡

የቀረበውን መመሪያና ገለጻ በመመርኮዝ የጽህፈት ሥርዓትን ተከትለው በሚሰጡ ምሳሌዎች መሠረት እንዲሰሩ የሚያደርጉ አቀራረቦች በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ መዘጋጀታቸው ለመማር

ማስተማሩ ሂደት ምቹ መሆናቸውን እንገነዘባለን፡፡ለዚህም  መረጃ ይሆን ዘንድ ከላይ የተገለጸውን ሠንጠረዥ አራትን መመልከት ይቻላል፡፡

**ሠንጠረዥ አራት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የቀረቡ የጽህፈት ትምህርት ይዘቶች**

| ምዕፍ | ርዕስ | ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የቀረቡ የጽህፈት ትምህርት ይዘቶች | ገፅ |
|---|---|---|---|
| ሶስት. | | 1.የድርሰት አጻጻፍ መርሆች<br>2.ቀጥሎ በቀረቡት ጽሑፎች ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላት በሚገኙበት አውድ መሠረት ያላቸውን አገባባዊ ፍችጻፉ፡፡በዚህ ትዕዛዚ ከተሰጡት ለአብነት የተወሰደ፡-<br>2.1.ለረጅም ጊዜ በሱስ <u>መጠመድ</u>ና ተጋላጭ መሆን የአእምሮ ጉዳት፣ የማስታወስ ክህሎት ማሽቆልቆል፣ተስፋ መቁረጥ፣እራስን መቆጣጠር አለመቻልና ሌሎች ተጓዳኝ የአካልና የሥነ-ልቦና ቀውሶችንና ብሎም ሞትን ሊያስከትል ይችላል፡፡ | 36-37 |
| አራት | ልቦለድ | • ከላይ በምዕራፉ የቀረበውን የልቦለድ ምንባብ ጭብጦች/ መልዕክቶች አሳጥራችሁ በሁለት አንቀጽ ጻፉ | 46-49 |
| አምስት | እንግዳ ተቀባይ | • በአንቀጽ ውስጥ አገልግሎት ላይ የዋሉ አሥር ዋናዋና ቃላት ናቸው የምትሏቸውን ለቅማችሁ አውጡና መዝገበ ቃላዊ ፍቻቸውን ጻፉ፤ | 57-58 |
| ስድስት | ባህላዊ ክንውኖች | • ባህላዊ የእርቅ ሥርዓት የሚገልጽ ድርሰት ጻፉ፤ | 67 |
| ሰባት | አካቶ ትምህርት | • አራቱ የድርሰት ዓይነቶች፤አንድ ርዕስ መርጣችሁ ከ150 ቃላት ባልበለጠ ተራኪ፣ስዕላዊ፣አስረጂ ወይም አመዛዛኝ ድርሰት ጻፉ፤ | 76-79 |
| ስምንት | | • የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች አብራርታችሁ ጻፉ፡፡ | 87 |
| ዘጠኝ | አንድነትና ብዝሀነት | • “በኢትዮጵያ የአስተዳደር ሥርዓቶች ታሪክ ውስጥ ከሚገኙ ቁልፍ ጽንሰ ሀሳቦች መካከል አንድነትና ብዝሃነት ዋነኞች ናቸው፤” ሲባል ምን ማለት እንደሆነ ለክፍል የሚቀርብ ማብራሪያ ጻፉ፡፡<br>• ቅጥያ ያልተጨመረባቸውን ቃላት ለይታችሁ ጻፉ፡፡ | 96 |

ሲጠቃለል በአዲሱ *መማሪያ መጽሀፍ ዝግጅት* **ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የቀረቡ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ጥቅል የሆነን ርዕሰ ጉዳይ በመተንተን ላይ የተመሠረቱ** በመሆናቸው ተማሪዎቹ አፅንኦት ሰጥተው እንዲጠቀሙ(እንዲተገብሩ)የተመቻቹ ናቸው፡፡ለምሳሌ በምዕራፍ ዘጠኝ ላይ ያለውን ብቻ እንኳ ብናይ አንድነትና ብዝሀነት ሁለት የተለያየ ተቃራኒ ሀሳብ ያላቸው ጥቅል ሀሳቦች ናቸው፡፡የእነኚህን ሀሳቦች ማብራሪያ ጻፉ ሲባል ማብራሪያ ገለጻነው ገለጻ ደግሞ በምሳሌ እና በመረጃ በማስደገፍ የሚብራራ ጉዳይ ነው ከዚህ አንጻር ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ የጽህፈትንክሂሉ ቀርቧል ማለት ይቻላል፡፡

## 4.2.3.ውጤት ተኮር አቀራረብ

ይህ የአቀራረብ ስልት መሠረት የሚያደርገው በታላሚው ቋንቋ ተግባቦት ዙሪያ ባለው የቋንቋ ቅርፅ ላይ መሆኑን፣ Batstone (1994:51) ይገልጻሉ፡፡ እንደ Batstone (1994) አባባል ከተግባቦት መንገዶች አንዱ የጽህፈት ክሂል ነው፡፡ይህም ማለት ተማሪዎቹ በታላሚው ቋንቋ የጽህፈት ሥርዓት ላይ በማተኮር የቃላትና የዓረፍተነገር አሰዳደር ይሁን እንጂ የአቀራረብ ስልቱ ልማዳዊ የሆነ የጽህፈት ትምህርት የአቀራረብ መርህን የተከተለ፣ በመፃህፍት ላይ የተመሰረተና በዘዴው የሚቀርበው የጽህፈት ትምህርት ዓላማ ተግባቦት ላይ ብቻ የተመሰረተ ሳይሆን ተማሪዎች የቋንቋውን ቃላት በቃል ክፍላቸው በጽሁፍ እንዲለዩ፣ ቃላትን፣ ሀረጋትንና ዓረፍተ ነገራትን በተናጠል በመጻፍ እንዲተነትኑ እና እንዲመሰርቱ የሚያደርግ እንጂ እነዚህን ክንውኖች ከተግባቦት ጋር በማቀናጀት ብቻ እንዲለማመዷቸው የሚያስችል አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ግን ለማስተማር ሥራ ፈጣን መሆኑ፣ለመምህሩ ትምህርት አሰጣጥ ቀላልና ምቹ መሆኑ ደግሞ ከጠንካራ ጎኑ የሚጠቀሱት ናቸው፡፡

Harmer(1991)እና Batstone(1994:51)የአቀራረብ ስልቱን ጥንካሬና ድክመት በሚከተለው መልኩ አስፍረውታል፡፡

- ግብዓቶችንመርጦና አደራጅቶ ማቅረቡ፣
- ውስን ዓላማ ይዞ የተማሪውን ልምምድ በተወሰነ የጽህፈት ክንውን ላይ መገደቡና የጽህፈትን ሃሳብ ግንዛቤ ማስጨበጡ ከጠንካራ ጎኖቹ የሚጠቀሱ ሲሆኑ፣

ከደካማ ጎኖቹ የሚጠቀሱ ደግሞ

- የጽህፈት ይዘቶችን በመምረጥና በማደራጀት ሂደት የተማሪውን ፍላጎት መሠረት ያለማድረጉ፣

- ለጽህፈት  እንጂ ለጽህፈት ሂደት ወይም ሥርዓት ትኩረት ያለመስጠቱና
- ድርጊታዊ የማስተማሪያ ስልትን ያለመጠቀሙ ደግሞ ከደካማ ጎኖቹ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ በመሆኑም በውጤት ተኮር አቀራረብ የጽህፈት ክሂል ተግባራት እንደሚከናወኑ በምዕራፍ ሁለት ተጠቅሶ ነበር፡፡ በውጤት ተኮር ስልት የተዘጋጀው ትምህርት የተለያዩ የጽህፈት ክሂል ይዘቶችን  እንዲለማመዱ እና እንዲጽፉ በማድረግ ላይ ትኩረት አድርጓል፡፡ እንዲያው የበለጠ ግልጽ ለማድረግ ቃላትን መሠረት በማድረግ ወይም ቃላትን በመጠቀም የተለያዩ ጽሁፎችን በመጻፍ ክሂሉን ማጎልበት እንደሚቻል የሚከተሉትን ምሳሌዎች ለአብነት መመልከት ይቻላል፡፡

በምዕራፍ አምስት ገጽ 57-58 ላይ ቃላትን ተጠቅማችሁ አንድ አንቀጽ ጻፉ፤የግጥምን ጭብጥ ጸሀፊው የት ሆኖ እንደጻፈው በማሰላሰል አንድ አጭር ድርሰት አዘጋጁ፤ የሚከተሉትን አያያዥ ቃላት ተጠቅማቸሁ አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡በአንቀጽ ውስጥ አገልግሎት ላይ የዋሉ አሥር ዋናዋና ቃላት ናቸው የምትሏቸውን ለቅማችሁ አውጡና መዝገበ ቃላዊ ፍቻቸውን ጻፉ፡፡

በምዕራፍ ስምንት ገጽ 87 የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች አብራርታችሁ ጻፉ፡፡

በምዕራፍ ዘጠኝ ገጽ 96 ከተዘረዘሩት ቃላት ውስጥ የተወሰኑትን መነሻ በማድረግ አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡ቅጥያ ያልተጨመረባቸውን ቃላት ለይታችሁ ጻፉ፡፡

ከላይ ለአብነት በተጠቀሱት ላይ የምናየው ቃላትን መሠረት በማድረግ ከዓረፍተነገር እስከ ድርሰት ወይም ልቦለድ ድረስ በማጻፍ የጽህፈትን ክሂል ማለማመድ እና ማበልጸግ እንደሚቻል እንገነዘባለን፡፡

ከላይ ያየናቸው የጽህፈት ተግባራት የሚያመለክቱን የመጽሀፉ ዝግጅት ለአማርኛ ቋንቋ የጽህፈት ሥርዓት የሰጠውን አፅንኦት ስናይ የጽህፈት ክንውኑን ከቃላት መረጣ ጀምሮ እስከ ድርሰት መጻፍ ያሉ የጽህፈት ክንውኖችን ተማሪዎቹ ከየት ተነስተው የት መድረስ እንዳለባቸው የተገደቡ በመሆናቸው ውጤት ተኮር አቀራረብ እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡

## 4.2.4.ሂደት ተኮር አቀራረብ

በዚህ አቀራረብ ተማሪዎች ተግባቦታዊ በሆነ ዘዴ የጽህፈት ክሂልን በተግባር የሚለማመዱበትን ክንውን የምናይበት ነው፡፡በመሆኑም ለዚህ ተግባር የአሥረኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የተዘጋጁ ይዘቶችን የሚከተሉትን ለአብነት እናገኛለን፡፡

በምዕራፍ አራት ገጽ 46 ላይ መጻፍን ለመማር ጠቃሚ መመሪያ ፡-ሀሳብን ማመንጨት፤ ሀሳብን መምረጥ፣ቢጋር ማዘጋጀት፣ማርቀቅና መጻፍ፤ጅምር ሀሳብ አሟልታችሁ አንቀጽ ጻፉ፤ከላይ የቀረበውን መመሪያ መሰረት በማድረግ የሚከተለውን ጅምር ሀሳብ አሟልታችሁ አንቀጽ ጻፉ።

ምዕራፍ አምስት ገጽ 57 ላይ ርዕስ መምረጥ፣ ቢጋር መንደፍ፣ ማርቀቅ፣ መጻፍ፣ ማደት፣ እንደገና መጻፍ፣ የሚሉ ቅደም ተከተሎችን በመጠበቅ በመረጣችሁት ርእስ አንቀጽ ጻፉ።

ምዕራፍ ዘጠኝ ገጽ 96 ላይ የድርሰት አጻጻፍ ህግጋትን ተከትላችሁ በአንድነትና ብዝሃነት ላይ ያተኮረ አመዛዛኝ ድርሰት ጻፉ።

ምዕራፍ አሥር ገጽ 104 ላይ በምዕራፍ ሰባት በቀረበው ድርሰት አጻጻፍ መመሪያ መሰረት በሚከተሉት ርዕሶች አመዛዛኝ ድርሰትጻፉ።መምህርና ተማሪ ፣ገጠርና ከተማ፣ ትምህርት ቤትና ገበያ፣ እናንተ በመረጣችሁት ርዕስ በምክንያትና ውጤት የአጻጻፍ ስልት አንቀጽ ጻፉና ለጓደኞቻችሁ አሳዩ።

ከላይ ለአብነት በተጠቀሱት ላይ የምናየው ጽህፈትን የሚለማመዱበት እና የሚጽፉበት ትዕዛዝ በአብዛኛው መመሪያን መሠረት በማድረግ እና በመከተል የሚጽፉበት ትዕዛዞች ናቸው ያሉት፤ይህ የሚያመለክተን መመሪያ ቅደም ተከተል አፈጻጸም አለው፤ቅደም ተከተሉ ደግሞ ሂደታዊ ነው።

ሆኖም በአዲሱ የአሥረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የተማሪው መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ሂደት ተኮር አቀራረብ ይኑር እንጂ በመጠን ከሌሎቹ አቀራረቦች ያንሳል።ለምሳሌ የጽህፈት ክሂል ይዘቶችን ተማሪዎች ለብቻቸው እንዲለማመዱ የተደረገው ውጤት ተኮር አቀራረብ በመጽሀፉ ዝግጅት ውስጥ አብዛኛውን ክፍል እንደያዘ ከላይ በተሰጠው መረጃ መመልከት ይቻላል።ሆኖም ተማሪዎች ተግባቦታዊ በሆነ ስልት እንዲለማመዱና አንዲጠቀሙ ተመጣጣኝ እንዲሆን ቢደረግ የተሸለ ነበር።

ሲጠቃለል በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር የመጀመሪያ እትም 2014 ዓ.ም የሆነውን አማርኛን እንደፌዴራል ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀውን የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መጽሐፍ የጽህፈት ክሂል የይዘት አቀራረብ በአብዛኛው ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ሳይሆን ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የቀረበበት መንገድ ላቅ ያለ ይመስላል፤ከውጤት እና ሂደት ተኮር አቀራረብ ደግሞ በውጤት ተኮር ሂደት የቀረቡ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች በርከት እንደሚሉ ከላይ በምሳሌ ተመልክተናል።

በሂደታዊ አቀራረብ ሦስት የመማር ማስተማር ሂደቶች አሉ፡፡ቅድመ ጽህፈት፣የጽህፈት ጊዜ እና ድህረ ጽህፈት በመጽሀፉ ይዘት ለጽህፈት ትምህርት መማር ማስተማር ሂደት ይዘት የተካተቱ ናቸው፤ዝርዝሩን እንደሚከተለው እናያለን፡፡

## 4.2.1.ቅድመ ጽህፈት

ተማሪዎች የሚጽፉት መረጃ ለመሰብሰብ፣አንባቢውን ለማሰብ፣ዓላማውን ለመወሰን እና የመጀመሪያ ንድ ፍለማቀድ የሚሰሩትን ክንውን ያካትታል፡፡የቅድመ ጽህፈት ተግባር ላይ ለመጻፍ የሚያስችሉ አስተ ሰቦችን የሚያሰባስቡበት ሂደት እንደሆነ በምዕራፍ ሁለት ተጠቅሷል፡፡ከዚህ አንጻር በሚጠናው መጽሀፍ ውስጥ ለአብነት ምዕራፍ ሶስት ገጽ 36 ድርሰት በአንድ ርእሰ ጉዳይ ላይ የሚጻፍ ጽሑፍ ሲሆን ይህን ተግባር ለመከወንም በቅድመ ጽሕፈትና በጽሕፈት ሂደት ታሳቢ ሊደረጉ የሚገቡ ተግባራት አሉ፡፡

- ድርሰቱ የሚጻፍበትን ርእሰ ጉዳይ መምረጥ፡- አንዳንዴ ርዕሰ ጉዳይ ሊሰጥ ስለሚችል ሁልጊዜ ርዕሰ ጉዳይ መምረጥ የጸሐፊው/ዋ/ ሥራ ላይሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ጸሀፊው/ዋ/ በሚመቸው/ኣት/ መንገድ ርዕሱን ማስተካከል ይችላል /ትችላለች/፡፡
- የሚጻፍበትን ዓላማ ሊያሳካ በሚችል መልኩ ርዕሱን ማጥበብ (መወሰን)
- በተመረጠው ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ተገቢ መረጃዎችን መሰብሰብ እና በፈርጅ በፈርጃቸው ማደራጀት፣አጠቃላይ የጽሑፉን አካሄድ የሚያሳየውን ዕቅድ (በድርሰቱ ውስጥ መካተት የሚገባቸውን ማጠንጠኛ ነጥቦች የያዘ ንድፍ) ማዘጋጀት፣ጸሐፊው የሚጽፍበትን ዓላማ ማወቅ እና ጽሑፉ ለማን እንደሚዘጋጅ ማወቅ፡፡

## 4.2.2. የጽህፈት ጊዜ

የጽህፈት ጊዜ ሃሳብን በማርቀቅ በወረቀት ላይ ትክክለኛ የጽህፈት ክንውን የሚጀመርበት ሂደት ነው፡፡ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች በቅድመ ጽህፈት ደረጃ የሰበሰቡዋቸውን አመለካከቶች ወይም አስተሳሰቦች የሚጽፉበት ደረጃ ነው፡፡ በተጨማሪም ሀሳቦችን በቅደም ተከተል አደራጅተው ጽሁፉን ቅርጽ የሚያስይዙበት ክፍል እንደሆነ በምዕራፍ ሁለት ተገልጿል፡፡በመሆኑም በጽሕፈት ሂደት ታሳቢ ሊደረጉ የሚገቡ ተግባራት አሉ፡፡ ለአብነት ምዕራፍ ሶስት ገጽ 3 ላይ የጽሕፈት ጊዜ ተግባራት፡-

•በተዘጋጀው ንድፍ መሠረት ረቂቁን መጻፍ፣

• በረቂቁ ላይ ማስተካካያና እርማት ማድረግ፣

• የመጨረሻ ረቂቁን መጻፍ፡- ይህ ሲከናወን አላስፈላጊ ግድፈቶችን ማስተከካል ይገባል፡፡

### 4.2.3. ድህረ ጽህፈት

ድህረ ጽህፈት በጽህፈት ጊዜ የተጻፈውን ጽሁፍ እንዴት እንደተጻፈ የሚፈተሸበትና እንዲተላለፍ የተፈለገውን ሀሳብ ለማስተላለፍ የመጨረሻ ማስተካከያ የሚደረግበት ሂደት ነው፡፡ተማ ሪው የጽሁፉን መልእክት ለተደራሲው ግልጽ መሆኑን የሚረዳበት እና የሚያረጋግጥበት የትግበራ ሂደት እንደሆነ ይህም በምዕራፍ ሁለት ተጠቅሷል፡፡ ለአብነት ምዕራፍ ሶስት ገጽ 37 ላይ እንደሚከተለው የማጠቃለያ ተግባሩ ተገልጿል፡- ከላይ ያሉት ሁለቱ ተግባራት ከተሰሩ በኋላ ቀጥሎ ደግሞ ከላይ በቀረበው የድርሰት አጻጻፍ ማስታወሻ መሠረት አንድ ርዕስ በመምረጥ ድርሰት ጻፉ በማለት የመጨረሻውን ክንውን ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ ጽህፈትን በክፍል ውስጥ በመማር ማስተማር ሂደት ሶስቱም የጽህፈት ክንውን ተግባራት ደረጃቸውን(ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው እንደተከናወኑ ከላይ በተገለጸው ምሳሌ አይተናል፡፡ በመሆኑም በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተካተቱ የጽህፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ለተማሪው እና ለመምህሩ (ለመማር ማስተማሩ ሂደት )ምቹ ሆነው የተዘጋጁ ወይም የቀረቡ ናቸው፡፡

## 4.3. በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የጽህፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት

### 4.3.1.ተከታታይነት

በምዕራፍ ሁለት እንደተገለጸው ተከታታይነት በአንድ የክፍል ደረጃ የቀረበው የጽህፈት ክሂል የትምህርት ይዘት በዚያው ክፍል አልፎ አልፎ በየምዕራፎቹ ካልሆነም በተከታይ የትምህርት እርከን እየተደጋገመ የሚገኝ መሆኑን ቀደም ሲል በክለሳ ድርሳን ላይ ተመልክተናል፡፡በመሆኑም በዚህ ጥናት፣ ፍተሻ ወይም ግምገማ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር የመጀመሪያ እትም 2014 ዓ.ም የሆነው አማርኛን እንደፌዴራል ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀውን የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መጽሐፍ ውስጥ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ምንያህል በተደጋጋሚ እንደቀረቡ በሚቀጥለው ሠንጠረዥ እናያለን፡፡

## ሠንጠረዥ አምስት በመጽሀፉ ውስጥ በተከታታይ የቀረቡ የጽህፈት ትምህርት ይዘቶች

| ምዕራፍ | ቃላት መጻፍ | ዓረፍተነገር መጻፍ | አንቀጽ መጻፍ | ድርሰት መጻፍ | ልቦለድ መጻፍ | ግጥም መጻፍ | ደብዳቤ መጻፍ | የህይወት ታሪክ መጻፍ | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አንድ | | | | | | | ደብዳቤ አጻጻፍ | የህይወት ታሪክ መጻፍ | 8-12 |
| ሁለት | | | በትዊተርና በፌስቡክ መካከል ያሉ ልዩነቶችን በማንሳት **አንድ አንቀጽ** ያለው አነጻጻሪ ጽሑፍ አዘጋጁ፡፡ በስልክና በበይነ መረብ መካከል ያሉ ተመሳሳይነቶችን በማንሳት አንድ **አንቀጽ** ያለው ጽሑፍአዘጋጁ፡፡ | በኢሜል መልዕክትን መላክናበፖስታ መ ልዕክትን መላክ አ ስመልክቶ መረጃዎችን ከድረገጾች በመፈለ ግበሁለቱመካከልያ ለውን ተመሳስሎ በማንሳት ከአንድ ገጽ ያልበለ ጠ **አመዛዛኝ ድርሰት** | | | | | 22-23 |
| ሶስት | 2.ቀጥሎ በቀረቡት ጽሑፎች ውስጥ የተሰመረባ ቸው **ቃላት** በሚገኙበት አውድ መሠረትያላ ቸውንአገባባ ዊ ፍች ጻፉ፡፡ | | | | | | | | 36-37 |
| አራት | | ከዚህ በታች የሚገኙት **አረፍተ ነገሮች** ሰዋስዋዊ ስህተቶች ያሉባቸው ስለሆኑ አስተካክላ ችሁ ጻፏቸው፡፡ | መጻፍን ለመማር ጠቃሚ መመሪያ ሀሳብንማመንጨት፤ሀ ሳብንመምረጥ፣ቢጋርማዘጋጀት ፣ማርቀቅና መጻፍ፤ከላይ የቀረበውን መመሪያ መሰረት በማድረግ የሚከተለውን ጅምር ሀሳብ አሟልታችሁ **አንቀጽ ጻፉ**፡፡ከላይ በምዕራፉ የቀረበውን የልቦለድ ምንባብ ጭብጦች/ መልዕክቶች አሳጥራችሁ በሁለት **አንቀጽ ጻፉ**፡፡ | | ቃላትን በመጠቀም በልቦለድ ውስጥ የላቸውንአ ጠቃቀም ለመለየት የሚያስች ል አጭር **ልቦለድ ጻፉ**፡፡ | ከታች የቀረበው ን **ግጥም** እንደገና በማስተካ ከል ጻፉ፡፡ | | | 46-49 |
| አምስ ት | በአንቀጽ ው ስጥአገልግ ሎት ላይየዋ ሉ አሥር **ዋናዋና ቃላት** ናቸው የም ትሏቸውን ለቅማችሁ አውጡናመ ዝገበ ቃላዊ ፍቻቸውን ጻፉ፤ | | የሚከተሉትን አያያዥ ቃላት ተጠቅማቸሁ አንድ **አንቀጽ ጻፉ**፡፡ርዕስ መምረጥ፣ ቢጋር መንደፍ፣ ማርቀቅ፣ መጻፍ፣ ማደት፣ እንደገና መጻፍ፣ የሚሉ ቅደም ተከተሎችን በመጠበቅ በመረጣችሁት ርእስ **አንቀጽ ጻፉ**፡፡ | የግጥምን ጭብጥ ጸሀፊው የትሆኖ እንደጻፈው በማሰላሰልአንድ **አ ጭር ድርሰት** አዘጋጁ፤ | | | | | 57-58 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ስድስት | | | ባህሎችንአስመልክቶ ከሸማግሌዎች በመጠየቅና መጽሀፍትን በማንበብ **አንቀጽ ጻፉ**፤ | | | | | | 67 |
| ሰባት | | ቀጥሎ የቀረቡት **አረፍተ ነገሮች** ሰዋስዋዊ ስህተቶቹን በማረም ሰዋስዋዊ ህጎችን የጠበቁ **አረፍተ ነገሮች** ጻፉ። | | አራቱ **የድርሰትዓይነቶች**፤አንድ ርዕስ መርጣችሁ ከ150ቃላት ባልበለጠ ተራኪ፣ስዕላዊ፣አስረጂ ወይም **አመዛዛኝ ድርሰት ጻፉ**፤ስለአካል ጉዳተኞች መረጃ በማሰባሰብ ታሪካቸውን የሚገልጽ **ድርሰት ጻፉ**፤አካል ጉዳተኛ የሆኑ ሰዎች አካል ጉዳተኛ ካልሆኑ ሰዎች እኩል ውጤታማ መሆን ይችላሉ በሚል ርዕሰ ጉዳይ **ድርሰት ጻፉ**። | | | | | 76-<br>79 |
| ስምንት | **የቃላትን** እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች አብራርታችሁ ጻፉ። | | | | | **ግጥምሞችን** አሟልታችሁ ጻፉ፤ስለመማሪያ ክፍላችሁ **አጭር ግጥም** ጻፉ፤ | | | 87 |
| ዘጠኝ | ቅጥያ ያልተጨመረባቸውን **ቃላት** ለይታችሁ ጻፉ። | | እያንዳንዳችሁ በምትኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ ያለውን ማህበራዊ ግንኙነት በሚመለከት **አንቀጽ ጻፉ**።ከተዘረዘሩት ቃላት ውስጥ የተወሰኑትን መነሻ በማድረግ አንድ **አንቀጽ ጻፉ**። | የድርሰት አጻጻፍ ህግጋትን ተከትላችሁ በአንድነትና ብዝሃነት ላይ ያተኮረ **አመዛዛኝ ድርሰት ጻፉ**። | | | | | |
| አስር | | ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጻቸው የተስማሙ አስር **አረፍተ ነገሮች ጻፉ**። | በመረጣችሁት ርዕስ በምክንያትና ውጤት የአጻጻፍ ስልት **አንቀጽ ጻፉ**ና ለጓደኞቻችሁ አሳዩ። | በምዕራፍ ሰባት በቀረበው ድርሰት አጻጻፍ መመሪያ መሰረት በሚከተሉት ርዕሶች **አመዛዛኝ ድርሰት ጻፉ**። | | | | | |
| ድግግሞሽ | ቃላት አራት ጊዜ | ዓረፍተ ነገር ሶስት ጊዜ | **አንቀጽ አስር ጊዜ** | ድርሰት ሰባት ጊዜ | ልቦለድ አንድ ጊዜ | ግጥም ሁለት ጊዜ | | | |

- **በአጠቃላይ በአሥረኛ ክፍል አዲሱ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች 29 ጊዜ በተለያዩ የመማር ማስተማር ርዕሶች ወይም ይዘቶች ቀርበዋል፡፡**

በሠንጠረዡ የተገለጸው በየምዕራፎቹ ከቀረቡት አጠቃላይ ሀያ ዘጠኝ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ውስጥ አሥር (10) ጊዜ በመደጋገም የቀረበው ስለ አንቀጽ አጻጻፍ እንደሆነ ከሠንጠረዡ መመልከት

ተችሏል። በተለይ በምዕራፍ 2፣4፣5፣እና 9 ሁለት ሁለት ጊዜ በተከታታይ ቀርበዋል። የጽህፈት ክሂልን ከመማር እና ማስተማር አንጻር ከሉት ይዘቶች አንቀጽ ላይ የተደረገው ትኩረት ወይም አጽንኦት ለድርሰት ይዘቶች ጥሪጊያ መንገድ መክፈት እና ማነሳሳት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል።በመቀጠልም ከፍተኛ ድግግሞሽ ወይም ክትትሎሽ የተደረገው ድርሰት በመጻፍ ላይ ነው፤ይኸውም ሰባት(7) ጊዜ በተከታታይ እንዲማሩ ተደርጓል፤በተለይ በምዕራፍ ሰባት ሶስት ጊዜ በተከታታይ እንዲማሩ ተደርጎ ቀርቧል።ክሂሉን ከመማር ማስተማር አንጻር ከሌሎች ስልቶች ይልቅ በአንቀጽ እና በድርሰት ላይ የተደረገው ቅደም ተከተላዊ ቁጥር ያለው ድግግሞሽ የሚያመለክተን የክፍል ደረጃውን የተማሪዎቹን ዕድሜ እና ብስለት ያገናዘበ ተማሪዎቹ ወደፊት ጥሩ ጸሀፊ እንዲሆኑ ታስቦ የተሰራ ይመስላል፤ለዚህ አመለካከት የሚጋብዘው ነገር ሠንጠረዡን ስናይ ካሉትሀያ ዘጠኝ ተከታታይ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ውሰጥ አስራሰባቱ የተሸፈነው አንቀጽ እና ድርሰት መጻፍ ላይ ብቻ በመሆኑ ነው።

በመቀጠል በመጽሀፉ ዝግጅት በአነስተኛ መጠን በተከታታይ ወይም በድግግሞሽ የቀረቡት የጽህፈት ይዘቶች እንደየቅደም ተከተላቸው ቃላት አራት ጊዜ፣ዓረፍተነገር ሶስት ጊዜ ግጥም ሁለት ጊዜ ሲሆን ልቦለድ፣ደብዳቤ እና የህይወት ታሪክ አጻጻፍ ይዘቶች አንዳንድ ጊዜ ቀርበዋል። ሆኖም በዚህ ዝግጅት ሥነጽሁፍ እንደ ይዘት እንደሌሎቹ እራሱን ችሎ አልቀረበም፤ሥነጽሁፍን እንደአንድ ይዘት አለማካተቱ ተጨማሪ የጽህፈት ትምህርት እንዳይኖር ተደርጓል።

## 4.3.2.ተለጣጣቂነት

በአንድ የክፍል ደረጃ ለዛውም በተከታታይ የመማሪያ የክፍል ደረጃዎች ላይ የሚገኝ የትምህርት ልምድን(ይዘት)መነሻ በማድረግ የይዘት ጥልቀት እና ስፋት ደረጃ እየጨመረ እንደሚሄድ በምዕራፍ ሁለት ተገልጿል።በተማሪው መጽሀፍ ውስጥ በአብዛኛው በተከታታይ ወይም ተደጋግሞ የቀረበው የጽህፈት ክሂል ይዘት አንቀጽ በመሆኑ ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል። አንቀጽን በተመለከተ የቀረበው የጽህፈት ክሂል ይዘት ከአስሩ ምዕራፍ በምዕራፍ 2፣4፣5፣6፣9፣እና 10 (በስድስቱ) የቀረበ ሲሆን መልመጃዎቹም በሠንጠረዥ ሶስት ውስጥ በገጽ ተጠቁመዋል።አንቀጽ ከሌሎቹ ይልቅ በስድስት ምዕራፍ አስር ጊዜ በተከታታይ ወይም ተደጋግሞ መቅረቡ የይዘት ተለጣጣቂነቱን በሚገባ ጠብቆ የቀረበ(የተደራጀ)ሲሆን ከቀላል ወደ ከባድ ከሚታወቅ ወደማይታወቅ ጥልቀቱን እና ስፋቱን እያሳደገ የተደራጀ ወይም የቀረበ መሆኑን እዚህጋ ቢብራራም ከሠንጠረዡ ባጭሩ በተጨማሪ መረዳት ይቻላል።

ስለ አንቀጽ አጻጻፍ ለአብነት ብናይ በምዕራፍ ሁለት ከገፅ 22-23 በቲውተርና በፌስቡክ መካከል ያሉ ልዩነቶችን በማንሳት አንድ አንቀጽ ያለው አነጻጻሪ ጽሁፍ አዘጋጁ በማለት ይጀምራል፡፡ ይህን የጽህፈት መልመጃ ስናይ ርዕሱ ራሱ ተማሪዎች በአሁኑ ሰዓት የሞባይል ቴክኖሎጂን ከመጠቀም አንጻር ከነሱ ጋር አብሮ ያለ በመሆኑ የሚያውቁት ነገር በመሆኑ ሀሳብን አመንጭቶ በንጽጽር ለመጻፍ አይቸገሩም፡፡ በዚሁ ምዕራፍ በድጋሚ በስልክና በበይነመረብ መካከል ያሉ ተመሳሳይነታቸውን በማንሳት አንድ አንቀፅ ያለው ጽሁፍ አዘጋጁ በማለት ተጨማሪ መልመጃ ቀርቧል፡፡ይህ ርዕስ ከመጀመሪያው ርዕስ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ቢመስልም የተወሰነ ጥልቀትና ስፋት አለው፡፡አንቀጽ የመጻፍ ክንውን ከስድስቱ ምዕራፍ አስርጊዜ በተደጋገመው በምዕራፍ ሁለት ወይም ከመጀመሪያ ያለውን ሁለቱን አይተናል ፡፡ስፋትና ጥልቀቱ፣ከቀላል ወደከባድ፣ከሚታወቅ ወደማይታወቅ እያለማመደ ተለጣጣቂነቱን እያደራጀ መሄዱን በመጨረሻው ምዕራፍ አሥር ላይ ያለውን ቀጥሎ እናያለን፡፡እናንተ በመረጣችሁት <u>ርዕስ በምክንያትና ውጤት የአጻጻፍ ስልት አንቀጽ ጻፉ</u> እና ለጓደኞቻችሁ አሳዩ የሚል እናገኛለን፡፡በጅምር ላይ ያለውን አንቀጽ የመጻፍ መለማመጃ ስናይ ተማሪዎቹ ከሚጠቀሙት እና በሚያውቁት ነገር ላይ ተመሳስሎንና ልዩነት እንዲጽፉ ነው የይዘቱ ትዕዛዝ፣የመጨረሻው አንቀጽ መለማመጃ ይዘት ምዕራፍ አሥር ላይ የምናገኘው ስፋትና ጥልቀት ጨምሮ <u>**በምክንያትና ውጤት የአጻጻፍ ስልት አንቀጽ ጻፉ**</u> የሚል ሰፊ እና ጥልቅ እውቀትን የሚጠይቅ መልመጃ እናያለን፡፡አቀራረቡ(አደረጃጀቱ) ከተለጣጣቂነት መርህ አንፃር ትክክል ነው፡፡የሌሎቹንም ምዕራፎች አቀራረብ ወይም አደረጃጀት ለመመልከት በተጨማሪ ሠንጠረዥ ሶስትን መመልከት ይቻላል፡፡

በመቀጠል በአብዛኛው አፅንኦት የተሰጠው የጽህፈት ክሂል ክንውን ድርሰት ነው፡፡ድርሰት ከአንቀጽ በመቀጠል ትኩረት ያገኘ የጽህፈት ክሂል መለማመጃ ሲሆን ከአስሩ ምዕራፍ በምዕራፍ 2፣5፣7፣9 እና 10(በአምስቱ) የቀረበ ሲሆን የይዘት ከቀላል ወደ ከባድ፣ከሚታወቅ ወደ ማይታወቅ የተደራጁ ወይም የቀረቡ ሲሆኑ ይህ ደግሞ የሚያመለክተን ተከታታይነታቸው እና ተለጣጣቂነታቸውን ጠብቀው በአግባቡ የተዘጋጁ መሆናቸውን ነው፡፡ለአብነት ከመጀመሪያ የተጀመረውን መለማመጃ ምዕራፍ ሁለት ላይ ያለውን እንይ፤በኢሜል መልዕክትን መላክና በፖስታ መልዕክትን መላክ አስመልክቶ መረጃዎችን ከድረ ገጾች በመፈለግ በሁለቱ መካከል ያለውን **ተመሳስሎ በማንሳት** ከአንድ ገጽ ያልበለጠ <u>አመዛዛኝ ድርሰት</u> ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ የሚል እናገኛለን፡፡ ከዚህ መለማመጃ አንድ ነገር መገንዘብ እንችላለን ይኸውም ምናልባት አልፎ አልፎ የድሮ ሰው ወይም ከቴክኖሎጂ አጠቃቀም ጋር ያልተገናኘ ሰው ካልሆነ በስተቀር በአሁኑ ጊዜ መልዕክት በፖስታ የሚላላክ ያለ

አይመስለኝም፤ተማሪዎች(ወጣቶች) በአሁኑ ሰዓት መልዕክትን የሚላላኩት በአብዛኛው በኢሜል በመሆኑ ከነሱ ጋር አብሮ ያለ የሞባይል ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ስለሆነ ወይም የሚያውቁት ነገር በመሆኑ ሀሳባቸውን አስፍተው ለመጻፍ ብዙም አይቸገሩም።ቴሌ ብርና ሞባይል ባንክ በተሰኙት አገልግሎቶች መካከል ያሉ **ልዩነቶችን በማንሳት** ከአንድ ገጽ ያልበለጠ <u>**አመዛዛኝድርሰት**</u> ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።ቀጥሎ ያለው መለማመጃ ከመጀመሪያው ይልቅ ትንሽ ጠጠር ይላል፤ህ የሚያመለክተን ከጠባቡ ወደ ሰፊው ወይም ከሚታወቅ ወደ ማይታወቅ መሸጋገሩን ሲሆን ስፋትና ጥልቀትም እየጨመረ መምጣቱን ያስገነዝበናል፡፡ሁሉንም ከመዘርዘር ይልቅ በተጨማሪ በመጨረሻ ላይ ያለውን ወይም የመጽሀፉ የድርሰት ጽህፈት መለማመጃ የሆነውን በምዕራፍ አስር ላይ የሚገኘው ትዕዛዝ በምዕራፍ ሰባት በቀረበው ድርሰት አጻጻፍ መመሪያ መሰረት በሚከተሉት ርዕሶች <u>**አመዛዛኝድርሰትጻፉ**</u> የሚል ነው፤በዚህ መጽሀፍ አቀራረብ (ዝግጅት) ላይ የሚጻፍበት ርዕስ ይለያይ እንጂ ከአራቱ የድርሰት ዓይነቶች ትኩረት የተደረገውና በተደጋጋሚ የተገለጸው <u>**አመዛዛኝ ድርሰት**</u> ነው፡፡በምዕራፍ ሁለት በቀላሉ በተመሳሳይነት እና ልዩነት ላይ ለዛውም በሚያውቁት ነገር ሲጀመር በምዕራፍ አሥር ላይ ግን የይዘት ስፋት እና ጥልቀት ጨምሮ በድርሰት አጻጻፍ መርህ መሠረት ተመርጦ በተሰጣቸው ርዕስ ላይ ብቻ እንዲጽፉ ያስገድዳል፡፡ይኸውም በምዕራፍ ሰባት በቀረበው ድርሰት አጻጻፍ መመሪያ መሰረት በሚከተሉት ርዕሶች <u>**አመዛዛኝ ድርሰት**</u>ጻፉ የሚል ነው፡፡በተጨማሪ በአምስቱም ምዕራፍ ሰበትጊዜ በተደጋጋሚ(በተከታታይ) የቀረበውን መለማመጃ ከመዘርዘር ይልቅ ሠንጠረዥ ሶስትን መመልከት ይቻላል፡፡

ቀሪዎቹ የጽህፈት ክሂል መለማመጃዎች የድግግሞሽ መጠናቸው ይነስ እንጂ ከጽህፈት ክሂል አደረጃጀት እና አቀራረበረ አኳያ መርሁን የተከተሉ ናቸው፤ከመጀመሪያው ጀምሮ ምዕራፉ እና ይዘቱ በጨመረ ቁጥር **ሀያ ዘጠኙም የጽህፈት ክሂል ይዘቶች** ተከታታይነት እና ተለጣጣቂነታቸው እየጨመረ የሚመጡ ናቸው፡፡ለዚሁም መረጃ ሠንጠረዥ ሶስት ላይ ስለሚገኝ በተጨማሪ መመልከት ይቻላል፡፡ሆኖም ግን በአዲሱ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ልክ እንደ አስረኛውም የሥነጽሁፍ ይዘቶች ራሳቸውን ችለው አልተካተቱም (የሉም)፤ቢኖሩ ኖሮ ተጨማሪ የጽህፈት ክሂል መለማመጃ ይሆኑ ነበር፡፡

## 4.4.የመጻፍ ክሂል ከሌሎች ክሂሎች ጋር ያለው አደረጃጀት

**በቅድሚያ የዘጠነኛ እና የአስረኛ ክፍል መጽሀፍት ሁለቱም የተዘጋጁት በአዲስ መልክ ስለሆነ በሚፈለግበት ቦታ ሁሉ በተዛምዶም ሆነ በንጽጽር የምናየው ሁለቱን ብቻ ነው**፡፡በመሆኑም ከተዘጋጁበት ዓላማ እና ግብ አንጻር በሁለቱም ላይ አጭር ዳሰሳ እንደሚከተለው እናያለን፡፡

**የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ** እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መፅሐፍ፣ የተማሪዎችን የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብ እና የመፃፍ ክሂሎች በተደጋጋሚ በማስተማር ክሂላቸው እንዲሻሻል፤ እንዲሁም የስነልሳን እና የስነፅሑፍ ዘርፍ ዕውቀቶችንም በአግባቡ እንዲገነዘቧቸው በሚያስችል መልኩ ተዘጋጅቷል። ከእነዚህ ክሂሎችና ዕውቀቶች በተጨማሪ የቃላት ትምህርትም ራሱን ችሎ እንዲቀርብ ተደርጓል። ይህም ከዚህ በፊት ከነበሩት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ለየት ያደርገዋል። መፅሐፉ የተደራጀው ተፈጥሯዊ የቋንቋ ለመዳ ሂደትን መሰረት በማድረግ ነው። የመልመጃዎቹ አደረጃጀት፡-ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ ክፍል ሁለት፡- ንግግር ፣ክፍል ሦሥት፡- ንባብ፣ክፍል አራት፡- ቃላት ክፍል አምስት፡ ጽህፈት፣ክፍል ስድስት፡ ሰዋስው ሲሆኑ እነዚህ ክፍለ ትምህርቶች በየምዕራፉ እኩል ትኩረት የተሰጣቸው ሲሆን በተቻለ መጠን ሳቢ እና አሳታፊ እንዲሆኑ ጥረት ተደርጓል። በየምዕራፉ መጀመሪያ ላይም የሚጠበቁ ውጤቶች በተማሪው መፅሐፍ የተሰጡ በመሆኑ፤ ተማሪዎች አስቀድመው ምን መማር እና መለማመድ እንዳለባቸው ይጠቁማል።

ከአሥረኛ ክፍል የመማሪያ መጽሐፍ የሚጠበቁ ዋና ዋና ውጤቶችም፤ የማዳመጥ ክሂልን ማዳበር፣የንግግር ክሂልን ማዳበር፣፣ የንባብ ክሂልን ማዳበር፣የጽሕፈት ክሂልን ማጎልበት፣ የቃላት ዕውቀትን ማዳበር እና የሰዋስው ዕውቀትን ማበልጸግ ነው።መጽሐፉ የተሰናዳው ለደረጃው የተዘጋጀውን መርሀትምህርት መሠረት አድርጎ ነው። ተማሪዎች በደረጃቸው የተለያዩ ባህላዊ፣ ሳይንሳዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ አካባቢያዊ፣ ዓለማቀፋዊ፣ ወዘተ.ይዘቶችን/ እሴቶችን በአማርኛ ቋንቋ እንዲገልጹ ስለሚጠበቅ፣ መጽሐፉ ለይዘቶችም ከክሂሎች ያልተናነሰ ትኩረት ሰጥቷል። የዚህም ዋና ዓላማ ተማሪዎች በምንባቦች አማካይነት የንግግርና የማዳመጥ፣ የንባብና የጽሕፈት ክሂሎቻቸውን፤ የቃላትና የሰዋስው ዕውቀታቸውን እንዲያጎለብቱ የሚያደርጋቸው ነው።ከዚህ ዳሰሳ የምንረዳው የጽህፈት ክሂል ክንውኖች የተዘጋጁት ተዋረዳዊም ሆነ ጎናዊ አደረጃጀታቸው ተከታታይ፣ተለጣጣቂ እና የተዛመዱ መሆናቸውን ከላይ በቀረበው አጭር ዳሰሳ መመልከት ተችሏል፤በሁለቱም የዓላማ እና የግብ አንድነት እንዳላቸው መገንዘብ ይቻላል።

## 4.4.1.የጽህፈት ክሂሎቹ ተዋረዳዊ አደረጃጀት

ተዋረዳዊ አደረጃጀት የጽህፈት ክሂል ይዘቶች በቅደም ተከተል በጊዜ ሂደት የሚኖራቸው ግንኙነት የሚገለጽበት ነው።በተጨማሪ ተማሪዎች መማር የሚችሉት እንዴት እንደሆነ በመረዳት አደረጃጀቱን የሚያግዝ ስልት ነው።**ተማሪዎች ሊለማመዱ የሚችሉት ከመጀመሪያው ዕውቀታቸው ጋር ሊገናኝ በሚችል ይዘት መሰረት እደሆነ በምዕራፍ ሁለት ተገልጿል**።ከዚህ አንጻር ተዋረዳዊ አደረጃጀቱን ለምሳሌ የ9ኛክፍሉ ከ10ኛ ክፍሉ ጋር እንዴት እንደተገናኙ በሚቀጥለው በሚቀጥለው ምሳሌ

እንደሚከተለው እናያለን፦በ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ምዕራፍ 4 ገፅ 38 ላይ ከዓረፍተነገሮች ውስጥ የአገባብ ስህተትን ለይቶ ለማውጣት ወይምየዓረፍተነገሩን ቅርጽ አስተካክሎ ለመጻፍ በሚቀጥለው ትዕዛዝ ተገልጿል፣ ከምንባቡ የተወሰዱ ሀረጎችና አረፍተነገሮች ቀርበዋል፡፡በእነዚህ ሀረጎችና **አረፍተ ነገሮች** ውስጥ የምታዩአቸውን ስህተቶች፤በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን ትክክለኛ ቅርፅ በመፈለግ እንደገና **አስተካክላችሁ ፃፉ የሚል ይዘት እናገኛለን፡፡ በተመሳሳይ** ከዚሁ ትዕዛዝ ጋር በጭብጥ አንድ የሆነ የተጻፈበት መንገድ ግን ለየት ያለ ትዕዛዝ በ10ኛ ክፍል መጽሀፍ ምዕራፍ 4 ገፅ 49 ላይ ከዚህ በታች የሚገኙት **አረፍተ ነገሮች** ሰዋስዋዊ ስህተቶች ያሉባቸው ስለሆኑ **አስተካክላችሁ ጻፏቸው** የሚል የዓረፍተነገር ማስተካከያ ይዘት እናገኛለን፡፡በተጨማሪ በ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ በምዕራፍ 9 ገፅ 90 ላይ ስለ ደብዳቤ አጻጻፍ ዓይነቶች የሚገልፅ የሚከተለውን ይዘት እናገኛለን፡፡ **የደብዳቤ አፃፃፍ ሥርዓት** የሰላምታ ደብዳቤ እና የስራ ደብዳቤ ብሎ መመደብ ይቻላል፡፡ሁለቱ የደብዳቤ አይነቶች የየራሳቸው ያፃፃፍ ስርዓት አላቸው፡፡ልክ ይሄንኑ ትዕዛዝ በአጻጻፍ የሚለይ በይዘት ተመሳሳይ የሆነ በ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ በምዕራፍ 1 ገፅ 8 ላይ **የደብዳቤ አጻጻፍ**፣ኢ-መደበኛ (የግል) ደብደቤ፣እና መደበኛ (የሥራ) ደብዳቤ፣የሚል ይዘት እናገኛለን፡፡ስለዚህ በጥቂቱ በነኚህ ምሳሌዎች ብቻ እንኳ ብናይ መጽሀፉ ተዋረዳዊ አደረጃጀቱን አሟልቶ የተዘጋጀ መጽሀፍ ነው፡፡ይህን ሁኔታ በሠንጠረዥ ለአብነት እንደሚከተለው እናያለን፦

## ሦንጠረዥ ስድስት የጽህፈት ክሂሉን ተዋረዳዊ አደረጃጀት የሚያሳይ አጭር መግለጫ

| ዐብይ የጽህፈት ክሂሎች | የዘጠነኛ ክፍል | | | የአሥረኛ ክፍል | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ዝርዝር ይዘቶች | ምዕራፍ | ገጽ | ዝርዝር ይዘቶች | ምዕራፍ | ገጽ |
| ቃላት | የምንባቡን ሀሳብ መሰረት በማድረግ ከዚህ በታች **ከተሰጡት ቃላት** መካከል እየመረጣችሁ በአረፍተነገሮቹ ውስጥ የሚገኙትን ክፍት ቦታዎች በጽሑፍ አሟሉ፡፡ | 1 | 5 | ቀጥሎ በቀረቡት ጽሑፎች ውስጥ **የተሰመረባቸው ቃላት** በሚገኙበት አውድ መሠረት ያላቸውን አገባባዊ ፍችጻፉ፡፡<br>የሚከተሉትን አያያዥ ቃላት ተጠቅማቸሁ አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡ | 3<br>5 | 36<br>57 |
| ዓረፍተ ነገር | ቀጥሎ ከምንባቡ የተወሰዱ ሀረጎችና አረፍተነገሮች ቀርበዋል፡፡በእነዚህ ሀረጎችና **አረፍተ ነገሮች** ውስጥ የምታዩአቸውን ስህተቶች፤በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን ትክክለኛ ቅርፅ በመፈለግ እንደገና **አስተካክላችሁ ፃፉ፡፡** | 4 | 38 | ከዚህ በታች የሚገኙት **አረፍተ ነገሮች** ሰዋስዋዊ ስህተቶች ያሉባቸው ስለሆኑ **አስተካክላችሁ ጻፏቸው፡፡** | 4 | 49 |
| አንቀጽ | በምትኖሩበት አካባቢ ወይም በሀገራችንውስጥበአርአያነታቸው ከሚታወቁ ሴቶች መካከል አንድበመምረጥ ለህብረተሰቡ አርአያ ስለሆኑበት ተግባር ገላጭ **አንቀፅ ፅፋችሁ** ለመምህራችሁ አንብቡ፡<br>ከዚህ በታች ጥቅም ላይ እየዋሉ ካሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ጥቂቶች ቀርበዋል፡፡ ከተዘረዘሩት መካከል አንዱን በመምረጥ እንዴት እንደሚሰራና ለምን ጥቅም እንደሚውል የሚገልጽ **አንቀጽ ጻፉ፡፡**<br>.ከዚህ ቀጥሎ ቅደም ተከተላቸዉ ተዘበራርቆ የተቀመጡትን ዐረፍተ ነገሮች በማስተካከል **አንድ አንቀጽ ጻፉ** ፡፡ | 2<br>3<br>9 | 17<br>27<br>89 | በትዊተርና በፌስቡክ መካከል ያሉ ልዩነቶችን በማንሳት **አንድ አንቀጽ** ያለውአነጻጻሪ ጽሑፍ አዘጋጁ፡፡በስልክና በበይነ መረብ መካከል ያሉ ተመሳሳይነቶችን በማንሳት አንድ **አንቀጽ** ያለው ጽሑፍአዘጋጁ፡፡<br>*መጻፍን ለመማር ጠቃሚ መመሪያ* :-<br>*ሀሳብንማመንጨት፤ሀሳብን መምረጥ፣ቢጋር ማዘጋጀት፣ማርቀቅና መጻፍ፤ጅምር ሀሳብ አሟልታችሁ* **አንቀጽ ጻፉ**፤ከላይ የቀረበውን መመሪያ መሰረት በማድረግ የሚከተለውን ጅምር ሀሳብ አሟልታችሁ **አንቀጽ ጻፉ፡፡** | 2<br>4 | 22<br>46 |
| ድርሰት | በሀገራችን ከሚገኙት አራት ወቅቶች መካከል አንዱን መሰረት በማድረግ የወቅቶቹን ትክክለኛ ባህሪ የሚገልፅ መግቢያ፣ ሀተታ እና መደምደሚያ ያለው **ድርሰት ፃፉ** | 6 | 56 | አራቱ የድርሰት ዓይነቶች፤አንድ ርዕስ መርጣችሁ ከ150 ቃላት ባልበለጠ ተራኪ፣ስዕላዊ፣አስረጂ ወይም አመዛዛኝ **ድርሰት ጻፉ**፤<br>በምዕራፍ ሰባት በቀረበው ድርሰት አጻጻፍ መመሪያ መሰረት በሚከተሉት ርዕሶች አመዛዛኝ **ድርሰት ጻፉ፡፡** | 7<br>10 | 76<br>104 |
| ልቦለድ | .ቀጥሎ **ከአጭር ልቦለዱ የተወሰዱ** ሀረጎችና ዓረፍተ ነገሮች ቀርበዋል፡፡ እነዚህ ሀረጎችና ዓረፍተ ነገሮች የሚያስተላልፉትን ሃሳብ በራሣችሁ አገላለፅ አብራርታችሁ ፃፉ፡፡ | 9 | 88 | ከታች የተዘረዘሩ ቃላትን በመጠቀም ቃላት በልቦለድ ውስጥ ያላቸውን አጠቃቀም ለማሳየት የሚያስችል **አጭር ልቦለድ ጻፉ፡፡** | 4 | 49 |
| ደብዳቤ | **የደብዳቤ አፃፃፍ ሥርዓት** የሰላምታ ደብዳቤ እና የስራ ደብዳቤ ብሎ መመደብ ይቻላል፡፡ ሁለቱ የደብዳቤ አይነቶች የየራሳቸው ያፃፃፍ ስርዓት አላቸው፡፡ | 9 | 90 | **የደብዳቤ አጻጻፍ**፣ኢ-መደበኛ (የግል) ደብደቤ፣እና መደበኛ (የሥራ) ደብዳቤ፣ | 1 | 8 |

### 4.4.2.ጎናዊ አደረጃጀት

ጎናዊ አደረጃጀት፡- የጽህፈት ክሂሉ ከሌሎች ክሂሎች እና የትምህርት ዓነቶች ይዘት ጋር ያላቸውን ግንኙነት የሚመለከት አደረጃጀት ነው፡፡ የክሂሎች የእርስ በርስ ግንኙነት ለተግባቦት ብቃት ወሳኝ ነው፡፡ክሂሎችን በጋራ አቀናጅቶ መገልገል (መጠቀም) እንደተጨማሪ አምስተኛ ክሂል ይቆጠራል፤ ይህ ማለት በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ አንድ ምንባብ ለአንድ የትምህርት ይዘት ብቻ አይዘጋጅም፤የተለያዩ ክሂሎችን ለመስራት ይነበባል የተነበበው ይጻፋል የተጻፈው ከተማሪው ጋር ወይም ከመምህሩ ጋር በሚኖረው የመማር ማስተማር ተራክቦ በመደማመጥ ይናገሩታል፡፡ይህ የክሂሎች ግንኙነት በቀጥታ አንዱን ለማስተማር ተብሎ ቢታሰብ በጎንዮሽ ቅንጅታዊ ሂደትን ይፈጥራሉ፤በተጨማሪ ጽሁፍን ማሳጠር፣ግጥም መጻፍ፣የቃል ጽህፈት፣ማስታወሻ መውሰድ (መያዝ) ተዋረዳዊ ግንኙነትን ይፈጥራሉ፤የሰመረ የተግባቦት ብቃት የሚገኘው ሰፊ ጊዜ በመውሰድ ትርጉማዊ በሆነ መንገድ የክሂሎች ቅንጅታዊ ልምምድ ነው፤በመሆኑም ክሂሎች በግልም ሆነ በጋራ ሊበለጽጉ እንደሚችሉ በምዕራፍ ሁለት ተገልጿል፡፡በመሆኑም በሚቀጥለው ሠንጠረዥ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ከሌሎች የትምህርት እና የክሂል ዓይነቶች ጋር የሚኖራቸውን የጎንዮሽ ግንኙነቱን ለምሳሌ በምዕራፍ ሁለት ገፅ 22 ላይ የማወዳደር እና የማነጻጸር የአጻጻፍ ስልቶች ላይ የቀረበውን ማስታወሻ መሠረት አድርጋችሁ ቀጥሎ ከቀረቡት ተግባራት መካከል አንዱን በመምረጥ ሥሩ የሚለው ትዕዛዝ ለመተግበር ይነበባል፣የተነበበው ይጻፋል፡፡ይህንን እና ሌሎች ምሳሌዎችን እንደሚከተለው በሠንጠረዥ እናያለን፡-

## ሠንጠረዥ ሰባት የጽህፈት ክሂል ከሌሎች ክሂሎች ጋር ያለው ጎናዊ ግንኙነት ወይም አደረጃጀት

| ምዕራፍ | ገጽ | ጽህፈት | ማንበብ | መናገር | ማዳመጥ |
|---|---|---|---|---|---|
| ሁለት | 22 | የማወዳደር እና የማነጻጸር የአጻጻፍ ስልቶች፣ላይ የቀረበውን **ማስታወሻ መሠረት አድርጋችሁ** ቀጥሎ ከቀረቡት ተግባራት መካከል አንዱን በመምረጥ ሥሩ:- በትዊተርና በፌስቡክ መካከል ያሉ ልዩነቶችን በማንሳት አንድ አንቀጽ ያለው አነጻጻሪ ጽሑፍ አዘጋጁ::በስልክና በበይነ መረብ መካከል ያሉ ተመሳሳይነቶችን በማንሳት አንድ አንቀጽ ያለው ጽሑፍአዘጋጁ::በኢሜል መልዕክትን መላክና በፖስታ መልዕክትን መላክ አስመልክቶ መረጃዎችን ከድረ ገጾች በመፈለግ በሁለቱ መካከል ያለውን ተመሳስሎ በማንሳት ከአንድ ገጽ ያልበለጠ አመዛዛኝ ድርሰት ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ::ቴሌ ብርና ሞባይል ባንክ በተሰኙት አገልግሎቶች መካከል ያሉ ልዩነቶችን በማንሳት ከአንድ ገጽ ያልበለጠ <u>**አመዛዛኝ ድርሰት**</u> ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ:: | ✓ | ✓ | ✓ |
| አራት | 49 | ከላይ የቀረበውን መመሪያ መሰረት በማድረግ የሚከተለውን ጅምር ሀሳብ አሟልታችሁ አንቀጽ ጻፉ::ከታች የቀረበውን ግጥም እንደገና በማስተካከል ጻፉ::ከላይ በምዕራፉ የቀረበውን የልቦለድ ምንባብ ጭብጦች/ መልዕክቶች አሳጥራችሁ በሁለት አንቀጽ ጻፉ::ከታች የተዘረዘሩ ቃላትን በመጠቀም ቃላት በልቦለድ ውስጥ ያላቸውን አጠቃቀም ለማሳየት የሚያስችል አጭር ልቦለድ ጻፉ::ከዚህ በታች የሚገኙት አረፍተ ነገሮች ሰዋስዋዊ ስህተቶች ያሉባቸው ስለሆኑ አስተካክላችሁ ጻፏቸው::<br>ከላይ የቀረበውን መመሪያ መሰረት በማድረግ የሚከተለውን ጅምር ሀሳብ አሟልታችሁ አንቀጽ ጻፉ::ከታች የቀረበውን ግጥም እንደገና በማስተካከል ጻፉ::ከላይ በምዕራፉ የቀረበውን የልቦለድ ምንባብ ጭብጦች/ መልዕክቶች አሳጥራችሁ በሁለት አንቀጽ ጻፉ::ከታች የተዘረዘሩ ቃላትን በመጠቀም ቃላት በልቦለድ ውስጥ ያላቸውን አጠቃቀም ለማሳየት የሚያስችል አጭር ልቦለድ ጻፉ::ከዚህ በታች የሚገኙት አረፍተ ነገሮች ሰዋስዋዊ ስህተቶች ያሉባቸው ስለሆኑ አስተካክላችሁ ጻፏቸው:: | ✓ | ✓ | ✓ |
| ስምንት | 96 | ግጥሞችን አሟልታችሁ ጻፉ፤ | ✓ | ✓ | ✓ |

በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የጽህፈት ክሂል ከሌሎች የትምህርት ይዘቶች ጋር የሚኖራቸውን ጎናዊ አደረጃጀት ለአብነት ባጭሩ እንደሚከተለው እናያለን፡-

**ሠንጠረዥ ስምንት የጽህፈት ክሂል ከሌሎች የትምህርት ይዘቶች ጋር ያለው ጎናዊ አደረጃጀት**

| የትምህርት ዓይነቶች | የጽህፈት መልመጃው ይዘቶች | ምዕራፍ | ገጽ |
|---|---|---|---|
| ማህበራዊሰ ይንስ | **ስለእንግዳ አቀባበል በመጠየቅ መጻፍ**፤ሁለት አንቀጽ ድርሰት ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፤ | 5 | 57 |
| | **ባህሎችን አስመልክቶ ከሽማግሌዎች በመጠየቅና መጽሀፍትን በማንበብ አንቀጽ ጻፉ፤ባህላዊ የእርቅ ሥርዓት የሚገልጽ ድርሰት ጻፉ፤የጋብቻ ዓይነቶችን ጻፉ፤ባህላዊ ጋብቻ ሲከናወን** የሚደረጉ ነገሮችን መረጃ ከሰበሰባችሁ በኋላ ሙሉ ሂደቱን የሚገልጽ ጽሁፍ አዘጋጁ፡፡ | 6 | 67 |
| | ስለአካል ጉዳተኞች መረጃ በማሰባሰብ ታሪካቸውን የሚገልጽ ድርሰት ጻፉ፤**ሴቶችን ማስተማር ማህበረሰብን ማስተማር ነው፤በዚህ ሀሳብ ጽሁፍ አዘጋጁ፡፡አካል** ጉዳተኛ የሆኑ ሰዎች አካል ጉዳተኛ ካልሆኑ ሰዎች እኩል ውጤታማ መሆን ይችላሉ በሚል ርዕሰ ጉዳይ ድርሰት ጻፉ፡፡ | 7 | 77 |
| | እያንዳንዳችሁ **በምትኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ ያለውን ማህበራዊ ግንኙነት** በሚመለከት አንቀጽ ጻፉ፡፡ **"በኢትዮጵያ የአስተዳደር ሥርዓቶች ታሪክ** ውስጥ ከሚገኙ ቁልፍ ጽንሰ ሀሳቦች መካከል አንድነትና ብዝሃነት ዋነኞች ናቸው፤" ሲባል ምን ማለት እንደሆነ ለክፍል የሚቀርብ ማብራሪያ ጻፉ፡፡ የድርሰት አጻጻፍ ህግጋትን ተከትላችሁ በአንድነትና ብዝሃነት ላይ ያተኮረ አመዛዛኝ ድርሰት ጻፉ፡፡ ከተዘረዘሩት ቃላት ውስጥ የተወሰኑትን መነሻ በማድረግ አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡ | 9 | 96 |
| የተፈጥሮ ሳይንስ | በትዊተርና በፌስቡክ መካከል ያሉ ልዩነቶችን በማንሳት አንድ አንቀጽ ያለው አነጻጻሪ ጽሑፍ አዘጋጁ፡፡ | 2 | 22---23 |

### 4.4.3. ተተግባሪነት

ለጽህፈት የሚመረጠው ይዘት ተማሪው እንዲለማመደው እና በታቀደው ይዘት ጽሁፋዊ ተግባቦትን በተግባር እንዲገልጽ ጥቅም ላይ የሚውሉ የቋንቋ መዋቅራዊ ቅርጾች እና ቃላት ላይ አጽንኦት ማድረግን ይጠይቃል፡፡በመሆኑም የጽህፈት ክሂል ይዘት ሲመረጥ ሆሄያትን(ፊደላትን)ከመለየት ጀምሮ ቃላት፣ ሀረግ፣ ዓረፍተነገር፣አንቀጽ እያለ ሰፊውን የጽሁፍ አካል ድርሰትን እስከመጻፍ የሚያደርስ በመሆኑ እና ደረጃውን በመጠበቅ በቅደም ተከተል የሚተገበር በመሆኑ ለልምምድ ወይም ለትግበራው ክብደት አይኖርም፡፡ ለተማሪው የሚቀርቡ ይዘቶች መነሻቸውን የሚያውቃቸው እና ከራሱ ልምድ ጋር ግንኙነት ያላቸው ከሆነ በቀላሉ በመጻፍ እንደሚተገብራቸው በምዕራፍ ሀለት ተገልጿል፡፡ከዚህ አንጻር የተዘጋጁት የጽኀፈጽ ክሂሎች እሄንን እንዳሟሉ መፈተሽ ግድ ይላል፡፡በመሆኑም ከጽህፈት ክሂሎቹ ለአብነት የተወሰኑትን እናያለን፡-**በምዕራፍ ሁለት ገጽ 22 ላይ** የማወዳደር እና የማነጻጸር የአጻጻፍ ስልቶች ላይ የቀረበውን ማስታወሻ መሠረት አድርጋችሁ ቀጥሎ ከቀረቡት ተግባራት መካከል አንዱን በመምረጥ ሥሩ፡-

- በትዊተርና በፌስቡክ መካከል ያሉ ልዩነቶችን በማንሳት አንድ አንቀጽ ያለው አነጻጻሪ ጽሑፍ አዘጋጁ፡፡በስልክና በበይነ መረብ መካከል ያሉ ተመሳሳይነቶችን በማንሳት አንድ አንቀጽ ያለው ጽሑፍአዘጋጁ፡፡
- በኢሜል መልዕክትን መላክና በፖስታ መልዕክትን መላክ አስመልክቶ መረጃዎችን ከድረ ገጾች በመፈለግ በሁለቱ መካከል ያለውን ተመሳስሎ በማንሳት ከአንድ ገጽ ያልበለጠ አመዛዛኝ ድርሰት ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡
- ቴሌ ብርና ሞባይል ባንክ በተሰኙት አገልግሎቶች መካከል ያሉ ልዩነቶችን በማንሳት ከአንድ ገጽ ያልበለጠ <u>**አመዛዛኝ ድርሰት**</u> ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

እነኚህን የጽህፈት ክሂል መልመጃዎችን በሁለት መልኩ እናያቸዋለን ፤የመጀመሪያው በአንድ ምዕራፍ ላይ ያሉ ሆነው **ልምምዱ ከጠባቡ ወደ ሰፊው ወይም ከቀላሉ ወደከባዱ ነው** የሆነው፤ይህ ማለት የጽህፈት ትዕዛዙ ወይም የማወዳደሩ እና የማነጻጸሩ ሂደት ከአንቀጽ ወደ ድርሰት የአጻጻፍ ቅደም ተከተል የታቀደ ነው፡፡በመቀጠል ሁሉም ጥያቄዎች ከቴክኖሎጂ አጠቃቀም አንጻር ከግልጽ ወደውስብስብ የተዘጋጀ ነው፡፡ በመሆኑም እነኚህ የጽህፈት ተግባሮች አብዛኛው ተማሪ ወይም ወጣቶች በዕለት ህይወቶቻቸው እየተጠቀሙት ያሉ ነገሮች በመሆናቸው ትዕዛዙ በጥቂቱም ቢሆን ከሚያውቁት ነገር እና ለማወቅ ከሚጓጉት ነገር መነሳታቸው የክሂሉን ተግባራዊነት ያጎለዋል፡፡

**በምዕራፍ ስድስት ገጽ** 67 ባህሎችን አስመልክቶ ከሽማግሌዎች በመጠየቅና መጽሀፍትን በማንበብ አንቀጽ ጻፉ፤ባህላዊ የእርቅ ሥርዓት የሚገልጽ ድርሰት ጻፉ፤የጋብቻ ዓይነቶችን ጻፉ፤ባህላዊ ጋብቻ ሲከናወን የሚደረጉ ነገሮችን መረጃ ከሰበሰባችሁ በኂላ ሙሉ ሂደቱን የሚገልጽ ጽሁፍ አዘጋጁ።እነኚህ መድገም ካልሆነ በስተቀር ልክ እንደላይኛውም የተዘጋጁ ናቸው።ርዕሶቹ ይብዛም ይነስም በማህበረሰቡ ውስጥ በተግባር እተገለጹ ያሉ ጉዳዮች በመሆናቸው ጸሀፊዎቹ(ተማሪዎቹ)ብዙም እንግዳ አይሆኑም፤በመሆኑም ሊተገብሩት ወይም ሊለማመዱት ይችላሉ።

**በምዕራፍ ሰባት ገጽ 78-79 ላይ** ስለአካል ጉዳተኞች መረጃ በማሰባሰብ ታሪካቸውን የሚገልጽ ድርሰት ጻፉ፤ሴቶችን ማስተማር ማህበረሰብን ማስተማር ነው፤በዚህ ሀሳብ ጽሁፍ አዘጋጁ።አካል ጉዳተኛ የሆኑ ሰዎች አካል ጉዳተኛ ካልሆኑ ሰዎች እኩል ውጤታማ መሆን ይችላሉ በሚል ርዕሰ ጉዳይ ድርሰት ጻፉ።የእነዚህ ትዕዛዞች ተማሪዎቹ በሚኖሩበት አካባቢ(በማህበረሰቡ ውስጥ) የሚገኙ እና በከፊልም ቢሆን የሚያውቋቸው ነገሮች በመሆናቸው ለመጻፍ ብዙም አይቸገሩም።

**በምዕራፍ ዘጠኝ ገጽ** 96 እያንዳንዳችሁ በምትኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ ያለውን ማህበራዊ ግንኙነት በሚመለከት አንቀጽ ጻፉ። "በኢትዮጵያ የአስተዳደር ሥርዓቶች ታሪክ ውስጥ ከሚገኙ ቁልፍ ጽንሰ ሀሳቦች መካከል አንድነትና ብዝሃነት ዋነኞች ናቸው፤" ሲባል ምን ማለት እንደሆነ ለክፍል የሚቀርብ ማብራሪያ ጻፉ። የድርሰት አጻጻፍ ህግጋትን ተከትላችሁ በአንድነትና ብዝሃነት ላይ ያተኮረ አመዛዛኝ ድርሰት ጻፉ።ይህ ከተማሪዎቹ አንጻር የርዕሱ አመራረጥ በሚኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ መሆኑ እና በሲቪክስ የተማሩት በመሆኑ አስፍተው ለመጻፍ አይቸገሩም፤በመሆኑም ለተተግባራዊነቱ ጥርጥር የለውም።

**በምዕራፍ አሥር ገጽ** 104 . በምዕራፍ ሰባት በቀረበው ድርሰት አጻጻፍ መመሪያ መሰረት በሚከተሉት ርዕሶች አመዛዛኝ ድርሰት ጻፉ።መምህርና ተማሪ፣ገጠርና ከተማ ፣ትምህርት ቤትና ገበያ፣እናንተ በመረጣችሁት ርዕስ በምክንያትና ውጤት የአጻጻፍ ስልት አንቀጽ ጻፉና ለጓደኞቻችሁ አሳዩ።የነዚህ ርዕስ ትዕዛዝ እስካሁን ካሉት ላቅ ይላል ፤ይህ የሆነበት ምክንያት ደግሞ ለክፍሉ እና ለምዕራፎቹ ማብቂያ ስለሆነ ቅደም ተከተሉን ጠብቆ ከጠባቡ ወደሰፊው የመጣ(የተዘጋጀ) ነው።በመሆኑም ርዕሶቹ ተማሪዎቹን ራሳቸውን ለተግባር ያካተተ እና አብሯቸውም ያለ በመሆኑ እየተለማመዱ ከመጡት የጽህፈት ተግባር አንጻር ሊፈጽሙት ወይም ሊተገብሩት ብዙም አይጨነቁም።

**ሲጠቃለል** ለጽህፈት ክሂሉ የሚመረጠው ይዘት ተማሪው እንዲለማመደው እና በታቀደው ይዘት ጽሁፋዊ ተግባቦትን በተግባር እንዲገልጽ ጥቅም ላይ የሚውሉ የቋንቋ ቅርጾችን ከቃላት ጀምሮ እስከ ድርሰት ድረስ አጽንኦት በመስጠት የጽህፈት ክሂልን አደረጃጀት እንዲሁም አቀራረብን ተከትሎ መዘጋጀቱ ለተተግባራዊነቱ ምቹ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በመቀጠል የጽህፈት ክሂሉን አደረጃጀት እና አቀራረብን በተመለከተ ከመምህራን ጋር በተደረገ የቃለመጠይቅ ምላሽ፣

ጥያቄ 1. የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ያሉ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ዓላማውን ከግብ ያደርሳሉ? ለምላሹ ተጨማሪ ማብራሪያ ቢሰጥ

መምህር 1፡‹‹አዎ ያደርሳሉ፤ተማሪው ያሰበውን በመጻፍ መልዕክቶችን ለማስተላለፍ በጽህፈት ክህሎት የሚያሰሩ ወይም የሚያጽፉ መልመጃዎች በየምዕራፉ ይገኛሉ፡፡››

መምህርት 2፡‹‹አዎ! ተማሪዎች ያሰቡትን በመጻፍ ብቻ ሳይሆን የሚማሩትንም ቢሆን በአግባቡ ጽፈው እንዲማሩ የሚያግዙት ዝግጅቶች አሉበት፡፡››

የሁለቱም መምህራን ምላሽ ሲጠቃለል የጽህፈት ትምህርት ዓላማን መሰረት ያደረገ ተማሪዎች ያሰቡትን ነገር ወይም አመለካከታቸውን በጽሁፍ በመግለጽ ጽሁፋዊ ተግባቦትን እንዲለማመዱ የሚያደርጉ ግብ መቺ ይዘቶች እንዳሉ በሁለቱም ተገልጿል፡፡

ጥያቄ 2.ከጽህፈት ክሂል ይዘቶች አቀራረብ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ እና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአቀራረብ ስልት የቀረቡ ናቸው?ምላሹ ቢብራራ

መምህር 1፡‹‹አዎ የቀረበ ነው፤ ስናስተምር አንዳንድ ምዕራፎች ላይ ተማሪዎቹ በራሳቸው የሚሰሩት (የሚለማመዱት) የጽህፈት መልመጃዎች አጋጥመውናል፡፡››

መምህርት 2፡‹‹አዎ የቀረበ ነው፤በተለይ መልመጃዎችን ስናሰራ ምሳሌዎች እና ሞዴሎችን በማየት የሚያሰሩ መልመጃዎች ስላሉ እነኚህ አጠቃላይ ከሆነ ይዘት ወደ ዝርዝር እንደሆነ ጥቆማ ይሰጠናል፡፡››

ምላሹ ሲተነተን ጽህፈትን ሲማሩም ሆነ መልመጃዎችን ሲሰሩ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡትን የጽህፈት ክሂል ይዘቶችን ተማሪዎች በምሳሌዎች እየታገዙ መልመጃዎችን ከተለማመዱ በኋላ የጽህፈት ሥርዓትን በራሳቸው ጥረት እንዲተገብሩት የሚያደርግ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ

የሆነ የይዘት አደረጃጀት እንዳለ ነው፤በተጨማሪ የአማርኛ ቋንቋ የጽህፈት ህግን በመመርኮዝ የተዘጋጁትን መልመጃዎች በመለማመድ እንዲጽፉ የሚያደርጉ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የቀረቡ ይዘቶች መኖራቸውን ከምላሻቸው እንረዳለን፡፡

ጥያቄ 3. የጽህፈት ክሂል አቀራረቡ ውጤት ተኮር እና ሂደት ተኮር አቀራረብን አካቷል? ምላሹ ትንሽ ቢብራራ

መምህር 1፡‹‹አካቷል፤ሁለቱም በመጽሀፉ የጽህፈት መልመጃዎች ውስጥ ተካተው ይገኛሉ ለምሳሌ በውጤት ተኮር አቀራረባ ከቃላት አቀነጃጀት ጀምሮ እስከ አንቀጽ አጻጻፍ ድረስ ጽህፈታቸውን ያበለጽጋሉ፤፡፡››

መምህርት2፡‹‹አካቷል ፤ስናስተምራቸው ወይም ሥናጽፋቸው የመልመጃዎቹ ትዕዛዝ እና ይዘቱ ይጠቁመናል፤በመሆኑም በመማር ማስተማር ሂደት በጽህፈት ጊዜ ከውጤት ይልቅ በሂደት ላይ ትኩረት የሚያደርጉ መልመጃዎችና ይዘቶች አሉ ፡፡››

ሁለቱም መምህራን የመለሱት ምለሽ የተናገሩበት የአገላለጽ ስልት የተለያየ ቢመስልም ጭብጡ አንድ ዓይነት ነው፡፡ስናጠቃልለው በመጽሀፉ ዝግጅት ውስጥ ሁለቱም(ውጠት ተኮር እና ሂደት ተኮር) አቀራረብ እንዳለጠቁመውናል፡፡

ጥያቄ 4.የጽህፈት ክሂሎች የይዘት አደረጃጀት ተከታታይነት እና ተለጣጣቂነትን መርህ አሟልቶ የተዘጋጀ ነው?

መምህር1፡‹‹ያሟላል፤በተለይ ከ9ኛ ክፍል ጋር ተያያዥነት አላቸው፤ለምሳሌ ዐረፍተነገር ማስተካከል፣አንቀጽ መጻፍ፣ ድርሰት መጻፍ፣ደብዳቤ መጻፍ በ10ኛ ክፍል ላይ ተደግመዋል፤ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር በተለይ ከማህበራዊ ሳይንስ ጋር ይገናኛሉ፡፡››

መምህርት2፡‹‹ያሟላል፤ከታችኛው ክፍል ተያይዞ የመጡ የጽህፈት ክሂል መልመጃዎች አሉ፤ በተጨማሪ ከአማርኛ ትምህርቶች ጋር የህብረተሰብ ትምህርቶች ይገናኛሉ፡፡››

የመምህራኑ ምላሽ የይዘት ተከታታይነትንና ተለጣጣቂነትን እንዳሟላ ነው ይኸውም ከታችናዎቹ ክፍሎች(9ኛ ክፍል)ተያይዘው የመጡ ቀጣይነት ያላቸው የጽህፈት ክሂል ይዘቶች እንዳሉ ነው፤በተጨማሪ ከአማርኛ ቋንቋ ጋር የጎንዮሽ ግንኙነት ያላቸው ይዘቶች ነበሩ ፤ለምሳሌ

በማህበረሰቡ ውስጥ የሚገኙትን ባህላዊ የሆኑ ነገሮችን፤ቴክኖሎጂዎችን ስለሚነካካ ተከታታይነትም ሆነ ተለጣጣቂነት ያላቸው የጽህፈት ይዘቶች እንዳሉ ነው፡፡

ጥያቄ 5. የጽህፈት ክሂል መልመጃዎች ጎናዊ እና ተዋረዳዊ የሆነ ግንኙነት አላቸው?

መምህር1፡‹‹አዎ አላቸው፤ያው የጽህፈት ክሂል ይዘቶቹ ከታችኛዎቹ ክፍሎች ስፋት እና ጥልቀት ጨምረው ተያይዘው የመጡ ናቸው፡፡››

መምህርት2፡ከ9ኛ ክፍል ተያይዘው የመጡ መልመጃዎች አሉ ግን ትንሽ ከበድ ይላሉ፤››

ምላሻቸው የጋራ ሲደረግ የጽህፈት ክሂል ይዘቶቹ ከ(9ኛው)ክፍል ስፋትና ትልቀት ቸምሮ በ10ኛው ክፍል ላይ ጎናዊውም ተዋረዳዊውም ዝግጅቶች እንዳሉ ነው፡፡

ጥያቄ 6.ለጽህፈት የተመረጡት መልመጃዎች ተተገባሪ ናቸው?ምላሹ በብራራ

መምህር1፡‹‹አዎ፤በመጽሀፉ ዝግጅት ተማሪዎች በራሳቸው ምሳሌ እያዩ የሚሰሩት አለ፣ከጓደኞቹ እና ከመምህሩ ጋርም የሚሰሩት መልመጃዎች አጋጥመውኛል ስለዚህ አስቸጋሪ የሆነ ከተማሪው አቅም በላይ ሆኖ ያስቸገረ የጽህፈት መልመጃ አላጋጠመኝም፡፡››

መምህርት 2፡‹‹አዎ፤በተለይ ሰፋ ባለ ምሳሌ የተሰጡ መልመጃዎችና በቡድንና በጥንድ እንዲሰሩ የተዘጋጁት መልመጃዎች ተማሪዎቹ በራሳቸው የሚሰሩ ዓይነት ስለሆኑ ለመተግበር የማያስቸግሩ ናቸው፡፡

ምላሹ ሲጠቃለል፡-የጽህፈት ትምህርትን ይዘት ከታችኛዎቹ (9ኛ) የክፍል ደረጃ ጀምሮ አሁን እስካለበት (10ኛ) ክፍል ድረስ ሳይቋረጥ በጽህፈት ይዘትነት የቀጠሉ አሉ፤ ከቀላል ወደ ከባድ የታለሙ ይሁኑ እንጂ ተማሪው እንዲሰራ ታስቦ በምሳሌ እና በሞዴል (ሰርቶ በማሳየት የተዘጋጁ ዝግጅቶች ስላሉ ተማሪዎች በቀላሉ ይሰሩታል ወይም ይረዱታል ተብሎ ይታሰባል፡፡

ጥያቄ 7. የጽህፈት መልመጃዎቹ ተማሪዎች ለብቻቸው እና ከመምህሩ ጋር ለመስራት የሚያስስችሉ ናቸው?

መምህር 1፡‹‹አዎ ከመምህር ጋር የሚያሰሩ ናቸው፡፡የመጽሀፉ ዝግጅት በአብዛኛው ተማሪን ማዕከል አድርጎ የተዘጋጀ ቢሆንም የመምህሩን ምሪት የሚፈልጉ አሉ፡፡››

መምህርት 2፡አዎ ሁለቱንም መምህሩንና ተማሪውን ማዕከል ያደረጉ ናቸው፡፡››

ከምላሹ የምንረዳው ተማሪዎች ጽህፈትን በተለያዩ ስልቶች እና መርሆዎች እንዲማሩ የተደረገውን ቀደም ሲል በሌሎች መጠይቆች ምላሽ ተገኝቶበታል፤ቢሆንም እዚህጋ በተጨማሪ አፅንዖት ለመስጠት ዝግጅቱ በአብዛኛው ተማሪ ተኮር እንደሆነ እና ምህሩንም በመሪነት የሚጋብዙ የጽኁፈጽ ክሂል ይዘቶች እንዳሉ ነው፡፡

ጥያቄ 8.አጠቃላይ የጽህፈት ክሂሉ ይዘቶች የተማሪውን ዳራ ያገናዘቡ ናቸው ?

መምህር1፡‹‹አዎ ከተማሪው ዕድሜ ጋር እና በአብዛኛው ከክፍሉ ደረጃ ጋር የተመጣጠኑ ናቸው፡፡››

መምህርት2፡‹‹አዎ፤ከማህበረሰቡ፣ከአካባቢው በመገንዘብ ከባህሉ፣ከቴክኖሎጂ ጋር ባለውግንኙነት የሚሰሩዋቸው መልመጃዎች ስላሉ ከተማሪው ዳራ ጋር ቅርበት ያላቸው ናቸው፡፡

የመጠይቁ ምላሽ ሲጠቃለል ባጭሩ የተማሪውን ዳራ እንዳካተተ ሲያስተምሩ ባጋጠማቸው በተለያዩ ምሳሌዎች አስረድተዋል ፡፡**በተጨማሪ (አባሪ 2 እና 3 ይመልከቱ)**

## 4.4.የውጤት ማብራሪያ

ይህ ጥናት ዋና ዓላማ አድርጎ የተነሳው ከዚህ በኋላ በመማር ማስተማር ሥራ ላይ በሚውለው በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር የመጀመሪያ እትም 2014 ዓ.ም የሆነው አማርኛን እንደፌዴራል ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀውን የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መጽሐፍ ውስጥ የመፃፍ ክሂልን የይዘት አደረጃጀት መገምገም ነው፡፡ በመሆኑም የጥናቱ ትኩረትከ2 015ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ በሚውለው በአዲሱ የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መጽሐፍ ውስጥ የመፃፍ ክሂልን የይዘት አደረጃጀት ለመገምገም ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀም ለግምገማው በሚዘጋጁት መርሆዎች አማካይነት መረጃዎቹ ገላጭ የምርምር ስልትን በመጠቀም ተብራርተዋል፡፡ለጥናቱ ደጋፊ እና ፍንጭ ሰጪ የሆኑ ክለሳ ድርሳናት ተጠቅሰዋል፡፡

ዐብይ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሆኖ ያገለገለው የሰነድ ግምገማ ነው፡፡የተገመገመው ሰነድ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር የመጀመሪያ እትም 2014 ዓ.ም የሆነው አማርኛን እንደፌዴራል ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀውን የ10ኛ ክፍል የአማርኛ

መጽሐፍ ላይ ሲሆን ትኩረቱ የመጻፍ ክሂል ይዘት ላይ ብቻ ሆኗል፤በመቀጠልም የመምህራን ቃለ-መጠይቅ ሲሆን ለጥናቱ በተመረጠው ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን በቃለመጠይቅ መረጃ ሰጥተዋል፡፡

መረጃው የተተነተነበት ዘዴ የጥናቱን ዋና ዓላማ መሠረት በማድረግ የመፃፍ ክሂልን የይዘት አደረጃጀት ለመገምገም ለመተንተን በምዕራፍ ሁለት ስለ ጽህፈት ክሂል የተጠቀሱትን ጽንሰ ሀሳቦች መሰረት በማድረግ በመጽሀፉ ዝግጅት ውስጥ የመጻፍ ክሂልን የይዘት አደረጃጀት መስፈርትን፣የጽህፈት ክሂል መልመጃዎች ተዋረዳዊ እና ጎናዊ አደረጃጀቶችን፣የጽህፈት ክሂል አቀራረብን(ቅድመ ጽህፈት፣ጊዜ ጽህፈት እና ድህረ ጽህፈትን)ለጥናቱ መሠረት በተደረገው ዓይነታዊ የምርምር ዘዴ በመፈተሽ የሚገኙትን መረጃዎች በዓነት በዓይነት ለይቶ በገላጭ ስልት ተተንትነዋል፤ በሁለተኛ ደረጃ ለሙከራ በተመረጠው ትምህርት ቤት በአሥረኛ ክፍል ላይ በማስተማር የሚገኙ መምህራን በቃለ-መጠይቅ የሰጡት መረጃ እንደየአጠያየቁ ተገልጿል፡፡

ዋናው የመጽሀፉ ይዘት ከመተነተተኑ በፊት የመጽሀፉ አጠቃላይ ገጽታ እና የቋንቋ ትምህርትን ዓላማ መሠረት በማድረግ የተዘጋጁ አጠቃላይ የመጽሀፉ ይዘት በአጭሩ ተቃኝቷል፡፡ለአብነት በጥቂቱ ለ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበው በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር የመጀመሪያ እትም 2014 ዓ.ም የሆነው አማርኛን እንደፌዴራል ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀውን የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መጽሐፍ አሥር ምዕራፎች አሉት፡፡መጽሀፉ በመጠን ለአያያዝ አመቺ እንዲሆን ተደርጎ የተዘጋጀ ነው፡፡በመጽሀፉ ውስጥ የትምህርት ይዘቶችን ዓላማን ግብ ለመምታት የሚያደርሱ ዐቢይና ንዑሳን የትምህርት ልምዶች ይገኙበታል፡፡የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች ዋናዋናዎቹ ሁለት ሲሆኑ እነርሱም አራቱ ክሂሎች እና ሁለቱ የዕውቀት ዘርፎች መሆናቸው ተገልጿል፤ይሁንና በመጽሀፉ ውስጥ የእነዚህን አጠቃላይ አደረጃጀት በአስሩም ምዕራፍ ውስጥ እንዴት እንደተካተቱ መጠናቸው እና ዓይነታቸው በሠንጠረዥ እና በገለጻ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያ እና አስተያየት

## 5.1.ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ አዲሱ የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መጽሐፍ ውስጥ የመፃፍ ክሂልን የይዘት አደረጃጀት መገምገም ሲሆን በዚህ ዐቢይ ዓላማ ሥር ለሚገኙት ዝርዝር ዓላማዎች ጭምር መፍትሄ(መልስ) ማግኘት ነው፡፡ግምገማውን ወይም ፍተሸውን ለማከናወን መጽሀፉን በማንበብ የሚገኙትን መረጃዎች በምዕራፍ ሁለት ላይ በተጠቀሱት የመገምገሚያ ጽንሰሀሳቦችን መሠረት በማድረግ በዓይነታዊ የምርምር ዘዴ እና በገላጭ ስልት ቀርቧል፡፡

ለ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበው አዲሱ የአማርኛ ቋንቋ መጽሀፍ አሥር ምዕራፎች አሉት፤በአስሩም ምዕራፍ ውስጥ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች በተለያየ የአቀራረብና የአደረጃጀት መርህ ተዘጋጅተዋል፡፡

በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የጽህፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ እና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአቀራረብ ስልት ተማሪዎች በምሳሌዎች እየታገዙ የጽህፈት ክሂል ተግባራትን እንዲተገብሩ የሚያደርጉ የይዘት አደረጃጀቶች እንዳሉ አይተናል፡፡በአጠቃላይ በተደረገው የሰነድ ግምገማ ወይም ፍተሸ በመጽሀፉ ውስጥ የተገለጹት ከዝርዝር ወደአጠቃላይ የቀረቡ የጽህፈት ክሂል የትምህርት ይዘቶች በተለያየ የአቀራረብ ስልት እንደቀረቡ ተገንዝበናል፡፡

በመጽሀፉ ውስጥ ለሂደት ተኮር እና ውጤት ተኮር የጽህፈት ክሂል አቀራረብ ለሁለቱም የተሰጠውን አፅንኦት በመረጃው ትንታኔ አይተናል፡፡

የጽህፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ተከታታይነት በአንድ የክፍል ደረጃ የቀረበው የጽህፈት ክሂል የትምህርት ይዘት በዚያው ክፍል አልፎ አልፎ በየምዕራፎቹ ካልሆነም በተከታይ የትምህርት እርከን እየተደጋገመ የሚገኝ መሆኑን ቀደም ሲል ተመልክተናል፡፡ተለጣጣቂነት በአንድ የክፍል ደረጃ ለዛውም በተከታታይ የመማሪያ የክፍል ደረጃዎች ላይ የሚገኝ የትምህርት ልምድን(ይዘት)መነሻ በማድረግ የይዘት ጥልቀት እና ስፋት ደረጃ እየጨመረ እንደሚሄድም ተገንዝበናል በግምገማው በመጽሀፉ ውስጥ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች 29 ጊዜ በተለያዩ የመማር ማስተማር ርዕሶች ወይም ክንውኖች እንደቀረቡ ተገልጿል፡፡

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር የመጀመሪያ እትም 2014 ዓ.ም የሆነው አማርኛን እንደፌዴራል ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀውን የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መጽሐፍ ዝግጅት ውስጥ የጽህፈት ክሂል አቀራረብ እና አደረጃጀት መርህን እና መስፈርትን የተከተለ መሆኑን ከመረጃዎቹ መረዳት ተችሏል፡፡

## 5.2.አስተያየት

በማጠቃለያ ላይ የተገለጹትን የጥናቱን ውጤቶች መሠረት በማድረግ አስተያየት እንደሚከተለው ተሰንዝሯል፡፡

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር የመጀመሪያ እትም 2014 ዓ.ም የሆነው አማርኛን እንደፌዴራል ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀውን የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የጽህፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ከአቀራረብ አንጻር ከአጠቃላይ ወደዝርዝር እና ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ቀርቧል፤ቢሆንም የይዘት አቀራረቡ በአብዛኛው ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝዘር ሳይሆን ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የቀረበበት መንገድ ላቅ ያለ ይመስላል፤ከውጤት እና ሂደት ተኮር አቀራረብ ደግሞ በውጤት ተኮር ሂደት የቀረቡ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች በርከት እንደሚሉ ተመልክተናል፤ሆኖም ተማሪዎች የጽህፈት ክሂሉን ተግባቦታዊ በሆነ ስልት እንዲለማመዱና እንዲጠቀሙ የሚያደርጉ ተግባራት ተስተውለዋል፡፡

በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የጽህፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ውስጥ ተከታታይነት በአንድ የክፍል ደረጃ የቀረበው የጽሀፈት ክሂል ይዘት በዚያው ክፍል አልፎ አልፎ በየምዕራፎቹ ካልሆነም በተከታይ የትምህርት እርከን እየተደጋገመ የሚገኝ መሆኑን ቀደም ሲል ተመልክተናል፡፡በመሆኑም በዚህ ጥናት፣ ፍተሸ ወይም ግምገማ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር የመጀመሪያ እትም 2014 ዓ.ም የሆነው አማርኛን እንደፌዴራል ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀውን የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መጽሐፍ ውስጥ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች በአሥሩም ምዕራፍ በተደጋጋሚ ቀርበዋል፤ ተለጣጣቂነት በአንድ የክፍል ደረጃ ለዛውም በተከታታይ የመማሪያ የክፍል ደረጃዎች ላይ የሚገኝ የትምህርት ልምድን(ይዘት)መነሻ በማድረግ የይዘት ጥልቀት እና ስፋት ደረጃ እየጨመረ የሚሄድ መሆኑን ከዘጠነኛ ክፍል ጋር በማመሳከር ታይቷል፡፡

በመጨረሻም በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር የመጀመሪያ እትም 2014 ዓ.ም የሆነው አማርኛን እንደፌዴራል ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀውን የ10ኛ ክፍል

የአማርኛ መጽሐፍ  ውስጥ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች 29 ጊዜ በተለያዩ የመማር ማስተማር  ርዕሶች ወይም ይዘቶች  እንደቀረቡ ተገልጿል፤ነገርግን በአብዛኛው የክሂሉ ትኩረት አንቀጽን በማነጻጸር እና በማወዳደር መጻፍ፣ከድርሰት ደግሞ በአመዛዛኝ  ላይ በተደጋጋሚ እንደቀረበ በመረጃ ትንተና ላይ ታይቷል፤ ይህ ደግሞ ለተማሪው አሰልቺ የሆነ ተደጋጋሚ ትዕዛዝና ይዘት ይሆናል ተብሎ ይታሰባል፤በመሆኑም በተለያዩ የትምህርት ልምዶች እና ዘዴዎች ቢቀርቡ፣

በመጨረሻ ግን በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር የመጀመሪያ እትም 2014 ዓ.ም የሆነው አማርኛን እንደፌዴራል ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀውን የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መጽሐፍ ዝግጅት ውስጥ የጽህፈት ክሂል አቀራረቦች፣እና አደረጃጀቶች መርህን  የተከተሉ በመሆናቸው ጠንካራ ጎናቸው ስለሚያመዝን  ለሚቀጥለውም ጊዜ አዘገጃጀቱ በሌሎቹም የመጽሀፍት ዝግጅቶች ላይ ቢደገም፣

# ዋቢ መጽሀፍት

**ማረው አለሙ**(1996)፡፡ በሳል ድርስት ማስተማሪያ፡፡አዲስ አበባ ፣ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

**ተስፋዬ ሸዋዬ**(1981)፡፡ስነልሳንና ቋንቋን ማስተማር ፡፡አዲስ አበባ፣አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ፣(ያልታተመ)

**ትምህርት ሚኒስተር**(2014)፡፡አማርኛ ቋንቋ መጽሐፍ አስረኛ ክፍል የተማሪው መጽሐፍ፡፡አዲስ አበባ፣ትምርት ሚኒስተር

**ትምህርት ሚኒስተር**(2014)፡፡አማርኛ ቋንቋ መጽሐፍ አስረኛ ክፍል የምህሩ መምሪያ፣አዲስ አበባ ፣ትምህርትሚኒስተር

**ያለዉ እንዳወቅ** (2009)፡፡የምርም መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር፡፡ባህርዳር፣ባህርዳር ዩንቨርሲቲ፡፡

**Attkins.J.and et Al.**(1996)skill developments methodology Addis Ababa University press.

**Breen, M. (**1984) Processes in syllabus design. In C. Brumfit (ed.) *General English Syllabus Design*. Oxford: Pergamon Press.

**Brown,H.**(2001).Teachingby Principle:An Interactive Approach to Languag Pedagogy.(2nded ) NewYork:Addison wesly Longman.

**Byrne, D.** (1988). *Teaching Writing Skills.*London: Longman.Flower, L. S.

**Cunningsworth,A.** (1995)*Choosing Your Coursebook*. Oxford: Heinemann.

**Dubin,F.and Olishtain,E.**(1986)Course Design.Cambride:Cambridge University Press.

**Grant, N** (1987).Making the Most of Your Text Book. London Longman.

**Heaton, JB** (1991) *Writing English Language Test*. New York : Edinburg Gate.

**Larsen-Freeman,D. (1991).** Teaching Grammar. In Celcemurcia; M. (ed).Teaching English as second or Foreign Language. Boston: Heinle and Heinle Publishers.

**Lawrence, W. P. W.**(2011).Textbook Evaluation:A Framework for Evaluating the Fitness of the Hong Kong New Secondary School (NSS)Curriculum. M.A.thesis,City University of Hong Kong,China,Hong Kong.

**Nunan,D.**(1988TheLearner-Centred Curriculum.Cambridge:Cambridge University Press.

**Nunan,D.**(1999).Second Language Teaching and Learning.USA: Henle Publishers.

**Raimes,A.**(1983).Techniques in Teaching Writing. Oxford:Oxford University Press.

**Rechards,J.C.**(1990)The Language Teaching Matrix.Cambridge:Cambridge University Pres.

**Reid ,J.M**(1993) Teaching ESL Writing :New Jersey:Prentice hallreagents.

**Sheldon, L.E.** (1988). Evaluating ELT textbooks and materials. *ELT Journal,* 42 (4), pp.237-246 [Electronic version]

**Taba,Hilde** (1962)Currculum Development:Theory and Practice New York: Harcourt BraceJovanovich Inc.

**Tangerpermpoon, T.**(2009) Integrated approaches to improve students writing skill for Englishmajor students.ABAC Journal, 28 (2), 1-9

**Tyler,R.**(1949)Basic Principles of Curriculum and Instruction.NewYork: Harcourt Brace.

**Tyler,R.W.**(1950) Basic Principles of Curriculum and Instruction.Chicago:The University of Chicago Press.

**Ur.P.**(1991) Acourse in language teaching: practice theory. Cambridge: Cambridge university press.

**Yalden,J.**(1987) Principles of course Design for Language Teaching, Cambridge: Cambridge University press.

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ

### አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ

### የሂውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅየአማርኛ ቋንቋ ሥነጹሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

### ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቀረቡ ቃለመጠይቆች

የመጠይቁ ዓላማ፡-ጥናቱ ትኩረት አድርጎ የተነሳው አዲሱ የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መጽሐፍ ውስጥ የመፃፍ ክሂልን የይዘት አደረጃጀት መገምገምን ነው ፤ይህን ዓላማ መሠረት በማድረግ የአማርኛ ቋንቋ ለሚያስተምሩ መምህራን የቀረበ ቃለመጠይቅ ነው፡፡

1.የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ያሉ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ዓላማውን ከግብ ያደርሳሉ?ለምላሹ ተጨማሪ ማብራሪያ ቢሰጥ

2.ከጽህፈት ክሂል ይዘቶች አቀራረብ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ እና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአቀራረብ ስልት የቀረቡ ናቸው?

3.የጽህፈት ክሂል አቀራረቡ ውጤት ተኮር እና ሂደት ተኮር አቀራረብን አካቷል ?ምላሹ ትንሽ ቢብራራ

4.ከጽህፈት ክሂሎች የይዘት አደረጃጀት ተከታታይነት እና ተለጣጣቂነትን አሟልቶ የተዘጋጀ ነው?

5.የጽህፈት ክሂል መልመጃዎች ጎናዊ እና ተዋረዳዊ የሆነ ግንኙነት አላቸው?

6.ለጽህፈት የተመረጡት መልመጃዎች ተተገባሪ ናቸው?ምላሹ ቢብራራ

7.የጽህፈት መልመጃዎቹ ተማሪዎች ለብቻቸው እና ከመምህሩ ጋር ለመስራት የሚስችሉ ናቸው?

8.አጠቃላይ የጽህፈት ክሂሉ ይዘቶች የተማሪውን ዳራ ያገናዘቡ ናቸው ?

## አባሪ ሁለት

### የሂውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ሥነጹሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የአማርኛ ቋንቋ ለሚያስተምሩ መምህራን የቀረበ ቃለመጠይቅ

የቃለ-መጠይቁ ምልልሶች ቅጂ

ከመምህር አንድ ጋር የተደረገ ምልልስ

ግንቦት 01/09/2015

የትምህርት ቤቱ ስም  ዱራሜ ህዳሴ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ

ሰዓት 9.00–9.30

በዚህ ሰዓት የተሰራው ሥራ፡-ትውውቅ፣የቃለ-መጠይቁ ዓላማ አዲሱ የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መጽሀፍ ዝግጅት ላይ የጽህፈት ክሂል አደረጃጀትን መገምገም እንደሆነ ገልጬ እሄንን በተመለከተ ያዘጋጀሁትን ዐብይ ጥያቄዎች ለግንዛቤ በንባብ ካሰማሁ በኋላ አያንዳንዱን ጥያቄ ተራ በተራ መጠየቅ ጀመርኩ፡፡

ጥያቄ 1. የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ያሉ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ዓላማውን ከግብ ያደርሳሉ? ለምላሹ ተጨማሪ ማብራሪያ ቢሰጥ

መምህር 1፡‹‹አዎ ያደርሳሉ፤ተማሪው ያሰበውን በመጻፍ መልዕክቶችን ለማስተላለፍ በጽህፈት ክህሎት የሚያሰሩ ወይም የሚያጽፉ መልመጃዎች በየምዕራፉ ይገኛሉ፡፡››

ጥያቄ 2.ከጽህፈት ክሂል ይዘቶች አቀራረብ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ  እና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአቀራረብ ስልት የቀረቡ ናቸው?ምላሹ ቢብራራ

መምህር 1፡‹‹አዎ የቀረበ ነው፤ ስናስተምር አንዳንድ ምዕራፎች ላይ ተማሪዎቹ በራሳቸው የሚሰሩት (የሚለማመዱት) የጽህፈት መልመጃዎች አጋጥመውናል፡፡››

ጥያቄ 3.የጽህፈት ክሂል አቀራረቡ ውጤት ተኮር እና ሂደት ተኮር አቀራረብን አካቷል ? ምላሹ ትንሽ ቢብራራ

መምህር 1፡‹‹አካቷል፤ሁለቱም በመጽሀፉ የጽህፈት መልመጃዎች ውስጥ ተካተው ይገኛሉ ለምሳሌ በውጤት ተኮር አቀራረባ ከቃላት አቀነጃጀት ጀምሮ እስከ አንቀጽ አጻጻፍ ድረስ ጽህፈታቸውን ያበለጽጋሉ፤፡፡››

ጥያቄ 4.የጽህፈት ክሂሎች የይዘት አደረጃጀት ተከታታይነት እና ተለጣጣቂነትን መርህ አሟልቶ የተዘጋጀ ነው?

መምህር1፡‹‹ያሟላል፤በተለይ ከ9ኛ ክፍል ጋር ተያያዥነት አላቸው፤ለምሳሌ ዐረፍተነገር ማስተካከል፣አንቀጽ መጻፍ፣ ድርሰት መጻፍ፣ደብዳቤ መጻፍ በ10ኛ ክፍል ላይ ተደግመዋል፤ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር በተለይ ከማህበራዊ ሳይንስ ጋር ይገናኛሉ፡፡››

ጥያቄ 5. የጽህፈት ክሂል መልመጃዎች ጎናዊ እና ተዋረዳዊ የሆነ ግንኙነት አላቸው?

መምህር1፡‹‹አዎ አላቸው፤ያው የጽህፈት ክሂል ይዘቶቹ ከታችኛዎቹ ክፍሎች ስፋት እና ጥልቀት ጨምረው ተያይዘው የመጡ ናቸው፡፡››

ጥያቄ 6.ለጽህፈት የተመረጡት መልመጃዎች ተተገባሪ ናቸው?ምላሹ በብራራ

መምህር1፡‹‹አዎ፤በመጽሀፉ ዝግጅት ተማሪዎች በራሳቸው ምሳሌ እያዩ የሚሰሩት አለ፣ከጓደኞቹ እና ከመምህሩ ጋርም የሚሰሩት መልመጃዎች አጋጥመውኛል ስለዚህ አስቸጋሪ የሆነ ከተማሪው አቅም በላይ ሆኖ ያስቸገረ የጽህፈት መልመጃ አላጋጠመኝም፡፡››

ጥያቄ 7. የጽህፈት መልመጃዎቹ ተማሪዎች ለብቻቸው እና ከመምህሩ ጋር ለመስራት የሚያስችሉ ናቸው?

መምህር 1፡‹‹አዎ ከመምህር ጋር የሚያሰሩ ናቸው፡፡የመጽሀፉ ዝግጅት በአብዛኛው ተማሪን ማዕከል አድርጎ የተዘጋጀ ቢሆንም የመምህሩን ምሪት የሚፈልጉ አሉ፡፡››

ጥያቄ 8.አጠቃላይ የጽህፈት ክሂሉ ይዘቶች የተማሪውን ዳራ ያገናዘቡ ናቸው ?

መምህር1፡‹‹አዎ ከተማሪው ዕድሜ ጋር እና በአብዛኛው ከክፍሉ ደረጃ ጋር የተመጣጠኑ ናቸው፡፡››

# አባሪ ሶስት

የሂውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ሥነጹሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የአማርኛ ቋንቋ ለሚያስተምሩ መምህራን የቀረበ ቃለመጠይቅ

የቃለ-መጠይቁ ምልልሶች ቅጂ

ከመምህርት ሁለት ጋር የተደረገ ምልልስ

ግንቦት 01/09/2015

የትምህርት ቤቱ ስም  ዱራሜ ህዳሴ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ

ሰዓት 9.40–10፡15

በዚህ ሰዓት የተሰራው ሥራ፡-ትውውቅ፣የቃለ-መጠይቁ ዓላማ አዲሱ የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መጽሀፍ ዝግጅት ላይ የጽህፈት ክሂል አደረጃጀትን መገምገም እንደሆነ ገልጬ እሄንን በተመለከተ ያዘጋጀሁትን ዐብይ ጥያቄዎች ለግንዛቤ በንባብ ካሰማሁ በኋላ አያንዳንዱን ጥያቄ ተራ በተራ መጠየቅ ጀመርኩ፡፡

ጥያቄ 1. የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ያሉ የጽህፈት ክሂል ይዘቶች ዓላማውን ከግብ ያደርሳሉ? ለምላሹ ተጨማሪ ማብራሪያ ቢሰጥ

መምህርት 2፡‹‹አዎ! ተማሪዎች ያሰቡትን በመጻፍ ብቻ ሳይሆን የሚማሩትንም ቢሆን በአግባቡ ጽፈው እንዲማሩ የሚያግዙት ዝግጅቶች አሉበት፡፡››

ጥያቄ 2.ከጽህፈት ክሂል ይዘቶች አቀራረብ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ  እና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአቀራረብ ስልት የቀረቡ ናቸው?ምላሹ ቢብራራ

መምህርት 2፡‹‹አዎ የቀረበ ነው፤በተለይ መልመጃዎችን ስናሰራ ምሳሌዎች እና ሞዴሎችን በማየት የሚያሰሩ መልመጃዎች ስላሉ እነኚህ አጠቃላይ ከሆነ ይዘት ወደ ዝርዝር እንደሆነ ጥቆማ ይሰጠናል፡፡››

ጥያቄ 3.የጽህፈት ክሂል አቀራረቡ ውጤት ተኮር እና ሂደት ተኮር አቀራረብን አካቷል ? ምላሹ ትንሽ ቢብራራ

መምህርት2፡‹‹አካቷል ፤ስናስተምራቸው ወይም ሥናጽፋቸው የመልመጃዎቹ ትዕዛዝ እና ይዘቱ ይጠቁመናል፤በመሆኑም በመማር ማስተማር ሂደት በጽህፈት ጊዜ ከውጤት ይልቅ በሂደት ላይ ትኩረት የሚያደርጉ መልመጃዎችና ይዘቶች አሉ ፡፡››

ጥያቄ 4.የጽህፈት ክሂሎች የይዘት አደረጃጀት ተከታታይነት እና ተለጣጣቂነትን መርህ አሟልቶ የተዘጋጀ ነው?

መምህርት2፡‹‹ያሟላል፤ከታችኛው ክፍል ተያይዞ የመጡ የጽህፈት ክሂል መልመጃዎች አሉ፤ በተጨማሪ ከአማርኛ ትምህርቶች ጋር የህብረተሰብ ትምህርቶች ይገናኛሉ፡፡››

ጥያቄ 5. የጽህፈት ክሂል መልመጃዎች ጎናዊ እና ተዋረዳዊ የሆነ ግንኙነት አላቸው?

መምህርት2፡ከ9ኛ ክፍል ተያይዘው የመጡ መልመጃዎች አሉ ግን ትንሽ ከበድ ይላሉ፤››

ጥያቄ 6.ለጽህፈት የተመረጡት መልመጃዎች ተተገባሪ ናቸው?ምላሹ በብራራ

መምህርት 2፡‹‹አዎ፤በተለይ ሰፋ ባለ ምሳሌ የተሰጡ መልመጃዎችና በቡድንና በጥንድ እንዲሰሩ የተዘጋጁት መልመጃዎች በተማሪዎቹ የሚሰሩ ዓይነት ስለሆኑ ለመተግበር የማያስቸግሩ ናቸው፡፡

ጥያቄ 7. የጽህፈት መልመጃዎቹ ተማሪዎች ለብቻቸው እና ከመምህሩ ጋር ለመስራት የሚያስስችሉ ናቸው?

መምህርት 2፡አዎ ሁለቱንም መምህሩንና ተማሪውን ማዕከል ያደረጉ ናቸው፡፡››

ጥያቄ8.አጠቃላይ የጽህፈት ክሂሉ ይዘቶች የተማሪውን ዳራ ያገናዘቡ ናቸው ?መምህርት 2፡‹‹አዎ፤ከማህበረሰቡ፣ከአካባቢው በመገንዘብ ከባህሉ፣ከቴክኖሎጂ ጋርባለውግንኙነት የሚሰሩዋቸው መልመጃዎች ስላሉ ከተማሪው ዳራ ጋር ቅርበት ያላቸው ናቸው፡፡

# ማረጋገጫ

እኔ ቤዛዬ ፀጋዬ ኃይለማርያም በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ ተማሪ የሆንኩ ‹‹በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር የመጀመሪያ እትም 2014 ዓ.ም የሆነው አማርኛን እንደፌዴራል ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀውን የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መጽሐፍ ውስጥ የመፃፍ ክሂልን የይዘት አደረጃጀት እና አቀራረብ መገምገም››በሚል ርዕስ በድህረ ምረቃ መርሀ ግብር ለኤምኤ ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ጥናት ከዚህ በፊት በማናም ያልተሰራ የራሴ ሥራ ሲሆን ለሥራው የተጠቀምኩት ድርሳናት እና ዋቢዎች የራሴ ሥራ መሆናቸውን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ቤዛዬ ፀጋዬ ኃይለማርያም

ፊርማ---------------------------

ቀን--------------------------------